# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐግብር

**ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ክሂሎት ለማዳበር የሚኖረዉ ሚና (በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)**

**የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ**


**በ**

**መሐመድ አደም**



ሐምሌ 23፣ 2013

ጅማ

# ትብብራዊ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማንበብ ክሂሎት ለማዳበር የሚኖረዉ ሚና (በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ለማሰተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ የጥናት ጽሁፍ

በ

መሐመድ አደም

የጥናቱ ዋና አማካሪ፡- ዶ/ር ምህረት ሳዳም

የጥናቱ ረዳት አማካሪ፡- ዶ/ር ለማ ንጋቱ

ሐምሌ፡ 2013

ጅማ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር

# አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ የጥናት ጽሁፍ

‹‹ትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት›› በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል፣ የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር፤ የሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያነት፣ በመሀመድ አደም ሮሮ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራት እና የወጥነት መስፈርት ስለሚሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡ ፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ________________________________ፊርማ________ቀን____________

የውጭ ፈታኝ__________________________ፊርማ________ቀን____________

የውስጥ ፈታኝ__________________________ፊርማ________ቀን____________

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት በጅማ ዞን ሲግሞ ወረዳ በሲግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ‹‹ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረዉን ሚና መመርመር በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ የሰራሁት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል በድህረ ምረቃ መርሃ ግብር፣ የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር፤ ለሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያነት እንዲሆን ያቀረብኩት ሲሆን ጥናቱ ካሁን በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራና የራሴ ሥራ መሆኑን፤ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች ያደረግኳቸዉና ጅማ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ ማረጋገጥ እወዳለሁ፡፡

ስም መሀመድ አደም

ፊርማ_______________

ቀን_________________

# ምስጋና

አልህምዱ ሊላህ ለዚህ ላበቃኝ ፈጣሪዬ ምስጋናህ ገደብ የለዉም! በመቀጠል ይህን ጥናቴን ከውጥኑ ጀምሮ ተጠናቆ ለዚህ እንዲበቃ አስፈላጊዉን አቅጣጫ በማመልከት ወርቃማ ጊዜያቸዉንና የዳበረ እዉቀታቸዉን ሳይሳሱልኝ ረቂቁን ሳይሰላቹ በማንበብ እና እርማት በመስጠት አስፈላጊውን ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዎቼ ለዶክተር ምህረት ሳዳም እና ለዶክተር ለማ ንጋቱ ልባዊ አክብሮትና ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ለመልካም ትህትናቸውም የተለየ አድናቆት አለኝ፡፡ እንዲሁም ለተቀሩት የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ክፍሉ ሀላፊዎች፣ መምህራንና ለክፍል ጓደኞቼ ገንቢ አስተያየትና ማበረታቻ በመስጠት ላደረጉልኝ ወንድማዊና እህታዊ እገዛ ምስጋናዬ እጅጉን ላቅ ያለ ነው፡፡

በሌላ በኩል ይህን የትምህርት እድል አግኝቼ እንድማር ከዛም ባለፈ ለማጠቃለያዉ ጥናት የትግበራ ሂደት ከአጠገቤ በመሆን በጥናታዊ ሥራው ላይ ከፍተኛ ድጋፍ የሰጣቹኝ የሲግሞ ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ የሲግሞ 2ኛደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህርና መምህራን ምስጋናዬን ሳቀርብላችሁ አድናቆቴ ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይም ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ምክር በመስጠት፣ ክፍሎችን በማመቻቸት፣ በመፈተንና በማረም የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠት እስከ መጨረሻው ከጐኔ ላልተለዩኝ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በእጅጉ ሳደንቅ በተለይ ከጅምሩ ትምህርቴን እንድማር መልካም ድጋፍና ትብብር ላደረጉልኝ የወረዳዉ አስተዳደርና ሲቪል ሰርቪስ ጽ/ቤቶችን ከልቤ ማመስገን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም የቤትና የቤተሰብ ሀላፊነት በሙሉ አቅሙዋ በመሸከም ሰርታ እንድማር ላደረገችልኝ ዉድ ባለቤቴ ወ/ሮ መርዲያ ከድር፣ አይዞክ በርታ ሲሉኝ የነበሩ ለልጆቼ ለጂቱ፣ ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ለሚገኘዉ ልጄ ተዉፊቅ፣ ለናዲያ፣ ለወንድሞቼ በተለይ ለተማም እና ባለቤቱ እንዲሁም አይዞክ በማለት በትእግስት ከጐኔ ላልተለያችሁኝ የባለቤቴ ቤተሰቦችና መላዉ ዘመዶቼ እና ጓደኞቼ በሙሉ ላደረጋችሁልኝ ማነቃቃትና ለትምህርቴ ስኬት ላደረጋችሁልን መልካም ትብብራችሁ ከፍተኛ ልባዊ ምስጋናዬ በአድናቆት ይድረሳችሁ እያልኩ በመጨረሻም ለዚህ ጥናት ስራ መሳካት የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን የጅማ ዩኒቨርሲቲን ከዉስጤ ያለኝን አድናቆቴን እገልጻለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትብብራዊ መማር ዘዴን በመጠቀም ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና መመርመር ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ለማሳካት ከፊል ሙከራዊ የምርምር ንድፍ ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡ ከመተንተኛ ዘዴ አንጻር ደግሞ መጠናዊ ምርምርን የተገበረ ጥናት ነዉ፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎችም በሲግሞ ወረዳ በሲግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በመማር ላይ ከሚገኙ አጠቃላይ 353 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 62 ተጠኚዎች በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ በክፍላቸዉ 10ኛ D እና 10G ተጠመረጡ፡፡ ቡድኖቹም ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር በድኑ መካከል የማንበብ ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ቅድመ ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ በውጤቱም በመካከላቸዉ ጉልህ የሆነ ልዩነት የሌለና ተቀራራቢ መሆናቸዉ ተረጋግጧል፡፡ በመቀጠልም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ትብብራዊ መማር ዘዴን በመተግበር የተዘጋጀላቸውን የመለማመጃ ትምህርቶችን ለተከታታይ ስድስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ቀን  እንዲማሩ በማድረግ የድህረ ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ይዘት የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደዉ ዘዴ በመማር ፈተናዉን ወስዷል፡፡ ለነሱም ተመሳሳይ ድህረ ፈተና ተዘጋጅቶ በተመሳሳይ ሰአት እንዲፈተኑ ተደርጓል፤ ውጤቱም በድምዳሜያዊ ገላጭ ስታቲስቲክ በቲ-ቴስት አማካኝነት ተተንትኗል፡፡ የትንተናዉ ዉጤት እንዳመለከተውም በድህረ ፈተናዉ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ከቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የተሻለ አማካይ ውጤት (ቲ 60=-2.425, p=.018) በማስመዝገብ ብልጫ ማሳየቱን ነዉ፡፡ ይህም ውጤት በቡድኖቹ መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል ምክንያቱም የተገኘዉ የp ዋጋ P=0.18 ከ0.05 አንሶ መገኘቱ ነዉ፡፡ በመሆኑም(0.18<0.05) ይህ ዉጤት የሚያሳየዉ የሙከራ ቡድኑ የንባብ ችሎታ ዉጤት መሻሻሉን ነዉ፡፡ ስለሆነም ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታን ለማሻሻል ትብብራዊ የማስተማሪያ ዘዴዉ ወሳኝ ሚና እንዳለው ከጥናቱ መረዳት ይቻላል፡፡

## ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ ii
ማውጫ ........ iii
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ vi
ምእራፍ አንድ፤ መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 5
1.3 የጥናቱ መላምቶች ........ 6
1.4 የጥናቱ አላማዎች ........ 6
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 6
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 7
1.7 የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ ........ 7
ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ........ 9
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ........ 9
2.1.1 የማንበብ ክሂል ምንነት ........ 9
2.1.2 የማንበብ ትምህርት አላማ ........ 9
2.2 የንባብ ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎች ........ 11
2.2.1 ቅድመ ንባብ ደረጃ ........ 11
2.2.2 ጊዜ ንባብ ደረጃ ........ 12
2.2.3 ድህረ ንባብ ደረጃ ........ 13
2.3 የማንበብ ትምህርት የመልመጃ ጥያቄዎች ዓይነት ........ 14
2.4 የንባብ ስልቶች ........ 15
2.5 የትብብር መማር ንድፈ ሃሳቦች ከንባብ ክሂሎት አንጻር ........ 19
2.6. በትብብር መማር ማስተማር ምንነት ........ 22
2.7 የትብብር መማር ጠቀሜታ ........ 22
2.8 በትብብር መማር መሰረታዊ መርሆች ........ 25

2.9 በትብብር መማርና በተለመደዉ መማር(ገለጻ) መካከል ያለዉ ልዩነት ........................ 28
2.10 የትብብር መማር ስልቶች ........................ 30
2.11 በትብብር መማር ሂደት የመምህራን ሚና ........................ 33
2.12 በትብብር መማር ወቅት የተማሪዎች ሚና ........................ 33
2.13 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................ 35
ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ........................ 38
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........................ 38
3.2 የጥናቱ አካላይ ........................ 38
3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........................ 38
3.3.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ ........................ 39
3.3.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........................ 39
3.3.3 የተማሪዎች አመራረጥ ........................ 39
3.4 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ........................ 40
3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................ 40
3.5.1 ፈተና ........................ 40
3.5.2 የጽሁፍ መጠይቅ ........................ 42
3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................ 43
3.7 የጥናቱ አተገባበር ሂደት ........................ 43
3.7.1 የትብብራዊ መማር ቡድኑ አደራጃጀት ........................ 44
3.7.2 በትብብራዊ ቡድን ሚና የመከፋፈልና የስራ ድርሻ ሁኔታ ........................ 44
3.7.3 በትብብራዊ መማር የግልና የቡድን ጽብረቃ ሂደት ........................ 46
3.8 የቅድመ እና ድህረ ፈተና አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት ........................ 46
3.9 የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ........................ 47
3.10 የናሙና ሙከራዉ ጥናት አካሄድ ........................ 47
ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የወጤት ማብራሪያ ........................ 49
4.1 የመረጃ ትንተና ........................ 49
4.1.1 የቁጥጥር ቡድኑ እና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና ትንተና ........................ 50
4.1.2 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና ትንተና ማሳያ ........................ 51

4.1.3 የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ትንተና ........................................ 53
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........................................ 54
ምዕራፍ አምስት፤ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ........................................ 58
5.1 ማጠቃለያ ........................................ 58
5.2 መደምደሚያ ........................................ 59
5.3 አስተያየት ........................................ 59
ዋቢዎች ........................................ 61

# አባሪዎች

አባሪ ሀ፡- የናሙና ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የንባብ ችሎታ የቅድመናየድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤቶች-----------------------------------------------------------------------------------------------65

አባሪ ለ፡- የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና ዉጤቶች ማሳያ--------------------------------------------------------------------------------------------------66

አባሪ ሐ፡- የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና ዉጤቶች---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------67

አባሪ መ፡- በናሙና ሙከራዊ ጥናቱ ተማሪዎች ስለትብብራዊ መማር ያላቸዉን አስተያየት በሚመለከት ቅድመ የጽሁፍ መጠይቅ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ማሳያ-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------68

አባሪ ሠ፡- ተማሪዎች በናሙና ሙከራ ጥናቱ ስለትብብራዊ መማር ያላቸውን አስተያየት በተመለከተ በድህረ የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ-------------------------------------------------------------------68

አባሪ ረ፡- በሙከራዊ ጥናቱ ተማሪዎች ስለትብብራዊ መማር ያላቸዉን አስተያየት በሚመለከት በድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------69

አባሪ ሰ፡- ለተማሪዎች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ ማሳያ-------------------------------------------70

አባሪ ሸ፡- ለተጠኚ ተማሪዎች የቀረበ ቅድመ ት/ት የጽሁፍ መጠይቅ---------------------------71

አባሪ ቀ፡- የንባብ ችሎታ ለመለካት በቅድመና ድህረ ፈተና እንድሁም ስለ ትብብር መማር የተሰበሰቡ መረጃዎች በSPSS version 20 ተሰልተዉ የወጡ መረጃዎችን የሚያሳይ-----------------72

አባሪ በ፡- ቅድመ ትምህርት ፈተና------------------------------------------------------------------74

አባሪ ተ፡- የትብብራዊ መማር ግንዛቤን ለመፍጠር ተዘጋጅቶ የቀረበ ስልጠና ማንዋል------------------------------------------------------------------------------------------------------------------81

አባሪ ቸ፡- ለሙከራ ቡድኑ መማሪያ የተዘጋጀ የትምህርት እቅድ---------------------------------82

አባሪ ነ፡- ለተጠኚ ተማሪዎች የተዘጋጀ የማስተማሪያ ጽሁፍ--------------------------------------82

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡- የቁጥጥርና የሙከራ በድኑ ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት------------------------------------------------------------------------------50

ሠንጠረዥ 2፡- የቀጥጥርና የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት የችሎታ ውጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት-----------------------------------------------------------------------------------52

ሠንጠረዥ 3፡- የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት-----------------------------------------------------------------------------------------------------53

ሠንጠረዥ 4፡-የንባብ ችሎታ ለመለካት በቅድመና ድህረ ፈተና እንድሁም ስለ ትብብር መማር የተሰበሰቡ መረጃዎች በSPSSversion 20 ተሰልተዉ የወጡ መረጃዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ-----------------------------------------------------------------------------------------------72

ሠንጠረዥ 5፡- በትብብራዊ መማርና በተለመደዉ በቡድን ስራ መካከል ያለ ልዩነት ማሳያ-------81

# ምእራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ተቀዳሚ አላማዎች ተማሪዎች መሰረታዊያኑን የቋንቋ ክሂሎችን ከማዳበር በተጨማሪ ተጓዳኝ የቋንቋ ክህሎቶች የሆኑትን የሰዋሰዉና የስነ-ጽሁፍ እዉቀቶችን በማግኘት በማህበራዊ ኑሮዋቸዉ ዉስጥ ደረጃቸዉን የሚመጥን ተግባቦትን እንዲጎናጸፉ ማስቻል ነዉ፡፡ ከነዚህ ክህሎቶች ማንበብ አንዱ ነዉ፡፡ የዚህ ክህሎት መሻሻል ደግሞ ጠቀሜታዉ ለክህሉ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የቋንቋ ክሂሎችና እዉቀቶች መሻሻል የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ ለዚህም ይሆናል Nuttal (1982:3) "ማንበብ ተማሪዎችን በሚያነቡበት ወቅት ክሂሉን ማዳበር ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበርም የሚረዳ ክሂል ነው፡፡" ሲል የገለጸዉ፡፡ ከዚህ አገላለጽ የምንረዳው አንድን ጽሁፍ በማንበብ የሚናገኘዉ ጥቅም የማንበብ ክህላችንን ከማዳበር በተጨማሪ ደግሞ ሌሎች የቋንቋ ችሎታችንንም ከፍ እንድናደርግና እንድናሻሽል ሊያግዘን ይችላል ማለት ነዉ፡፡

የንባብ ክህሎት አላማ በዋናነት አንድን በጽሁፍ የቀረበዉን ነገር በማየት ትኩረት አደርገዉ የጽሁፉን መልእክት መረዳት ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ተማሪዎች በቃልም ሆነ በጽሁፍ ንባብን መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የማንበብ ችሎታ በጥቅልሉ ሲታይ አንድ ሰው ሊኖሩት ከሚገቡ አስፈላጊ ክሂሎች አንዱ ሆኖ ማንበብ በጽሁፍ የሚተላለፉ መልእክቶችን ለማግኘት ዋና መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡ አንብቦ መረዳትን የሚችል ሰው ችሎታዉን ለማዳበርና አእምሮውን በማዘዝ የአስተሳሰብ አድማሱን ለማስፋት እድል ይኖረዋል፡፡ በዚህ መነሻነት ማንበብ በመማር ሂደት ውስጥ ዋና ተግባር መሆኑን መገንዘብ እንደሚቻል እና ይህ ሲሆንም የንባብ ክህል የመማር ሂደቱን ማሻሻልም የማንበብ ፍላጎት  እንደሚያነሳሳ አጥኚዎች ይገልጻሉ፡፡ ለተማሪዎች የንባብ ችሎታ መዳበርና መሻሻል የማንበብ ትምህርት አሰጣጥ እና  አቀራረቡ ደግሞ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ መምህራን የሚጠቀሙባቸዉ ማንበብን የማስተማሪያ ዘዴ ከወቅታዊ እና ዉጤታማ የማንበብ ትምህርት ንድፈ ሀሳቦችና መርሆዎች ጋር እንዲጣጣም ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎትን ከማነሳሳት እና ችሎታዉንም ከማሻሻል አንጻር የጎላ ሚና ያላቸዉ አያሌ ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴዎች ወይም አሳታፊ የማስተማር ዘዴዎች መኖራቸዉ የታወቀ ነዉ፡፡ ከነዚህም የትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎች በትብብር የመማር ማስተማር አንዱና የዘመኑ ዉጤታማ የማስተማር መማር ስልት

መሆኑን በምሁራኑ ተብሎለታል፡፡ johnsonJohnson (1999) እንዳብራሩት፡ በትብብር መማር ማስተማር እ.ኤ.አ.ከ1960ዎቹ ወዲህ በአንደኛ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሁም ዩኒቨርስትዎችን ጨምሮ መተግበር መጀመሩንና ዛሬም በብዙ ሀገሮች እየተሰራባቸዉ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ትብብራዊ የመማር ዘዴ ተማሪዉን ያማከለ እና አሳታፊ መሆን እንደሚገባዉ በማሳሰብ የሚታወቀዉ የስነ ትምህርት ባለሙያዉ የዴይዊ ፍልስፍና መሆኑን፤ sharan(1999)፣ ጊሌስ እና Ashman(2003) ገልጸዋል፡፡ ይህም የዴይዊ አስተሳሰብ ትምህርቱ በሰዉ ልጆች የኑሮ ሁኔታ ከፍተኛ ሚና ስለሚኖረዉ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ፍላጎት መግዛት፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸዉን የማስፋትና አዳድስ ሀሳቦችን እንዲያፈልቁ ለማድረግ ሀላፍነት እንዳለባቸዉ በመግለጽ ዘዴዉ ከዚህ አንጻር ጠቃሚ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ይህን በማጠናከር በማረው (1998) ዋቢ የተደረጉት ኦዊንስና Astraten (1980) በትብብር በመማር ተማሪዎች ግላዊ ዓላማቸውን ከግብ የሚያደርሱት ከሌሎቹ ጓደኞቻቸዉ ጋር በጋራ ሲሰሩ ብቻ መሆኑን በመግለጽ፣ የትብብራዊ መማር የጋራ ግብና ዓላማ እንዳለው ይገልጻሉ። በተለምዶአዊ (ገለጻ) የመማር ሂደት ደግሞ የተወሰኑ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተወዳደሩ አየተፎካከሩ በሚሰሩት ስራ የአንዱ ውድቀት ወይም ሽንፈት ለሌላው ስኬት ምክንያት እንደሚሆንና የአሸናፊው ዓላማ ከግብ እንደሚደርስ አብራርቷል።

ከምሁራኑ ሀሳብ የምንረዳዉ መምህር መሩ የመማር ማስተማር ሂደት በተሻለ የሚሰሩትን ተማሪዎች አማካይ አደርጎ የሚሄድና አብዛኞችን ስኬታማ ከማድረግ አንጻር ጉድለቶች ያሉበት መሆኑን እና ተማሪ ተኮሩ ዘዴ ግን በጋራ በመተጋገዝና የጋራ ግብን ትኩረቱ አደርገዉ በመማር ሂደቱ ብዘዎቹ ተማሪዎች ዉጤታማ መሆን የሚችሉበት እድል የሚፈጠርበት መሆኑን ከአገላለጻቸዉ መረዳት ይቻላል፡፡ የተለያዩ ጥናቶችም እንደሚገልጹት በትብብር መማርን በክፍል ውስጥ በመተግበር ማስተማር በተማሪዎች መማር ላይ አዎንታዊ ውጤት ማስመዝገቡን kasar (2003) እና haberian (2007) አረጋግጠዋል። እንዲሁም johnson&Johnson (1989) እንዲሁም kumare (2013) በትብብር በመማር ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች በጥንታዊ ዘዴ ከተማሩት ጋር ሲነፃፀሩ ፅንሰ ሀሳብን በጥልቀት የመረዳት ችሎታቸው፣ የማስታወስ አቅማቸው የርስበርስ ግንኙነታቸውና የትምህርት ውጤታቸው እንደተሻሻለ ገልጸዋል፡፡ johnson (2008) በበኩላቸው ማንበብን ማስተማር ብቻ ሳይሆን

ማንበብን ለመማር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተማሪዎችን ለጥሩ ውጤት እንደሚያበቃና የማንበብ ተነሳሽነትንም እንደሚያሳድግ ያብራራሉ። ለዚህም ይሆናል Nunan (1989)፣ Natall (1996) የተማሪዎች የተሳታፊነት ስሜት ሊጐለብት የሚችለው በፀጥታ ከሚያነቡ ወይም መምህራንን ብቻ ከሚያዳምጡ ይልቅ በክፍል ውስጥ ተግባራትን በራሳቸው ባግባቡ በመፈፀም ዕውቀትን ማግኘት ሲችሉ ነው በማለት የገለጹት። አያይዘዉም በዚህ ዘዴ መማር ማንበብ ለተማሪዎች የመዝናናት ስሜትን በመፍጠር እግረ መንገዳቸውን በክሂሉ ላይ ይበልጥ ፍላጐት እንዲያድርባቸው ያደርጋል፤ በማለት ገልጸዋል። በዚህ ጥናትም አጥኚዉ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ከማሻሻል አንጻር ዘዴዉን በከፊል ሙከራዊ ጥናት ተግባራዊ በማድረግ ሚናዉን ለማረጋገጥ የተነሳሳበት፡፡

የማንባብ ክህሎትን ማስተማር በቋንቋ ትምህርት ተካተዉ መሰጠት ከተጀመረ አመታትን ስለማስቆጠሩ በመግለጽ Rojers & Richards(2005፡5) በሂደቱም የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ትኩረት ተሰጥቶ ይተገበር እንደነበር ገልጾታል፡፡ ይሁንና ዘርፉ ዛሬም ማደግ ከሚገባዉ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ገና በርካታ ችግሮች ያሉበትና ለዚህም አጥኚዎች ስለዚሁ ክሂል አሉታዊ አስተያየቶችን ሲሰነዝሩ ይስተዋላሉ፡፡ ለአብነትም የቋንቋ ክሂሎት ድክመት በተማሪዎች ዘንድ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ችግሮቹን እንደያዘ መዝለቁን ባዬ (1987)፣ ተስፋዬ(1981) ገልጸዋል፡፡ ይህ ችግር በኢትዮጵያ ብቻ የሚታይ አለመሆኑን የሚገልጹ የውጭ ሀገራት የቋንቋ ምሁራን በመጽሐፋቸው ለማስነበብ የሂዱበት ሁኔታም መኖሩን የጠቀሱ አጥኚዎች አሉ፡፡ “በዩኒቨርሲቲ ደረጃ እንኳን ብዙዎቹ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎትን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተማሩት መሠረት ሲተገብሩ አይታይም፡፡ ቁጥራቸው ይህ ነው የማይባል ተማሪዎች መጽሀፍን ለማንበብ ፍራቻና ጭንቀት ይታይባቸዋል›› Richards (1974፣100)፡፡ ለችግሩ እስከ ዩኒቨርሲቲ ዘልቆ ለመከሰቱ ደግሞ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ በምሁራኑ (Ellis1989, Richards 1974, Norrish 1983) ተገልጸዋል:: ከነዚህም ዋና ዋና ተብሎ ከተጠቀሱት የንባብ ክሂሎት ችግሮች መምህራን የሚከተሉት የማስተማር ስልት፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች /መጽሀፍት/ አዘገጃጀትና ስርጭት፣ የተማሪዎች ፍላጎት ማጣት፣ የክፍለ ጊዜ እጥረት እና የተማሪዎች ቁጥር በአንድ ክፍል ዉስጥ መብዛት አንኳር አንኳሮቹ ናቸው፡፡

ከቀረቡት ሀሳቦች የምንረዳዉ የማንበብ ክሂል በሀገራችን በትምህርትነት መሰጠት ከተጀመረ አመታትን ቢያስቆጥርም ክህሎቱ ከቋንቋ ትምህርት አንጻር እንደቆይታዉና እንደወሳኝነቱ

ተገቢዉን ትኩረት አግኝቶ ዉጤቱም የተፈለገዉን ያክል ለዉጥ ከማምጣት አንጻር ጉድለቶች ያሉበት ይመስላል፣ የዚሁ ማሳያ ተማሪዎቻችን ከትምህርት አለም አልፎም ዛሬ በስራ አለም ሲሰማሩ በርካታ ችግሮች ሲገጥማቸዉ እየተስተዋሉ ነዉ እንደ ባዬ(1987) የማህበረሰቡና የቀጣሪዎች እሮሮ እየተሰማ ስለመሆኑ ጠቁመዉታል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮችም ሁኔታ ስናየዉ የችግሮቹን ተጽእኖ መጠንና ሁኔታ በዝርዝር መፈተሽ የራሱ ጥናት የሚፈልግ ቢሆንም የትምህርት አቀራረባችን በምሁራኑም የተጠቆመ በመሆኑ ለድክመቱ የራሱን ድርሻ ያሳረፈበት መሆኑን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች አሉ፡፡

ይህንን ሁኔታ በሚደግፍ መልኩ አንድነት እርገቱ(2010) የማንበብ ክሂል ከአገልግሎቱ አንጻርም ሲታይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ቢሆንም ባለመሆኑ በየትምህርት ቤቱ የክህሎቱ ትምህርት አሰጣጥ ወጥ አይደለም ብዙ ክፍተቶች እንዳሉበት ገልጾ ከዚህ በመነሳት በተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች ክሂሉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሆነ መዓዛ ደጀኔ(1999)፣ እንግዳ ዘዉዴ(1992)ን በመጥቀስ ግሩም ጥበቡ(2003) አጥኚዎቹ በጥናታቸዉ ማረጋገጣቸዉን በምሳሌነት በማንሳት ያብራራ መሆኑን ከጥናቱ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለዚህ በተማሪዎች የማንባብ ክህሎት ላይ ችግሮች መኖራቸዉን እና ገና ጥናታዊ ሥራዎች ሊደረጉ እንደሚገባ ተመራማሪዎቹ ይጠቁማሉ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢም ላለፉት አመታት በመምህርነት ስራ ቆይታዉ ተማሪዎች በቋንቋ መማር ሂደት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንደኛው የማንባብ ክህሎታቸዉ መሆኑን በማስተዋሉ ብዙዎቹ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ደካማ ስለመሆኑ በየጊዜው ከሚያሰሯቸው የክፍል ዉስጥ መልመጃዎችና የግምገማ ስራዎች በመነሳት ያለባቸውን ድክመት አጥኚዉ መረዳት ችሏል:: ይህንን የተማሪዎቹን የማንበብ ክህሎት ድክመት ለመቅረፍ የትምህርት አቀራረቡን ትብብራዊ የመማር ዘዴን በሙከራ በመተግበር በተማሪዎች የማንባብ ክህሎት መሻሻል ላይ ለውጥ ያመጣ ይሆን? የሚለውን ለመመርመር አጥኚዉ በዚህ ርዕስ ላይ ትኩረቱን እንድያደርግ ሁኔታዎቹ አነሳስተዉታል::

የተማሪዎችን የማንባብ ችሎታን ማሻሻል የዚህ ጥናት መነሻ ከመሆኑም በላይ የችሎታዉ መሻሻል በትምህርት ጉዳይ ዛረም ብርቱ ትኩረት የሚፈልግ ሆኖ እያለ በቀደምት ጥናቶቹ የዘርፉ ችግር እልባት ያለማግኘቱ ርእሰ ጉዳዩን ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የማንበብ ክህሎት በትምህርት የሚገኝና የሚዳብር በመሆኑ በተማሪዎቻችን ዘንድ የዚህ ክሂል መሻሻል ደግሞ ለሌሎችም የቋንቋ ክህሎቶች መሻሻል ከሚሰጠዉ አስተዋጽኦ አንጻር ለዘርፉ መሻሻል ገና መፍትሄ የሚሹ ጥናቶች እንዲካሄዱ ጥረቶች ሊደረጉ እንደሚገባ ምሁራኑ ገልጸዉታልNunan(1991) እና Arningish(2010)፡፡ በመሆኑም እንደ አገላለጻቸዉ በተማሪዎች የማንበብ ክህሎት ላይ በርካታ ችግሮች ያሉ መሆኑን እና ለመፍትሄዉም ጥናቶች መካሔድ እንዳለባቸዉ ያመላክታል፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር፤ በተማሪዎች የማንባብ ክሂሎት መዳበር ላይ የሚኖረዉ ሚና መመርመር /በሲግሞ ወረዳ በሲግሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት/ ነዉ፡፡ አጥኚዉ ይህን ጥናት ለማካሄድ የተነሳሳበት በማስተማር ስራዉ አከባቢ ተማሪዎች በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንደኛው የማንበብ ክሂሎት ችግሮች ያሉባቸዉ መሆኑን ተገንዝበዋል፡፡ ብዙዎቹ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ደካማ መሆኑን በየጊዜው ከሚያሰሯቸው የክፍል መልመጃዎችና ፈተናዎች ግምገማ በመነሳት ያሉባቸውን ክፍተት ለማስተዋል ችለዋል:: በተጨማርም እስካሁን በማንባብ ክሂል ዙሪያ የተካሄዱ ጥናቶች በዋና ዋና እና በትላልቅ ከተሞች እንጂ ወረድ ብለዉ በወረዳ ደረጃ የተካሄዱ ጥናቶች አልተገኙም፡፡ እስከአሁን ሲሰሩ የቆዩ ጥናቶችም ቢሆኑ በስካሁኑ ስራዎቻቸዉ አብዛኞቹ በክህሎት ዙርያ አንብቦ መረዳት፣ የንባብ ፍጥነትና ተዛምዶ ወዘተ…በመፈተሽ ላይ ያተኩሩ ነገር ግን አጥኚዉ እስከ ሄደበት ዳሰሳ በማስተማር ትግበራ ከትብብራዊ ዘዴ አንጻር ክሂሉን ያልፈተሹ ናቸዉ፣ ከዚህም በተጨማሪ አጥኚዉ በስራ ላይ ቆይታዉ ከነበረዉ የማስተማር ልምድ አንጻር በአብዛኛዉ የነበሩት የማስተማር የክፍል ዉስጥ አቀራረብ ስልቶቹ ገለጻና መምህር መር በመሆናቸዉ ተማሪዎችን አሳታፊ ከመሆን አንጻር ክፍተቶች ነበሩት፡፡ አጥኚዉ የንባብ ትምህርት አቀራረቦች ካሉባቸዉ ክፍተቶች እንዳስተዋለዉ ተማሪዎችን ለማሳተፍ የሚደረግ ጥረት አናሳ በመሆኑ በክፍል ለንባብ የተዘጋጀዉን ጽሁፍ መምህሩ አንድ ዙር ያነብና በመቀጠል የተወሰኑ ጎበዝ ተማሪዎች አንብበዉት በርካቶቹ ከመሳተፍ አድማጭ በመሆን ወደ መልመጃ ይታለፋል፡፡ ይህ ደግሞ ለተማሪዎቹ ፍላጎት መነሳሳትና ለንባብ ክሂሉ መሻሻል የራሱ ተጽእኖ ሊኖረዉ ሲለሚችል ሂደቱ ለተማሪዎቹ የማንበብ አቅም መዳከም መንስኤ ሲለሚሆንባቸዉ ተማሪዎቹ በክፍለ ግዜዉ በቂ ትኩረት ሰጥተዉ

በትምህርቱ በንቃት ከመሳተፍ ይልቅ መሰላቸትና በወሬ በጫወታ ሲጠመዱ ይታዩ ስለነበር ይህ ሁኔታ ደግሞ እላይ ከተገለጹት ምክንያዎች በተጨማሪ የትምህርቱ አቀራረብ ከራሱ ጉድለቶች ሊኖሩት ይችላል ከሚል ሀሳብ፣ በመነሳሳት ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎቹን የንባብ ችሎታና ፍላጎት ላይ ለዉጥ ያመጣ ይሆን ? የሚለዉን ሁኔታ በጥናት መፈተሽ የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት ሆኗል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ለችግሩ መፍትሄ ለመሻት ቀጥሎ ያሉ መላምቶችን አስቀምጧል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መላምቶች

1. ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የሚያመጣዉ መሻሻል አለ፡፡

2. ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የሚያመጣዉ መሻሻል የለም፡፡

## 1.4 የጥናቱ አላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጅማ ዞን በሲግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ክህሎት ለማዳበር የሚኖረዉን ሚና መመርመር ነዉ፡፡ ጥናቱም በዚህ አብይ አላማ ስር ቀጥሎ የቀረቡ ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. በትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማሩት ተማሪዎች የንባብ ክህል ማሻሻል አለመሻሻሉን መመርመር፡፡

2. በትብብራዊ ዘዴ የመማር ትግበራ አንጻር ያለዉ ግንዛቤ ምን እንደሚመሲል መፈተሽ የሚሉት ናቸዉ ፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ሲጠናቀቅ መምህራን፣ ተማሪዎች እና የትምህርት ባለሙያዎች ስለትብብራዊ መማርና ትግበራ የነበራቸዉን ግንዛቤ በማሻሻል ዉጤቱም ቀጥለዉ በዝርዝር የቀረቡ ጠቀሜታዎችን ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

- በጥናቱ መላምት የተቀመጡ ሀሳቦች መጨረሻ ላይ በአዎንታዊነት ሊደረስባቸዉ እንደሚያስችል ይገመታል፣
- ትብብራዊ መማር ሂደቱ በትግበራ አንጻር ቅደም ተከተሉን በማሳየት ለንባብ ችግሮች መፍትሔ ለመሻት የራሱ አስተዋጽኦ ሊኖሩት ይችላል፡፡
- ተማሪዎች የንባብ ደረጃዎችን በትብብራዊ ዘዴ ቡድናቸዉ አመካይነት በጥናቱ ሞዴል መሰረት ተግባራዊ በማድረግ የማንበብና የመረዳት ችሎታቸዉ እንደሚሻሻል ይጠበቃል፡፡
- በመማር ማስተማር ሂደቱ ተሳታፊ የሚሆኑት አካላት መምህራንና ባለሙያዎች በምንባብ ትምህርት አቀራረብ የተሻለ ግንዛቤ በማግኘት ዘዴዉ እንደ ተጨማሪ ግብአት በመሆን ለተማሪዎች የማንበብ ክሂሎት መሻሻል የራሱ ድርሻ እንዲኖረዉ ሊረዱ ይችላሉ፡፡
- ወደ ፊት በዚህ ዘርፍ ለሚከናወኑ ተመሳሳይ ጥናቶች እንደመነሻ ግብአት በመሆን የራሱ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል ፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገዉ በሲግሞ ወረዳ ካሉት አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በሲግሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት ላይ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ቤቱ ከሌሎቹ ትምህርት ቤቶች በተሻለ ለጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ከጊዜ፣ ገንዘብና አቅም አንጻር ቅርበት ስላለዉ አመቺ በመሆኑ ነዉ፡፡ እንዲሁም የጥናቱም ትኩረት ከመሰረታዊያኑ የቋንቋ ትምህርት አላማ ክህሎቶች ማለትም (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጽሀፍ) መካከል በማንበብ ክሂል ትምህርት ላይ ብቻ ያተኮረ ነዉ፡፡ ከአቀራረብ ዘዴ አንጻርም በርካታ የማስተማር ዘዴዎች ቢኖሩም ጥናቱ የትብብር መማር ማስተማር ትግበራን በከፊል ሙከራዊ የጥናት ንድፍ መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ጥናቱ በ2013 ዓመተ ምህረት በሲግሞ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ  ትምህርት ቤት ካሉት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ከሚማሩት ተማሪዎች ዉስጥ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ የተገደበ ነበር፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት ተግባራዊ ብያኔ

*መላምት፡-* በምርምር ሂደት ለጥናቱ ስኬት ሊሆን ይችላል ወይም ሊሆን አይችልም ተብሎ የሚታሰብ የመጨረሻ ጊዜያዊ ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡

ትብብራዊ መማር፡- ተማሪዎች በሚማሩበት ክፍል አነስተኛ ቁጥር ባላቸው እና በሥርዓት በተደራጁ አናሳ ቡድኖች በመዋቀር አንድን የትምህርት ግብ ለማሳካት በጋራ በመሆን እየተደጋገፉ የግልና ጋራ አላማን ለማሳካት የሚሰሩበት ሥነ-ትምህርታዊ ዘዴ ይሆናል፡፡

ንባብ ክሂል፡- በዚህ ጥናት ሀሳብን ወይም መልእክትን በተመለከተ በጽህፈት የቀረበን ጽሁፍ አንብቦ በመረዳት መልእክቱን በራስ አመለካከት መግለጽ የመቻል ብቃነዉ፡፡ የሙከራ ቡድን፡- የንባብ ክህልን በትብብራዊ መማር ዘዴዉ የተማሩትን ወይም የተለማመዱትን ተማሪዎች መግለጽ ይችላል፡፡

የቁጥጥር በድን፡- የንባብ ክሂልን በገለጻና በግል በተለመደዉ የመደበኛው የትምህርት አሰጣጥ የተማሩትን ሊያመለክት ይችላል፡፡

የነጻነት ደረጃ፡- ጽንሰ ሀሳቡ ሂሳባዊ እሳቤ ሲሆን መሰረት የሚያደርገው የጥናቱ ተሳታፊዎችን ብዛት የሚያመለክት ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች

### 2.1.1 የማንበብ ክሂል ምንነት

ማንበብ የተነበበዉን ሀሳብ /መልዕክት/ ከመረዳትም አልፎ ምንባቡ የት? ለምን ዓላማ? እና በማን? እንደ ተጻፈ መመርመርንና ይህንንም በመገንዘብ መልዕክቱን ቃል በቃል ከመቀበል በላይ አመዛዝኖ መረዳትን ያመለክታል፡፡ ይህንንም በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን ከተሰጡት እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡ Williams (1984:3) "ማንበብ ተፈላጊውን መረጃ የማግኘትና የመረዳት ሂደት ነው፡፡" የመረዳቱ ሁኔታ ከሚነበቡት ዓላማ የማንበቢያ ስልት የተለያዩ ልሆን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአነባብ ስልት መለያየትን ሲያስቀምጡ Grellet (1981:3) "ከማስታወቂያ ፍሬ ሃሳቡን በገረፍታ የሚነበብ ሲሆን ሳይንሳዊ ምርምር ግን በጥልቀት ማንበብን ይጠይቃል" እነዚህ አገላለጾች የሚያስረዱን የአነባብ ስልታችን እንደ የአላማችን የሚለያይ መሆኑን እና ከመልእክቱም አንጻር ትኩረታቸዉ የሚለያይ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

Wallace (1992:4) ማንበብ አንባቢው ከጸሀፊው ጋር ግንኙነት ለመፍጠርና የጸሀፍውን ሃሳብ ለመረዳትና ለመተርጎም በግሉ የሚያደርገው ጥረት ነው፡፡ የተጠቀሰዉ ሃሳብ የሚያስረዳን ማንበብ አንባቢውን ከጸሀፊው ጋር ለማገናኘት እንደ አገናኝ ድልድይ የሚያገለግል መሳሪያ ሆኖ በመሳሪያነቱም አንባቢው በሂደቱ ጸሀፊዉ ለማስተላለፍ የፈለገዉን ሀሳብ እንዲተረጉም የሚያደርስ መሆኑን እንረዳለን፡፡ በአጠቃላይ ከምሁራኑ አገላለጽ የሚንረዳዉ ማንበብ በጽሁፍ የሰፈረን መልእክት መምረጥን፣ ማስተዋልን መመርመርንና ተጨባጩን እየገመገሙ ጽንሰ ሀሳቡን ከራስ ገጠመኝ ጋር ማዋሀድን የሚጠይቅ አንደምታዊ ይዘት ያለዉ የአእምሮ ስራን ያማከለ ክሂሎት መሆኑን እንረዳለን፡፡

### 2.1.2 የማንበብ ትምህርት አላማ

በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ የማንበብ ትምህርት የሚሰጥበት ዋናዉ አላማ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ለማዳበር ነዉ፡፡ የማንበብ አላማን በማስመልከት ሲገልጽ Nuttal (1982:21) ተማሪዎችን አላማ ነድፈዉ እንዲያነቡ በማድረግ ማስተማር ተማሪዎች የሚፈልጉትን መረጃ በፍጥነት አንብበው እንዲረዱ፣ አዳድስና ግራ የሚያጋቡ ሃሳቦች ብያጋጥማቸዉ እንኳ በትኩረት አንብበው ሃሳቡን እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፡፡

ከምሁሩ አገላለጽ የሚንረዳዉ በመማር ማስተማር ሂደት መምህራን ለተማሪዎቻቸዉ አላማን ነድፈዉ እንዲያነቡ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ከዚሁ አንጻር ተማሪዉ አላማ ነድፈዉ እንዴት ማንበብ እንዳለበት ከተረዳ ደግሞ የአነባብ ስልቱንም ማወቅ አይከብደዉም፣ በሂደቱም ስልቱን ማወቅ ደግሞ የጽሁፉን መልእክት አንብቦ ለመረዳት ይችላል ለማለት ነዉ፡፡

ከላይ እንደተብራራዉ የማንበብ ትምህርት በዋናነት የማንበብን ክሂል የሚያዳብር ሲሆን ዝርዝር አላማዎችም እንዳሉት በሚከተለዉ ሁኔታ Wallace (1992፡6) ገልጾታል፡፡

ማንበብ ለመጠንቀቅ ይረዳል፡፡ ማንበብ ሰዎችን አከባቢያቸዉን ለመረዳት እንዲችሉ ያግዛቸዋል፡፡ ይሂም ሰዎች አከባቢን ማወቃቸዉ ጠቃሚና ጎጂዉን በመለየት በተለያየ ሁኔታና አከባቢ በጽኁፍ የሚገለጹ ነገሮችን በማየት፣ አንብበዉ ከአደጋ ራሳቸዉን እንዲከላከሉ ወይም ለአደጋ እንዳይጋለጡ በማድረግ የአከባቢ ሁኔታ ለይተዉ ለማወቅ የማንበብ ክሂል የጎላ ፋይዳ እንዳለዉ ይገልጽልናል፡፡

ማንበብ ለመደሰትና ለመዝናናት ይጠቅማል፡፡ ማንበብ በቋንቋዉ ረገድ ክሂሉን ከማዳበር ባለፈም አእምሮን ለማስደሰትና ለማዝናናት ይጠቅማል፡፡ በማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎችን ለመዝናናት አላማ እንዲያነቡ ማድረግ ለተማሪዎቹ የማንባብ ፍላጎትን ሊጨምርላቸዉ እንደሚችል የሚሁራኑ ምክር ያሳያል፡፡

ማንበብ ለአዳድስ እዉቀት ይጠቅማል፡፡ የሰዉ ልጅ በማንበብ ስለ አከባቢዉ ሁኔታዎች፣ ስለአለማችን የቀደመ፣ ወቅታዊና የወደ ፊት ተጨባጭ ሁኔታዎች ግንዛቤ ያገኝበታል፡፡ አዳድስ የትምህርትም ሆነ ሌላ የተለያዩ እዉቀቶችን ለማግኘት ስለሚያግዘዉ ማንበብ ለአዳድስ እዉቀት ማግኛ ዘዴ መሆኑን ያስረደናል፡፡

ስለሆነም ከላይ የቀረቡት የWallace ሀሳቦች እንደሚያስረዱን ማንበብ አንዳንዴ ተማሪዎችን ለማዝናናት እንደሚጠቅም ይህን በማሳወቅ ማስተማሩ ደግሞ የማንበብ ፍላጎታቸዉን እንደሚያሻሽል፣ ችግር በሚኖርበት ሁኔታም አከባቢን ተረድተዉ ጽሁፎችን በማንበብ ከአደጋ ራሳቸዉን መጠበቅና ለመከላከል እንዲችሉ፣ እንድሁም አዳድስ እዉቀቶችን በማግኘት የተጨማሪ አዉቀት ባለቤት ለመሆን የሚረዳቸዉ በመሆኑ ይህን አዉቀዉ ከማንበብ በፊት አላማዉን ተረድተዉ በአላማ እንዲያነቡ ማስተማር ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## 2.2 የንባብ ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎች

የማንበብ ትምህርት የክፍል ዉስጥ አቀራረብ አሰልቺ በማይሆንና ሳቢ እንዲሆን ተደርጎ መቅረብ እንዳለበት ባለሙያዎች ያሳስባሉ፡፡ የትምህርት አቀራረብ ሳቢ መሆን የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሳል፡፡ በመሆኑም የንባብ አቀራረብ ደራጃዎችን በመጠቀም መማር እንዳለባቸዉ በሚከተለዉ ሁኔታ ያሳስባሉ፡፡ የማንበብ ደረጃዎች በማንበብ ትምህርት ወቅት የሚፈጠርን መሰናክል ለመቀነስ ይረዳሉ፡፡ እነዚህም በሶስት ደረጃዎች እንደሚከፈሉ ገልጸዋል፡፡ ግሩም (2003፡17) Karkas (2002) ን በመጥቀስ እንደገለጸዉ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ USAID /Ethiopia (2003፡14) የማንበብ ደረጃዎች ከማንበብ በፊት፣ በማንበብ ጊዜና ከማንበብ በኋላ ሲሆኑ በነዚህ ጊዜያት መምህሩና ተማሪው በማሰብ በመገመት፣ በማረጋገጥና በመፍጠር የነቃ ተሳትፎ ውስጥ ያሳልፋሉ፡፡ ትምህርቱ በነዚህ ተከፋፍሎ መቅረቡ በሙሉ ወይም ወደ ሙሉ የተቃረበ ስኬታማ የመማር ውጤቶች ያመራል፡፡ ይህም ማለት ትምህርቱ በደረጃዎች ተከፋፍሎ ቢቀርብ ተማሪው የትኛዉ ደረጃ ላይ ችግር እንዳለዉ መምህሩ ለይቶ ተማሪውን በመርዳት ውጤታማ እንድሆን እንደሚያደርገው የተገለጸበት ሆኖ ደረጃዎቹም በሚከተሉት ሁኔታ ይብራራሉ፡፡

### 2.2.1 ቅድመ ንባብ ደረጃ

ይህ ቀዳሚ ደረጃ አንባቢዎች/ተማሪዎች/ ጽሁፉን ማንበብ ከመጀመራቸዉ በፊት የጽሁፉን ርእስ የማስተዋወቅ ስራ የሚሰራበት፣ ፍላጎታቸዉን በመቀስቀስ ጽሁፉን ለምን እንደሚያነቡ ለማወቅና ሀሳቡን ለመረዳት እንቅፋት የሚሆኑ ሀሳቦችን በማንሳት አስቀድሞ ዝግጅት ለማድረግ እንዲችሉ የማድረጊያ ደረጃ ነዉ፡፡

ግሩም (2003፡17) Karkes (2002) ዋቢ አደርጎ በቅድመ ንባብ ጊዜ ስለ ትምህርት ርዕስ አጠቃላይ ነጥብ ማንሳትና ስለ ምንባቡ መላምቶችን አቅርቦ መገመት ያስፈልጋል፡፡ ይህም መደረጉ ለተማሪዎች እንዲያነቡ ከመታዘዛቸው በፊት በፍላጎታቸው እንዲያነቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ማቅረብ ተገቢ ይሆናል ይላል፡፡

Williams(1984) የቅድመ ንባብ ጊዜ ለተማሪዎች ርዕሱን ለማስተዋወቅና የማንበብ ፍላጎትን ለማነሳሳት፣ የሚያነቡበትን ምክንያት በማሳወቅ አንባቢዎችን ለማነቃቃት፣ ለማንበብ ዝግጁ እንድሆኑ ያደርጋል፡፡ በዚህም ጊዜ አንባቢዎች ምን? ለምን? ለማን? እንዴት? በየትኛው የማንበብ ስልት ማንበብ እንዳለባቸው በራሳቸዉ እንድወስኑ ይረዳቿል፡፡

USAID/ Ethiopia (2003:14) በዚህ ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን የቅድመ ንባብ ዕውቀትን ማነሳሳት፣ የማንበብ ፍላጎትን መቀስቀስ፣ የተማሪዎችን ቅድመ ዕውቀትን መገምገም፣ የአነባብ ስልቶችን በመጠቀም ማሳየት፣ ምንባቡን ከተማሪዎች ህይወት ጋር የተያያዙ እንድሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ስለዚህ በቀረበዉ የማንበብ ደረጃ አገላለጽ መሰረት በቅድመ ንባብ ደረጃ ተማሪዎቹ ለንባብ ከሚደረግ ዝግጅት ባለፈ ከርእሱ ጋር ተገቢዉን ትዉዉቅ ያደርጋሉ፣ ስለጉዳዩ ትንበያና የጽሁፉን አቅጣጫ በማሳየት እዲሞክሩና መነሳሳትን በመፍጠር አስቀድሞ መዘጋጀት እንዲችሉ ማድረግ ከመምህራኑ የሚጠበቅ መሆኑን ገለጻዎቹ ያሰረዱናል፡፡

## 2.2.2 ጊዜ ንባብ ደረጃ

በዚህ ደረጃ በቅድመ ማንበብ ደረጃ ለተነበዩት ትንበያ እና የቃላት ግምታዊ ፍች የሰጡበትን ለማረጋገጥ በሚያነቡበት ጊዜ ሲሆን እነዚህን ጉዳዮች በፍጥነት አንብቦ ለመረዳት መዓዛ ደጀኔ(2003) እንደጠቀሱት "ምንባቡ በአሰሳ እና በገረፍታ የአነባብ ስልት እንደሚነበብና የበለጠ መረጃን ለማግኘት በዝምታ የሚነበብበት ጊዜ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ተማሪዎቹ የጽሁፉን አደረጃጀት የሚለዩበት የቃላትን ፍች ከአውድ የሚረዱበት፣ ዝርዝር መረጃዎችን የሚያወጡበት ጊዜ ነው" በማለት ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Meiryun (1995:127) በዚህ ጊዜ ተማሪዎችን ርዕሱን ማስታወስ፣ ስዕሎችን፣ ሰንጠረዦችን ግራፎችን፣ ወዘተ ማሳየትና ተፈላጊውን መረጃ በዳሰሳና በገረፍታ እንዲያነቡ የሚደረግበት ደረጃ ነው፡፡ ቀደም ሲል የተነበዩትን ትንበያ ተፈላጊውን መረጃ ለማረጋገጥ ወይም ለመተው ግርፍ ንባብ የሚካሄድበት፣ እንደገና የሚነበቡበትና ተማሪው ትንበያ ወይም የመጀመሪያውን የሚከልስበት ደረጃ ነው፡፡

ግሩም(2003፥19) Karakas(2003:16) በዚህ ደረጃ አንብበው እንዲረዱ መምህራን አስቀድመው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ጋር የእርስ በርስ መማማርና መገማገም እንዲኖራቸው ስለ ጽሁፉ አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ሊጠይቁ ይገባል፡፡ በዚህም ጊዜ በጸሀፊውና በአንባቢዎቹ መካከል ያለው መስተጋብር እንዲፋጠን የቋንቋ መምህራን የዳሰሳ፣ የገረፍታና የገለጻ ስልት ተግባሮችን ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ይህን ማድረግም የጽሁፉ መልዕክት በአንባቢዎቹ አዕምሮ ምስልን እንዲፈጥር ያደርጋል በማለት ያሳስባሉ፡፡

### 2.2.3 ድህረ ንባብ ደረጃ

Williams (1984:1) የድህረ ንባብ ዓላማው የተነበበውን የጽሁፍ ሀሳብ ማንፀባረቅ፤ የጽሁፉን ሀሳብ ከራስ ገጠመኝ ፍላጎት ጋር በማያያዝ የራስን ዕወቀት መጨበጥ ነው፡፡ እነዚህንም ዓላማዎች ለማሳካት በምሁሩ አገላለጽ በዚህ ወቅት አንባቢዎች የተረዱትን ሀሳብ ከራስ የህይወት ልምድ ጋር እያይዘው በራሳቸው አገላለጽ የሚተነትኑበትና የሚያንፀባርቁበትን ክንውኖች ሊያቀርቡ እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

ግሩም (2003፡20) Karakas (2002) ዋቢ አድርጎ አንባቢዎች ምንባቡን አንብበው የተረዱትን ነገር ለማረጋገጥ መከለስ፣ መጠየቅና መመለስ፣ ማጠቃለያ መስጠት ተግባራትን ሲፈጽሙ በቀረበላቸው ጥያቄና መልሶቻቸው መካከል ያለውን ዝምድና ይፈትሻሉ፡፡ ቀደም ሲል በማንበብ ጊዜ ስሜት ያልሰጣቸውን ሀሳብ ተግባራትን ከጓደኞቻቸው ጋር በመለየት በመወያየት፣ ምንባቡን እንደገና በመከለስ በሚያነቡበት ወቅት ሀሳቡ በአዕምሮአቸው ውስጥ ምስሉን እንዲፈጥር ያደርጋል፡፡

በምሁራኑ አገላለጽ በዚኛዉ ደረጃ ተማሪዎች ከላይ በቀረቡት ደረጃዎች ያገኙትን ትምህርት የሚያጠናክሩበትና ወይም የማረጋገጫ ደረጃ ሆኖ ያገኙትን አዳድስ ዕወቀት ከግል ገጠመኞቻቸው ጋር በማጣጣም መልመጃዎችን በአግባቡ እንደየአቀራረባቸዉ ለመከወን ራሳቸዉን የሚያመቻቹበት ደረጃ መሆኑን እንረዳለን፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተመለከትነው የመስኩ ባለሙያዎች ማብራሪያዎች የሚንረዳዉ በነዚህ ሶስት ደረጃዎች ተጠቅሞ የማንበብ ትምህርትን ማስተማር ተማሪዎችን ለማንበብና የማንበብ ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያበረታቱና ለመማር ዕድል የሚሰጡ ሁኔታዎችን የሚፈጠሩበት መሆኑን ነዉ፡፡ እነዚህ ደረጃዎች ሲተገበሩ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስፈልጋቸውን የአነባብ ስልቶችን እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡ ለልምምዱ እንዲያመችም ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ጊዜ ርዕሱን በማየት ቀጥሎ በጽሁፉ ውስጥ ሊያገኙ የሚችሉትን ጭብጥ ነገር ይተነብያሉ፣ ዓላማ ይነድፋሉ ዓላማቸውም የአነባብ ስልታቸውን እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡ በማንበብ ጊዜ ደግሞ የተነበዩትንና የገመቱትን ግምት ለማረጋገጥ በዓላማቸው መሠረት በተወሰነው የአነባብ ስልት አንብበው እስከሚረዱ ያነባሉ፡፡ ያለአግባብ የተነበዩትን ይተዋሉ፡፡ በድህረ ማንበብ ጊዜ ደግሞ ከምንባቡ ያገኙት ዕወቀት

ቀድሞ ካላቸው ዕውቀት ጋር አዛምደዉ የእያንዳንዱ ደረጃ አንብቦ መረዳትን በተግባር የሚገልጹበት የማረጋገጫ ሁኔታና ደረጃ መሆኑን ያሳየናል፡፡

በተጨማሪም እነዚህ የማንበብ ደረጃዎች ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለመምህሩም የራሳቸዉ የሆነ መረጃዎችን ለመስጠት እንደሚጠቅሙ ነዉ፡፡ ይህም በቅድመ ማንበብ ጊዜ መምህሩ የተለያዩ የቅድመ እውቀት መቀስቀሻ ጥያቄዎችን በማቅረብ የተማሪዎችን ችግር ለይቶ እንድያዉቅ ይረዳል፡፡ በዚህም ለችግሩም መፍትሔ እንዲፈለግ ፍንጭና አቅጣጫን ይጠቁማል፡፡ በማንበብ ጊዜ ደግሞ መምህሩ በሰጡት ምሳሌ መሠረት ተማሪዎች ማንበብ መቻላቸውን ለመገምገም ያስችላቸዋል፡፡ በድህረ ማንበብ ጊዜ ከማንበብ በኋላ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ ውጤታማ የሚሆኑ ከሆነ የመምህሩ የማንበብ ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ አስተማማኝ መሆኑን መምህሩ ራሱንም እንዲገመግም እና ለበለጠ ስራ ራሱን እንዲዘጋጅ ይረደዋል ማለት ነዉ፡፡

## 2.3 የማንበብ ትምህርት የመልመጃ ጥያቄዎች ዓይነት

የመልመጃ ጥያቄዎች የማንበብ ልምድን ለማዳበር ተማሪዎች ካነበቡት ጽሁፍ አጠቃላይ መልዕክት የሚለይበት፣ የምንባቡን አወቃቀር ምን እንደሚመስል፣ በምንባቡ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተገለጹ እውነታዎችን መገንዘብ አለመገንዘባቸውን ለማረጋገጥና የተማሪዎችን ችግር ለይቶ ለመደገፍ  የሚሰጡት አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

መልመጃዎችን በተመለከተ Grellet (1981:5) የምንባቡን አወቃቀር ተማሪዎች አንብበው እንዲረዱ ለማድረግ ጥያቄዎቹ የምንባቡን አወቃቀር አስመልክተው ሊቀርቡ ይገባል፣ ይዘቱን እንዲረዱ ለማድረግ ደግሞ በምንባቡ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተገለጹ ይዘቶችን የሚጠይቅ ጥያቄ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ Nuttal(1982:132) ተማሪዎች አንብበው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎች ሊቀርቡላቸው ይገባል በማለት ያሳስባል፡፡

1. **ቀጥተኛ ጥያቄዎች፡-** የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ከቀረበው ምንባብ ውጭ ያልሆነ መልስ የሚሰጥበት ወይም ለጥያቄዎቹ መልሱን በቀጥታ ከምንባቡ አንብበዉ ከተረዱት በራሳቸው የሚመልሱት የጥያቄ ዓይነት የሚዘጋጅበት ሂደት ነው፡፡

2. **ማገናዘብና ማቀናበርን የሚፈልጉ ጥያቄዎች፡-** ተማሪዎች ከቀረበላቸው ምንባብ ያገኙትን እውቀት /ፍሬ ሀሳብ/ ሳያዛንፉ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እያገናኙ ጭብጡን በራሳቸው አገላለጽ አቀናብረው እንድገልጹ የሚያግዝ የጥያቄ ዓይነት ነው፡፡

3. **አንድምታዊ ግንዛቤ የሚፈልጉ ጥያቄዎች፡-** የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ ተማሪዎች በምንባቡ የቀረበውን ሀሳብ በቀጥታ ሳይሆን ከተለያዩ አቅጣጫ በመመልከትና በመመራመር የሚመልሱት ዓይነት በመሆኑ በትኩረትና በጥልቀት ማንበብ እንዳለባቸዉ ይመከራል፡፡

4. **የግምገማ ጥያቄዎች፡-** የምንባቡን ሀሳብና አጠቃላይ አወቃቀር፣ ይዘት፣ ወዘተ በተለያየ አቅጣጫ በማየት ጭብጡን ገምግመው በራሳቸው ሀሳብ እንዲገልጹ የሚጋብዝ ዓይነት ጥያቄ መሆኑ ነው፡፡

5. **የግል አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች፡-** ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ስላነበቡት ምንባብ ይዘት ያላቸውን ግላዊ አመለካከት እንዲገልጹ የሚጋብዙ የጥያቄ አይነቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በምሁራኑ ከተሰነዘሩ ገለፃዎች ተማሪዎች አንብበው መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በተለያዩ ሁኔታዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ ጥያቄዎችን ለተማሪዎች ማዘጋጀትም ሆነ እነሱም ለጥያቄዎቹ መልስ በተረዱትና በቀጥታ ከማንበብ ያገኙትን እንዲገልጹ መደረጉ በአላማ ለማንበብ እንዲችሉ ይገፋፋቸዋል፡፡ በተለይም ተማሪው በራሱ አገላለጽ የተረዳውን ሀሳብ ከገጠመኙ ጋር እያገናዘበ እንዲመልስ የሚጋብዙ ጥያቄዎች የተማሪውን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ ትምህርቱን በራሱ ፍላጎት እንድማርና አንብቦ የመረዳት ችሎታውን ለማዳበርና ለማሻሻል የሚሰጠው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ከገለጻዎቹ መረዳት እንችላለን፡፡

## 2.4 የንባብ ስልቶች

የንባብ ስልቶችን በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን ከሰነዘሩት የተለያዩ አስተያየቶች የተወሰኑትን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡ Grellet (1981:3) ከአንድ ጽሁፍ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ስንፈልግ የተለያዩ የአነባብ ስልቶችን ልንጠቀም እንደምንችል ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌ ማስታወቂያ ለማንበብ እና ሳይንሳዊ ጥናቶችን ለማንበብ የምንጠቀመው የአነባብ ስልት የተለያየ ነው፡፡ ይህም የሚያስረዳው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ

እንዲዳብር ከተለያዩ የአነባብ ስልቶች ጋር ተማሪዎችን ማስተዋወቅ ተገቢ መሆኑን ነው፡፡ የአነባብ ስልቶች የሚባሉትን በምሁራኑ እንደሚከተለው በዝርዝር የቀረቡት ናቸዉ፡፡

## 2.4.1 የትኩረት (ዝርዝር) ንባብ

ይህንን የአነባብ ስልት በተመለከተ Nuttal(1982:23) ከሚነበበው ምንባብ አጠቃላዩንና ዝርዝሩን ሀሳብ አንብቦ መረዳትንና መለየት የሚፈልግ በመሆኑ በጥንቃቄና በዝግታ ትኩረት ሰጥቶ ማንበብን የሚጠይቅ የአነባብ ስልት ነው፡፡ የትኩረት ንባብ ዓላማው ዋናውን ሀሳብ በጥልቀት መገንዘብ ማስቻል ነው፡፡ ግንዛቤውን ማስጨበጡ ፍሬ ሀሳቡን መረዳት ላይ ብቻ ሳይሆን ፍሬ ሀሳቡ እንዴት እንደተቀናበረ መረዳትም ጭምር የሚረዳ ስልት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱም የማንበብ ስልት ተማሪዎች ጽሁፉን አንብበው ጠቅላላ ፍሬ ሃሳቡን በመገንዘብ የራሳቸውን አስተያየት ከግል ገጠመኛቸው ጋር አገናዝበው እንዲረዱ የሚያግዟቸዉ ዘዴ መሆኑን ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ይህ የአነባብ ስልት አጠቃላይ መረጃዎችንና ዝርዝር መረጃዎችን በትኩረት በመመርመር መረጃዎችን ለመገንዘብ የሚደረግ የአነባብ ስልት ነው፡፡ የዚህ ስልት ጥቅሙም እውነትን ከግል አስተያየት ለመለየት፣ ገጠመኝን ከሚነበበው ጽሁፍ ሀሳብ ጋር ለማነፃፀርና ገምግሞ የተጣራ መረጃን ለማግኘት፤ በዋና ዋና እና በዝርዝር ሀሳብ መካከል ያለውን ዝምድና ለማየት፣ መመሪያን ተከትሎ ለመስራትናለመሳሰሉት እንደሚያገለግል ነው፡፡ በትኩረት የንባብ ስልት በጽሁፍ ውስጥ የቀረቡ ሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና፣ ድስኩርስ ቃላት አጠቃቀም፣ ወዘተ… ለእያንዳንዱ ነጥብ ትኩረት ሰጥተን ማንበብ አስፈላጊ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ከአገላለጹም እንደምንረዳው በዚህ የአነባብ ስልት ማንበብ በጽሁፍ ውስጥ ከሚገኙ ጥቃቅን ዱስኩር ቃላት አጠቃቀም አንስቶ እስከ ሰፊዉ የጸሀፊው አመለካከት ድረስ ያለውን ጭብጥ ለመረዳት ሰፊ ሚና የሚጫወት የአነባብ ስልት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## 2.4.2 የአሰሳ ንባብ

የአሰሳ ንባብ ከጽሁፍ ውስጥ በጊዜዉ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ተብሎ በፍጥነት የሚነበብ የአነባብ ስልት ነው፡፡ በዚህ ስልት በፍጥነት የሚነበቡ መረጃዎች ለምሳሌ /የአገር፣ የሰው፣ የነገሮች/ ስም፣ አሀዛዊ መግለጫዎች፣ ዓመተ ምህረት፣ ወዘተ ናቸው፡፡ በዚህ ስልት ተማሪዎች እንዲያነቡ ለማድረግም በምሳሌው የተጠቀሱትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ሊቀርቡ ይገባል፡፡ Nuttal (1982:34) ይህ የንባብ ስልት ትኩረታችንን ዝርዝር ጉዳይና በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ

ሳይሆን በምንፈልገው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ብቻ አድርገን እንድናነብ የሚያደርገን የአነባብ ስልት ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እንግዳ (1992፡29) Hyland (1995:104) ዋቢ አድርጎ በዚህ የአነባብ ስልት ትኩረት መደረግ ያለበት በሚፈለግ ነጥብ ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡ ስልቱ ተግባራዊ እንዲሆን ተማሪዎችን ከምንባቡ የሰዎችን ስም፣ ቀናት በምንባቡ የሚገኙበትን ስፍራ የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ማቅረብ፣ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አያያዥ ቃላትን ሀረጋትንና አባባሎችን ለይተው እንዲያመለክቱ በመጠየቅ፣ ተማሪዎች በዚህ ስልት እንዲያነቡ እንደሚያደርጋቸው ከምሁራኑ ሃሳብ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.4.3 የገረፍታ ንባብ

የገረፍታ ንባብ የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ምንባቡን እስከ መጨረሻ በፍጥነት የሚነበብበት ስልት ነው፡፡ አጠቃላይ መልዕክቱን ለማግኘት ተማሪዎች ሲለማመዱ ከአሰሳ ንባብ ስልት ባነሰ ፍጥነት እንዲያነቡ በማድረግ ማለማመድ ተገቢ ይሆናል፡፡ በልምምዱ ወቅትም ፍሬ ሀሳቡን ሊያገኙ የሚችሉበትን የጊዜ ገደብ ወስኖ ማለማመድ አስፈላጊ እንደሆነ Nuttal (1982:34) ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ እንግዳ (1992፡28) Hyland ጠቅሶ የዚህ አነባብ ስልት ዋና ዓላማው ምንባቡን በፍጥነት በመቃኘት አጠቃላይ የምንባቡን ሀሳብ መገመት ነው፡፡ በተጨማሪም እንግዳ (1992፡28) Hyland (1995)፤ Aebersold and Kield 1997) ዋቢ በማድረግ እያንዳንዱ አንቀጽ የራሱ የሆነ ፍሬ ሀሳብ እንዳለው፣ የመግቢያውና የመደምደሚያው አንቀጽ የምንባቡን መልዕክት አሳጥረው በመያዝ ለአንባቢያን ዳራዊ እውቀት እንደሚሰጡ ነዉ፡፡ ተማሪዎች በልምምዳቸው ወቅት እነዚህን ከላይ የቀረቡ ጉዳዮችን ካወቁ በኋላ በጽሁፉ አጠቃላይ ሀሳብና በዝርዝር ሀሳቡ መካከል ያለውን ዝምድና፤ እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ለመግለጽ ጸሀፊው የተጠቀማቸውን የቃላት አጠቃቀም ተረድተው የተረዱትን ነገር ግልጽ በሆነ መልክ ማቅረብ እንዲችሉ ማድረግ ነዉ፡፡ ተማሪዎች የአነባብ ስልቱን ተጠቅመው ምንባቡን እንዲያነቡ ለማድረግ የመልመጃዎች አቀራረብ ወሳኝነት እንዳለው ከምሁራኑ አገላለጽ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ተማሪዎች በዚህ በአነባብ ስልት እንዲያነቡ ለማድረግ እንግዳ (1992፡29) Nuttal (1996) እና Hyland (1995) ዋቢ አድርገው የሚከተሉትን ተግባራት እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- በአንቀጾቹ ውስጥ የተዛቡ ዐረፍተ ነገሮችን እንዲያቃኑ መጠየቅ

- በአንቀጾቹ የሃይለቃል መገኛ ስፍራንና የአንቀጹን ውስጣዊ ግጥምጥምያነት ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- ተዘበራርቀው የተቀመጡ አንቀጾችን እንዲያቃኑ መጠየቅና ስለምንባቡ አወቃቀር ያላቸውን ግንዛቤ የሚገልጹትን ጥያቄ መጠየቅ
- በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በተለያዩ ጸሀፊዎች የተጻፉ ጽሁፎችን በማቅረብ የትኛው የተሻለ የመልዕክት አገላለጽ እንዳለው የሚጠይቁ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡

እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ በገረፍታ ንባብ ስልት ተጠቅመው ተማሪዎች እንዲለማመዱ ማድረግ እንደሚቻል ያመለክታል፡፡

## 2.4.4 አመሳካሪ ንባብ

Grellet (1981) አመሳካሪ ወይም አውዳዊዉ ንባብ ስልት በጽሁፉ ውስጥ የቀረቡ የአዳድስ ቃላትን ሀሳብ ተማሪዎች በመረዳት ቃላቱን ከተለያየ አቅጣጫዎች አይተው ለመተርጎም የሚያስችላቸው የንባብ ዘዴ ነው፡፡ አቅጣጫዎችም ቃሉ ከአካባቢ ሁኔታ ጋር በማየት፣ ከባህል ጋር በማያያዝ፣ ከተለያዩ አስተሳሰቦች ጋር አያይዘው የሚመረምሩበት ሲሆን እነዚህም ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት ለተማሪዎች ፍንጭ መስጠት ሀሳቡን የመረዳት ፍጥነታቸውን እንደሚጨምርላቸዉ ይገልጻሉ፡፡

## 2.4.5 ሰፊ ንባብ

ይህ የአነባብ ስልት እንደስሙ በይዘቱም ሰፊና ሰፊ ጊዜን የሚጠይቅ ጽጉፍ የሚነበብበት ዘዴ ነዉ፡፡ እንድሁም ረጅም ልበወለድ፣ አጭር ልበወለድ እና ረጃጅም ጽሁፎችን ከክፍል ውጪ ማንበብን የሚጠይቅ ስልት ነው፡፡ ይህን የአነባብ ስልት ተማሪዎችን ለማለማመድ መምህራን የተለያዩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ቀደም ሲል የተጠቀሱ ጽሁፎችን እንዲየነቡ ሀሳቡን በክፍል አቅርቦት ላይ እንዲገልጹ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 2.4.6 ሂሳዊ ንባብ

ይህ ሂሳዊ የንባብ ስልትን አስመልክተዉ Meiryun(1995: 186) እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ የዚህ ንባብ ስልት አላማ ደራሲው ለማን? ምን? ለምን? እንደጻፈ ገምግሞ አስተያየት ለመስጠት ሲባል የሚነበብ የአነባብ ስልት ነው፡፡ ልምምዱን ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን

በተለያዩ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተጻፉ ጽሁፎችን በማቅረብ ተማሪዎቹ በጥልቀት አንብበው እንዲገመግሙ በማድረግ ማለማመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በምሁራኑ የተዘረዘሩ የአነባብ ስልቶች በአላማም ሆነ በአተገባበር የተለያዩ ቢሆኑም አንዱ የንባብ ስልት በሚተገበርበት ወቅት ሌላውም ዘዴ አብሮ በውስጡ ይኖራል፡፡ ማለትም ሰፊ የአነባብ ስልትን ተከትለን ስናነብ ሂስ እየሰጠን በትኩረት ስልት እናነባለን፤ ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ እየሰጠን እናነባለን፡፡ በተጨማሪም በአሰሳ በምናነብበት ጊዜ ተፈላጊውን መረጃ እስከምናገኝ በአሰሳ ካነበብን በኋላ መረጃውን እንዳገኘን ደግሞ መረጃዉን በደንብ ለመረዳት ያነባብ ስልታችን ወደ ትኩረት ንባብ ይቀየራል፡፡ ስለሆነም መምህሩ ይህንን ጉዳይ ተገንዝቦ እንደየአስፈላጊነታቸው በቅንጅት ሊያስተምራቸው እና አቀናጅተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ መርዳት እንደሚገባዉ ከአገላለጹ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.5 የትብብር መማር ንድፈ ሃሳቦች ከንባብ ክሂሎት አንጻር

ትብብራዊ መማር በዉስጡ የተለያዩ አተገባበር ዘዴዎችን ሊተገብር እንደሚቺል ይገልጻሉ፡፡ እንደ Johonson et al.(2000) and Ghaith (2003) ይህ ንድፈ ሀሳብ በዉስጡ የተለያዩ ዘዴዎችን የያዘ የጥቅል መጠሪያ ነዉ፡፡ ለዚህም አሳታፊ ስልት አስተዋጾኦ ካበረከቱት ንድፈ ሃሳቦች ሶስቱ የባህርያዊያን ንድፈሀሳብ፣ የአዕምሮታዊያን እና የማህበራዊ ግንባታዊያን ንድፈ ሃሳቦች ናቸው፡፡ የሶስቱንም ንድፈ ሀሳቦች አስተዋጽኦ ምሁራኑ ካቀረቡት የተወሰኑትን ቀንጨብ አደርገን በመዉሰድ ንድፈ ሃሳቦቹ በትብብር መማር ላይ ያበረከቱትንም አስተዋጽኦ አጠር አደርገን ለማየት እንሞክራለን፡፡

1. **የባሕርያውያን ንድፈ ሃሳብ**(Behaviourisms)፡- የዚህ ንድፈ ሃሳብ አራማጆች ሽልማትና ማነቃቅያ መስጠት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ጠቀሜታ እንዳለው የሚያምኑ ናቸው፡፡ ይህም በሽልማት የተበረታቱ ተማሪዎች በዉስጣዊ መነሳሳት የሚሰጣቸዉን ተግባራትን ደግመው ደጋግመው ይፈጽማሉ የሚል አስተሳሰብ አላቸዉ፡፡ በባህርያውያን እይታ ውስጣዊ መነሳሳት ወደ ውጤታማ መማር የሚያመራ ወሳኝ ተላውጦ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ የተመሰረተው በskinner ሲሆን በአነቃቂ ምላሽ ጽንሰ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ እምነት ነው።

እንደ skinner (1981) አገላለጽ መማር አነቃቂ ለሆነ ነገር ምላሽ በመስጠት የሚመጣ ዘላቂ የሆነ የባህሪ ለውጥ ነው፡፡ የዚህ ጽንሰ ሃሳብ አራማጆች የመማር ማስተማር ሂደት በአነቃቂ ምላሽ ስር የወደቀ ነው ብለው የሚያምኑ ሲሆን የመምህሩ ተግባር አነሳሽ የሆነ ነገር

በማቅረብ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲከናወን ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በትብብር መማር ውስጥ ማበረታቻ መስጠት ትልቅ ፋይዳ እንዳለውና ተማሪዎች ማበረታቻ ለማግኘት ሲሉ ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው እንዲሰሩ እንደሚያደርጋቸዉ ይገልጻሉ፡፡

2. **የአዕምሯዊያን ንድፈ ሃሳብ**(Cognitive psychology)፡- በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረት ተማሪዎች የክሂሎት ፈጣሪ ሆነው ይወሰዳሉ፡፡ ከአዕምሮ እድገት ትውረት ያገኘው ድጋፍ በትብብር መማር ተቀባይነት እያገኘ እንዲመጣ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ የአዕምሯዊያን ንድፈ ሃሳብ ውስጣዊ መነሳሳትን በትብብር መማር ጋር አቀናጅተዉ በማቅረብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የአዕምሮ እድገት ትውረት መሰረቱ የPiyajet (1954) እና የVigotiski (1962) ስራዎች ናቸው፡፡ Piyajet (1966) የራሳቸውን (1954) ስራ ጠቅሰው እንደገለጹት የእርስ በእርስ ግንኙነት ማህበራዊ እውቀቶችን ያስገኛል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም በትብብር መማር የጋራ ግቦችን ውጤታማ ማድረግ እንደመሆኑ የሌሎችን ስሜትና አስተያየት ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን እንደሚገባው ያብራራሉ፤ አክለውም በትብብር የመማር ሂደት ተማሪዎች ካላቸው የተለያየ እይታ ተነስተው የአስተሳሰብ ልዩነታቸውን ማጥበብ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስም ልዩነታቸውን ማጣጣም እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡ እንደ Piyajet (1962) ገለጻ እውቀት ውስጣዊ መነሳሳትን መነሻ በማድረግ ከልምድና ከአካባቢ ጋር መስተጋብር በመፍጠር የሚገነባ ነው፡፡ ይህ የአዕምሯዊያን ትውረት መምህሩ አነቃቂ የመማር ማስተማር አካባቢ እንዲፈጠር ያመቻቻል፤ ተማሪው በክፍል ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲኖረውና የመማር ማስተማር ሂደቱን ከመምህር ተኮር ወደ ተማሪ ተኮር ዘዴ እንዲቀየር ያደርገዋል፡፡ Vigotiski (1978) በሰው ልጅ አስተሳሰብና በማህበራዊ ግንኙነት መካከል ከፍተኛ ቁርኝት ያለ በመሆኑ መማር በተፈጥሮው ማህበራዊ ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም የግለሰቦች ማህበራዊና አዕምሯዊ እድገት በአካባቢያዊ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ Vigotiski (1978) የመዳበር ክልል በሚባለው ትውረታቸው በተሻለ የግንዛቤ ደረጃ ላይ ካሉ ተማሪዎች ጋር በአፍልቆት ክሂል ላይ የሚደረግ መስተጋብር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉትን ልዩነታቸውን አጥብበው ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርላቸው ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ተነስተን ይህ ትውረት በትብብር የመማር ዘዴ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ውጤታማ እንዲሆንና ተቀባይነት እንዲያገኝ አስተዋጽኦ ማበርከቱን እንረዳለን፡፡

በአጠቃላይ የPiyajet ትውረት መማር በተማሪው ንቁ ተሳትፎ የሚመጣ መሆኑን ትኩረት ሲሰጥ የVigotiski ትውረት ደግሞ ለመማር ማህበራዊ መስተጋብር ወሳኝ መሆኑን የሚያምኑ ናቸው፡፡ የሁለቱም ትውረት በትብብር መማርን በክፍል ውስጥ ለመተግበር አስፈላጊና የማይነጣጠሉ ሲሉ Vigotiski (1978) ያስርዳሉ።

3. **የማህበራዊ መስተጋብር ንድፈሃሳብ**(Socio cultural theory)፡- የማህበራዊያን እይታ ደግሞ የሚገለፀው የቋንቋና እውነታው ከቀደመ ልምድ የመነጨ ነው ይላሉ፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ ተማሪዎች ተከታትለው በትብብር እንዲማሩ የሚያደርግ ስለሆነ በትብብር ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ተማሪው ሁልጊዜ ሲሰራ ትክክለኛ መሆን አይጠበቅበትም፤ ምክንያቱም ስህተት መስራት ተማሪው ከስህተቱ ይማራል ብሎ ያምናል Johonson(1998)፡፡

የማህበራዊ መስተጋብር ትውረት በትብብር የመማር ዘዴ ከሌሎች የመማር ማስተማር ሞዴሎች የተለየ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ትውረት በ1920ዎቹ እና በ1930ዎቹ slaven፣ በ1940ዎቹ በደች፣ እንዲሁም በ1990ዎቹ በኮፋ ይበልጥ እየዳበረ መምጣቱን Johonson(2003) ይገልፃሉ፡፡ ንድፈ ሃሳቡ መማርን ከፉክክር ወደ ትብብር ተኮር ውይይት የቀየረ ነው፡፡ በእምነቱ እዉቀት ማህበራዊ ነዉ፡፡ ሰዎች እዉቀትን የሚገበዩት በመተባበር አብረዉ ሲሰሩ መሆኑን እንረዳለን፡፡ Johonson (2003) ዋቢ የተደረጉት Doch(1949) ሦስት አይነት ማህበራዊ የመደጋገፍ ጽንሰ ሃሳቦች አፍልቀዋል፡፡ እነሱም፡- አዎንታዊ፣ አሉታዊ (ውድድራዊ) እና ነፃ ማህበራዊ መደጋገፍ ናቸው፡፡

አዎንታዊ መደጋገፍ አነሳሽ ግንኙነትን የሚፈጥር ሲሆን አሉታዊ መደጋገፍ የመቃረን ውጤትን የሚያስከትል ነው፡፡ ነፃ ማህበራዊ መደጋገፍ ደግሞ ግንኙነትን የማያጠፋና መደጋገፍ የሚታይበት ነው፡፡ Johonson(2003) አዎንታዊ መደጋገፍን በመተግበር ግለሰቦች እርስ በእርስ እንዲረዳዱና እንዲበረታቱ ለማድረግ እንደሚያስችል ገልጸው በአሉታዊ መደጋገፍ ሂደት ግን ግለሰቦች የየራሳቸውን ግብ ለማሳካት እርስ በእርስ እንደሚፎካከሩና በነፃ ማህበራዊ መደጋገፍ ደግሞ ግለሰቦች ግላዊ ዓላማቸውን የሚያሳኩት እራስን ችሎ በመስራትና በግላዊ ጥረት እንጂ በመተባበርና በመፎካከር እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ እንደዚህ ንድፈ ሃሳብ እምነት በትብብር መማር፣ አዎንታዊ መደጋገፍ በአንድ ቡድን ውስጥ ባሉ አባላት መካከል መነሳሳትን ለመፍጠርና የቡድኑ አባላት ለጋራ ግብ መሳካት በጋራ እንዲጥሩ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ስለሆነም የቡድኑ አባላት በዚህ አይነቱ በትብብር መማርን

ውጤታማ ለማድረግ እርስ በእርስ የመደጋገፍ ሚናን ይጫወታሉ፡፡ ይህ ጥናትም አዎንታዊ መደጋገፍ አነሳሽ ግንኙነትን ከመፍጠር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የተገለጹት ሦስቱ ንድፈ ሃሳቦች በትብብር መማር ዘዴ ለንባብ ችሎታ መዳበር የየራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዳበረከቱና የተለያዩ ስብጥራዊ ዳራ(Hetrogenity background) ትዉረቶች ያሉት መሆኑን ምሁራኑ ከገለጹት መረዳት ይቻላል፡፡ Jacobs እና Hanna(2004)

## 2.6. በትብብር መማር ማስተማር ምንነት

ትብብራዊ መማር ጽንሰ ሀሳቡ አዲስ ባይሆንም በምርምር ዘርፍ እ.ኢ.አ ከ1970 ጀምሮ በተመራማሪዎች ዘንድ ትኩረት እያገኘ መምጣቱን ይነገራል፡፡ በመሆኑም በርእሱ ላይ የተለያዩ ተግባራዊ ስራዎችና ምርምሮች ሰፋ ባለ መልኩ መካሄድ መጀመራቸዉን ከሌሎች የማስተማር ዘዴዎችም የተሻለ ዉጤት ማስገኘቱን ይገልጻሉ Jacobs እና Hanna 2004)፡፡ በትብብር መማር ማለት በትናንሽ ቡድን የተከፈሉ ተማሪዎች አንድ ላይ በመሰባሰብ ለጋራ አላማ የሚጥሩበት፣ ሲሆን በቀላል ሰርተዉ ብዙ ደረጃዎችን የሚሄዱበት ዘዴ ነዉ፡፡ ስለዚሁ ሀሳብ Leyla(2010) በትብብር መማር የተለያየ የትምህርት አቀባበል ያላቸዉ ተማርዎች በአንድ ላይ ተባድነዉ ለጋራ አላማ በመረዳዳት እና በመተባበር የሚሰሩበት አካሄድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አለማየሁ(2009፡10) ሲገልጹ ‹‹ቁጥራቸዉ አነስተኛ የሆኑ ተማሪዎች በቡድን በመደራጀት የራሳቸዉን እና የሌሎችን የመማር ሂደትን የሚያሻሽሉበት ዘዴ ነዉ›› ብሎታል፡፡

ስለሆነም ከቀረቡት የምሁራኑ ገለጻ እንደምንረዳዉ በትብብር መማር ማለት በአንድ ክፍል ዉስጥ በትምህርት አቀባበላቸዉ /የተሻሉ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ/ ተብለዉ የተለያዩና በትናንሽ ቡድን ሆነዉ ነገር ግን ስብጥራቸዉን ከግምት በማስገባት ተደራጅተዉም እርስበርስ በመረዳዳት፣ በመደጋገፍ ተባብረዉም ለጋራ አላማ የሚሰራበት እያንዳንዱ የቡድኑ አባላት የራሳቸዉንና የሌሎችን የመማር ሂደት የሚያሻሽሉበት እና ለሚያከናዉኑት እኩል ተጠያቂ የሚሆኑበት የመማር አካሄድ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## 2.7 የትብብር መማር ጠቀሜታ

Richard & Renday (2002) የተለያዩ ጥናቶችን በመጥቀስ በትብብር መማር ያለውን ጠቀሜታ ሲገልጹ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ፣ ዘና ብለው መወያየት እንዲችሉ በማድረግ፣ ችግሮችን ተወያይተው እንዲፈቱ ማስቻል፣ ጥልቅ የሆነ የመስራት

ፍላጎት እንዲኖራቸው እና በአጭር ጊዜ እየተነጋገሩ ብዙ ጥያቄዎችን መስራት ይችላሉ ብለዋል፡፡

Lita rani (2009) ስለትብብር መማር ጠቀሜታ ሲገልፁ የተማሪዎች በጥልቀት ማሰብን ያጎለብታሉ፣ አካባቢን በደንብ ለመረዳት ያስችላል፣ ደከም የሚሉ ተማሪዎችንም አቅም ከፍ ያደርጋል፣ እንደ አንድ የመማሪያ ዘዴ አማራጭ በመሆን ያገለግላል በማለት ያስረዳሉ፡፡

አለማየሁ (2009) በበኩላቸው Veenman (2000) Kagan (2007) እና Jollife (2007) በመጥቀስ እንደገለፁት በትብብር መማር የተማሪዎችን የተሻለ የመማር ማህበራዊ ክሂሎትን፣ ስነልቦናዊ እድገትን አዕምሮአዊ ክሂሎትን ከፍ ሊያደርግ እንደሚችል አስረድተዋል፡፡

በአጠቃላይ ምሁራኑ ስለትብብር መማር ጠቀሜታ የገለፁትን ሀሳብ በሚመለከት ተማሪዎች ስለሚማሩት ነገር የበለጠ ግንዛቤ ለመያዝ በጋራ፣ በዉይይት፣ በክርክር ሁሉንም በማሳተፍ ስለሚሰሩ ሁሉም ተጠቃሚ መሆናቸዉን የሚገልጽ ሲሆን ይህን የሚያጠነክር ሌሎች ጠቀሜታዎችን ምሁራኑ ከገለጹት በቅደም ተከተል እንደሚከተለዉ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

**በትብብር መማር የአካዳሚካል ጥቅም አለዉ:-** አብዛኞቹ ተማሪዎችና የትምህርት ባለሙያዎች እንዳስቀመጡት የተማሪዎች መማር ከፍተኛ ደረጃ ሊደርስ የሚችለው በትብብር መማር መሰረታዊ መርህ የሆነውን አዎንታዊ መደጋገፍ፡፡ "ሁሉም ለአንድ አንድ ለሁሉም" የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ተማሪዎች ሲያዳብሩ ነው Akhtar et al( 2012)፡፡

በመማር ማስተማር ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች በትብብር እንዲሰሩ መደረግ ተማሪዎች በትምህርትና በማህበራዊ እሴታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በትብብር በሚማሩ ቡድኖች የሚወያዩትና በመከራከር በትምህርት ክፍለ ጊዜው የሚጠቀሙበትን መሳሪያዎች ፅንሰ ሀሳቦችን መረዳታቸውን መግለጽ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም እርስ በርሳቸው ለመረዳዳት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ እውነቶችን ለማስጨበጥ ይችላሉ፡፡ በትብብር መማር አላማው ተማሪዎች በትምህርታቸው ያላቸውን ስኬታማነት ከፍ እንዲል ማድረግ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው እርሰ በርሳቸው ለመወያየት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመፍጠር እንድማሩ በማድረግና በማነጋገር የላቀ ውጤት ለማምጣት ለማበረታታት ነው፡፡ Slavin & Cooper (1999) እንደገለጹት፡፡

**በትብብር መማር ፈጠራ እንዲጨምር ያደርጋል:-** በትብብር መማር የፈጠራ ሀሳብን ያጎለብታል ተማሪዎች በነፃነት በደስታ ሀሳባቸውን እንድገልፁ በማድረግ አዲስ ለተፈጠረ ችግር በራሳቸው መፍትሄ እንዲሰጡ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ Johnson & Johnson (2009) እንደጠቀሱት፡፡ በተጨማሪም በቡድን ውስጥ አብረው በሚሰሩበት ወቅት ከውድድር መንፈስ በመላቀቅ የራሳቸውን ሆነ የሌሎችን የቡድን ሀሳብ በማድነቅ እንድማሩ ያደርጋቸዋል፡፡ አብሮነትን ይለማመዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ በሌሎች ዘንድ የበለጠ መስራትና አዳድስ ሀሳብ በቡድኑ የማመንጨት አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡

**በትብብር መማር ስነ አእምሮአዊ ጥቅም አለዉ:-** ይህ ዘዴ በተማሪዎች ዘንድ የእርስ በርስ ግንኙነት እንድጠናከር ያደርጋል፡፡ በአነስተኛ ቡድን ውስጥ ሀሳባቸውን የመለዋወጥና በዚህ ላይም ምጋቤ ምላሽ የመቀበሉ እድል የተማሪውን በራስ የመተማመን የመከባበር ስሜቱን ይገነበዋል፡፡ በትምህርትም ክፍል ጊዜ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎች ስለሚሰጡት መልስ ለማሰብ ጊዜ ሳይሰጣቸው በብዙ ተማሪዎች ጥያቄ እንድመልሱ ስማቸው ይጠራል በትብብር መማሩ ይበልጥ አቀራራብና ደህንነቱን የጠበቀ አካሄድ ስለሆነ የተጠየቁትን ጥያቄ በሁሉም ፊት መልስ ለመስጠት አይፈሩም መጨናነቅም አይኖርባቸዉም፡፡ Johnson & Johnson (2009) ፡፡

**በትብብር መማር ማህበራዊ ጠቀሜታ አለዉ፡-** Johnson & Johnson (2009) በትብብር መማር ዋነኛው ጥቅሙ ማህበራዊ ክሂሎት ማስተሳሰሩ ነው የወዳጅነትና የመቀራረብ መንፈስ በመፍጠር የቡድኑ አባላት አዲስ ማህበራዊ ክሂሎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በትብብር መማር ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ አመለካከቶችን እንዲቀበሉ የሌሎችን ሀሳብና ስሜት በጥልቀት እንዲረዱ ሌሎችንም ሁኔታዎችን ለማወቅ ፍላጎት ይኖራቸዋል Stahi (1994) ስለዚህ የተፈለገውን የባህሪ ለውጥ ይመጣ ዘንድ የማህበራዊ ክሂሎት ትምህርት እንዲሰጥ እንደማንኛውም የትምህርት ዓይነት በተለየ ዘዴ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

**በትብብር መማር ለመምህራንም የሚሰጠዉ ጥቅም አለዉ፡-** በትብብር መማር ወቅት መምህራን እና ተማሪዎች ክሂሎታቸውን ለመገምገም የቡድኑ አስተዋፅኦ ለመፈተሽ ሀላፊነት ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች በቡድን ስራ ላይ እያሉ የትምህርቱን የአካዳሚክ እና ማህበራዊ አቅጣጫዎችን በተመለከተ በቡድን እንዴት እንደሚሰሩ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን መረጃ መሰብሰብና መለዋወጥ ይኖርባቸዋል ከቡድኑ ጋር መለዋወጥ የሚያካሂደው በትምህርት ክፍለ ጊዜና በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡ በተወሰነ የትምህርት ይዘት ላይ ተማሪው

ስላለው ችሎታና ስሜት የማወቅ ፍላጎት ላላቸው መምህራን የቀጥታ ምርመራ ለማድረግ ጠቃሚ መሳሪያ ነው Isacs (2008)፡፡

## 2.8 **በትብብር መማር መሰረታዊ መርሆች**

እንደ ምሁራን አገላለጽ በትብብር የመማር ስኬት የተማሪዎቹ በቡድን ተከፍሎ መቀመጥ ብቻዉን በቂ የሚሆንበት ሳይሆን አምስቱን የትብብር መማር መርሆች መኖራቸዉንና እነሱም ሲተገበሩ ነዉ፤ እነሱም አዎንታዊ ግንኙነት (Positive Interdependence)፣ የቡድን አባል ተጠያቂነት (Indivdual Group accountability) ፊት ለፊት ሃሳብ መለዋወጥ (Face to Face interaction) ማህበራዊ ክሂሎት (Approprate use of Social skill) እና የቡድን ስራ ሂደት መገምገም (Group processing) የተባሉትን ተማሪዎቹ ሥርዓት ባለው መንገድ በወጉ ሲተገብሩ መሆኑን Slavian (1996)፣ Johnson & Johnson(1999)፣ (2009) የገለጹትን አለማየሁ (2009) Gillies & Ashman (2003) ይስማማሉ፡፡ መርሆቹም እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ተብራርተዋል፡፡

**1.አዎንታዊ ግንኙነት** (Positive Interdependence)፡- ይህ የመጀመሪያና ዋናው የትብብር መማር መርህ ሲሆን ተማሪዎች በተቧደኑበት ቡድን በሚማሩበት ይዘት ላይ ያላቸው አመኔታ በጋራ በመሆን እርስ በርስ በመደጋገፍ በመረዳዳት፣ የድርሻቸውን በመወጣት፣ ያላወቁትን ነገር በግላቸው ጥረት በማወቅ ያገኙትን እውቀትና ክሂሎት ለሌሎች በማካፈል ጥሩ ውጤት የሚያመጡበት ነው መምህሩም ከክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ከየቡድኖቹ የሚሰጠውን ተግባር ላይ የአዎንታዊ ግንኙነት መርህ የሆነውን "አብሮ መስራት ወይም ማንበብናማዳመጥን" የሚለው አመለካከት ተማሪዎች ከውስጣቸው አስርፀው እንዲሰሩ ማድረግ አለበት፡፡ Johnson & Johnson (1999)፣ (2009) ይህ ማለት እያንዳንዱ የቡድን አባላት ለሚማሩት ትምህርት የጋራ የሆነ ጥሩ ውጤት ማምጣት ወይም ደግሞ መውደቅ ነው፡፡ የአንድ ተማሪ ማወቅ ወይም ውጤታማ መሆን ለሌሎች ቡድን አባላት እንደ ማወቅ ወይም ውጤታማ እንደመሆን ይቆጠራል ውድቀታቸውም እንደዚያዉ የጋራ ነው፡፡ በቡድን የተዋቀሩ ተማሪዎች ሁለት ሀላፊነት አለባቸው፡፡ የመጀመሪያው በዕለቱ የቀረበው የትምህርት ይዘት መረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሌሎች የቡድን አባላት እነሱ የተረዱትን ያህል እንዲረዱ ማድረግና ማረጋገጥ ነዉ፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው Gillis and Asheman (2003) እንደገለፁት በትብብር መማር ውስጥ ያሉት የቡድን አባላት ድርሻቸውን መወጣት ብቻ

ሳይሆን ሌሎች የቡድን አባላት  መስራት እንዲችሉ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አስደሳችናሳቢ ይሆንላቸዋል፡፡

በዚህ መልኩ የተማሩት ትምህርቱም ይገባቸዋል፡፡ የማወቅ አቅማቸውንም በማሳደግ የቡድን አባላቱ ከሌሎች ተባብሮ የመስራት እርስ በርስ የመደጋገፍ ክሂሎታቸውን ያዳብርሉ፡፡

2. **የቡድን አባል ተጠያቂነት** (Indivdual Group accountability)፡- የቡድን አባላት ተጠያቂነት ማለት እያንዳንዱ የቡድን አባል ሌላው በሚሰራው ሥራ ላይ ሳይተማመን የየራሳቸውን ድርሻ በማከናወን፣ ሌሎች የቡድን አባላት ድርሻቸውን እንዲወጡ በማድረግ ሀላፊነታቸውን መወጣት የሚያመለክት ነው Jolifk (2007) ይህን አስመልክቶ አለማየሁ (2009) እንደተናገሩት እያንዳንዱ የቡድን አባል በአባልነታቸው ያለውን ሀላፊነት አምነው የራሳቸውን የስራ ድርሻ በመወጣት ሌሎች አባላት ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለቡድኑ ውጤታማ መሆን ወይም መውደቅ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተጠያቂ ናቸው ሲገመገሙ የአጠቃላይ የቡድኑን ውጤት ለመስጠት በግል ይገመገማሉ፡፡ የቡድኑ አባላት ትምህርታቸውን በተሳትፎ መስራታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ መረጋገጥ አለበት፡፡ በቡድኑ ትክክለኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ ተማሪዎች የስራ ሚና በጥቂቶች ላይ ታምኖ ሌሎች ነፃ የሚሆኑበት አጋጣሚ አይኖረዉም ለቡድኑ ስራ ስኬት ሁሉም በተሳትፎ እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል ብለዋል፡፡

በትብብር መማር ወቅት የቡድንና የግለሰብ ሀላፊነት አፅኖት ሊሰጠው ይገባል Slavian (1996) እንደገለፁት፡፡ የቡድኑ አባላት ለጋራ አላማቸው የጋራ ጥረት ማድረግ አለባቸው ለቡድኑ ውጤት የሚሰጠው እያንዳንዱ ተማሪ ስራ ከተገመገመ በኃላ ነው በመጨረሻም ተጨማሪ እርዳታ የሚፈልግ ካለ ሊያውቅ ይችላል፡፡ በትብብር መማር ወቅት እያንዳንዱ የቡድን አባል መሳተፍን ለማወቅ መምህሩ ቀደም ብሎ የሰጣቸውን ተግባር መልሰው እንዲሰሩ በማድረግ በግል ይገመግማቸዋል ተማሪዎችም የግል ክትትል እንዳለ ካወቁ የበለጠ ጥረት በማድረግ ስራዎችን እንዲሰሩ ያደርጋቿል፡፡ Johnson & Johnson (1999) እንደገለፁት የቡድኑና የአባል ተጠያቂነት የማወቂያ መንገድ አንዱ ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ ያሉትን ሌሎች ተማሪዎች እንዲያግዙ በማድረግ ነው ብለዋል፡፡

3. ***ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ*** (Face to Face interaction)፡- *ፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ* ተማሪዎች በመቀራረብ እውነተኛን ሥራ አብረው በተነሳሽነት አንዱ የአንዱን የመማር

ሁኔታ ከፍ በማድረግ በመረዳዳትና በመደጋገፍ እንዲሁም በመበረታታት እንዲማሩ የማድረግ ስራ ነው Johnson & Johnson (1999)

በዚህ መርህ በቡድን መካከል አዎንታዊ መደጋገፍ ካለ መወያየት ይኖራል፡፡ በውይይቱ ጊዜ ተቀራርቦ የጋራ ስራን ለማከናወን እያንዳንዱ የቡድን አባል የራሱን እውቀት ተሞክሮ ክሂሎትን በግልጽነት ስለሚያካፍል የርስ በርስ የመደማመጥና የመቻቻል ተግባቦታቸው ይዳብራል፡፡ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ሲሉ የተሰጣቸውን የቤት ስራም ሆነ ሌላ ተግባር በጋራ ለመስራት በየጊዜው እየተገናኙ መወያየት ስለሚጠበቅባቸው በጋራ መስራት እንደ ግዴታ ወስደው ተነጋግረው ስራቸውን ያከናውናሉ፡፡ በየጊዜው በመገናኘት በሰሩ ቁጥር በመካከላቸው ያለው መስተጋብር ይጠነክራል፡፡

4. **ማህበራዊ ክሂሎታቸውን በአግባቡ መጠቀም መቻል** (Approprate use of Social skill)፡-

ይህ ሌላኛው የትብብር መማር መሰረታዊ ነገር ሲሆን ተማሪዎች በትብብር መማር ክፍል ውስጥ አብረው በሚሰሩበት ሰዓት ከሚማሩት ትምህርት እውቀት በተጨማሪ የራሳቸውን እና የቡድናቸውን ማህበራዊ ክህሎት ሊያሳድጉ ይችላሉ ክሂሎቶቻቸውን የሚያሳድጉት የቡድናቸውንና የራሳቸውን የጋራ ዓላማ ለማሳካት እርስ በርሳቸው ተገናኝተው በመደጋገፍና በመረዳዳት በሚሰሩበት ወቅት ነው፡፡ ከሌላ የቡድን አባላት ጋርም ሆነ ከራሳቸው ቡድን ጋር ያዳበሩትን እውቀት በሚሰጣቸውና ስራ ላይ እንዳስፈላጊነቱ የመጠቀም ልምዳቸው ያዳብርላቸዋል፡፡ ስራቸውን ተባብረው ያከናውኑ ዘንድ ከአባላቱ የሚጠበቀውን ይወጣሉ፡፡ Gillis & Asheman (2003) እንደገለጹት እርስ በርስ መተዋወቅ መፈላለግ መደጋገፍና በግል ተግባብቶ መስራት ብቻ ሳይሆን ተወያይቶ ችግሮችን መፍታትም የሌሎች ሀሳብ መቀበል የራስን አስተያየት መስጠትና አለመግባባቶችን በጋራ መፍታት ይጠበቅባቸዋል፡፡ Johnson & Johnson (2009) እንዳስቀመጡት በትብብር መማር ተማሪዎችን በህብረት እንዲሰሩ የመሳብ ሀይል ያለው ስልት ነው፡፡ ተማሪዎች አብረው በሚሰሩበት ወቅት አመራርነትን መምራትን፣ ውሳኔ መስጠትን የንግግር ክሂሎትን ማወቅና ግጭቶች ሲፈጠሩ በዉይይት መፍታት እንዳለባቸው ማወቅን ይማሩበታል ይህ ደግሞ ቡድኑ ለረጅም ጊዜ በስኬት አብሮ እንዲቆይ ያደርገዋል በማለት አብራርተዋል፡፡

5. **ቡድናዊ ሂደት** (Group processing)፡- በተወሰኑ ጊዜያት የቡድን አባላት የቡድኑን የመማር ሂደት ቆም ብለው በመገምገም ጥንካሬና ድክመታቸውን መለየት፣ ከድክመታቸው

እየተማሩ ቀጣይ የቡድኑ መማር ሂደታቸውን ማሻሻል የሚችሉበት ነው፡፡ ይህንን አስመልክተው አለማየሁ (2009፤4041) እንደገለጹት የቡድን መማር ውጤት የተሳካ እንደሆነ የቡድኑ አባላት በቋሚነት ቡድናቸው እንዴት እንደሚማሩ ውጤትና መጠን በዝርዝር መመዘን አለበት፡፡ እንዲሁም ዓለማየው የቡድን ስራዉን ለማሳካት ቀጥሎ ምን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ለይተው ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ የግምገማ ሂደት ውስጥ አባላት ለመማሩ ያደረጉት አስተዋጽኦ ይገመገማል፣ በግልጽም ይንፀባረቃል ይህ ደግሞ አባላቱ እንዴት ይሰሩ እንደነበር ለመረዳት እድል ይሰጣል፡፡ በቡድን ተዋቅረው ሲሰሩ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች በየግዜው እያሻሻሉ እንዲሄዱ ማሻሻያ ዘዴዎችን እያቀያየሩ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም Johnson & Johnson (2009) የሰጧቸው መፍትሄዎች

- በመካከላቸው የመስተጋብር ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ
- በቡድን ስራቸው እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ማረጋገጥ ውጤታቸው ይሻሻል ዘንድ ሁልጊዜ ክትትል ማድረግና በክፍል ውስጥ መሳተፋቸውን ማረጋገጥ
- አንድ የቡድን ስራ ለማከናወን ሰዓት መወሰንና የወሰደውን ሰዓት ማወቅ
- ከስራ በኋላ እንዲያቀርቡ እድል መስጠት

የትብብር መማር ቡድን መምህራን ተማሪዎችን በልማዳዊ የማስተማሪያ ዘዴ አቧድነው ከሚያስቀምጡ በተለየ መልኩ ትልቅ ትኩረት የሚሻ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፤ ተማሪዎች በቡድን በቡድን አድርጎ ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ከላይ በተብራራዉ መሰረት መምህራን ለተማሪዎች ግልፅ በሆነ መንገድ በመናገር እንዲተገብሩት የተለያዩ ድርጊቶችን ማድረጋቸዉን መከታተል አለባቸው፡፡

ተማሪዎችም የቡድናቸውንና የራሳቸውን መማር ሁኔታ ከፍ ለማድረግ እርስ በርስ በመደጋገፍ ለሚሰጣቸው ተግባር እራሳቸውንና ሌሎችን የቡድን አባላት መሳተፋቸውን በማረጋገጥ ሀላፊነታቸውን መወጣት መምህራንም በትብብር መማር ወቅት ሁሉም ሳይሆን ከቀረ ግን የትብብር መማር መርህ በሚገባ ሁኔታ የተተገበረ ሊባል አይችልምና ጥንቃቄ ሊደረግለት እንደሚገባ ነዉ፡፡

## 2.9 በትብብር መማርና በተለመደዉ መማር(ገለጻ) መካከል ያለዉ ልዩነት

በትብብር መማሪና በተለመደዉ መማር መካከል በርካታ ልዩነቶች መኖራቸዉን ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ከነዚህም የተወሰኑትን ለመጥቀስ አብዛኛዉን ጊዜ ትኩረት የሚያደርገዉ

እዉቀት ከአንድ አቅጣጫ በማስተላለፍ(ተማሪዉ ከመምህሩ ብቻ የሚጠብቅበት) ሲሆን የዚህ ዘዴ ትምህርት የመምህሩ ሚና የበላይነት ጎልቶ የሚተገበርበት በገለጻ የሚከናወን ሂደት ነዉ፡፡ የክፍል ዉስጥ መማር ማስተማር ትግበራ የሚከናወኑት በግላዊና ዉድድራዊ ሂደትን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

የትብብራዊ መማር ግን ትኩረቱ እዉቀትን በማሸጋገር ላይ የተመሰረተ ሲሆን የመምህሩ ሚና የበላይነት ጎልቶ የማይታይበት፣ መምህሩ የክፍል ዉስጥ የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን የሚያመቻችበት ራሱን ልክ ከተማሪ ጋር የሚሳተፍ አደርጎ ተማሪዎች ያለፍርሀት በነጻነት እንዲማሩ እንዲወያዩ የሚደረግበት ሁኔታ ያለዉ ነዉ፡፡ kagan(2000) አብዛኛዉ የክፍል ዉስጥ ተግባራት በተማሪዎች የሚከናወን ሆኖ በዚህም ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ በመሆን በየንኡስ ቡድናቸዉ በመሆን የሚሰጣቸዉን ተግባራት ያከናዉናሉ፡፡

## 2.10 የትብብር መማር ስልቶች

አብዛኛዎቹ ምሁራን የትብብር መማር ስልትን በተለያዩ መንገዶች ዘርዝረው ያስቀምጡዋቸዋል፡፡ ከነዚህም የተወሰኑት እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡ Jacobs and Hannah (2004)

1. **የጅግሳው ስልት**(Ji gsaw Method);- ስልቱ በስራ ክፍፍል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እያንዳንዱ የቡድን አባል በግላቸው የተወሰነ የትምህርት ይዘትን /ጥያቄን/ ሰርተው እንዲያመጡ ከተደረገ በኋላ ሌሎች አባላትን ያስረዳሉ፡፡ ሁሉም የየራሳቸውን ካስረዱ በኋላ በዋና ዋና ነጥቦች ላይ ተወያይተው በመጨረሻ ለአጠቃላይ ክፍሉ የመረጡትን የቡድን አባል ስራቸውን እንዲያቀርብላቸው ያደርጋሉ፡፡ በጅግሳው ስልት ትምህርት የማቅረብ አላማ በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ የትብብር መማር ክሂሎትን ለማስረጽ ነው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ጠቅለል ያለ እውቀት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ በቡድን ስራ ወቅት የድርሻቸውን በመወጣት ኃላፊነት እንዳለባቸው እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡

2. **የጥንድ ውይይት** (Think pair-share)፡- ይህ ዘዴ በአብዛኛው በሰፊ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚተገበር ሲሆን አራት ደረጃዎችም አሉት፡፡ የመጀመሪያው መምህሩ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ጥያቄዎችን ያቀርባል፣ ሁለተኛው ተማሪዎች እውቀትን የሚያዋቅሩት ከጓደኞቻቸው /ከአቻቸው/ እና ከመምህራን ጋር በመተባበር ነው፡፡ በጥንድ ስራ ላይ መምህሩ ያለማቋረጥ ስራዎችን ይቆጣጠራል፡፡ ጥንዱም ለሰራው ስራ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ወደ ሌላ ርእስ ከመሄዳቸው በፊት ምላሽ መስጠትና ስለተማሪዎች ባህሪ በመወያየት የተግባር ስራን እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡ ጥያቄ ላይ በራሳቸው እንዲያስቡበት ይደረጋል፣

ሦስተኛው ተማሪዎቹ በሀሳቡ ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲነጋገሩበት ይደረጋል፣ አራተኛው መምህሩ የተማሪዎችን ስም በመጥራት ሀሳባቸውን ለሌሎች የቡድን አባላት እንዲያካፍሉ ያደርጋል Stahal(1994) ፡፡

3. **ቁጥርን ሰጥቶ ራስን አንድ ላይ በማድረግ የማስተማሪያ ስልት** (Number Heads Together)፡- አራት አባላት ያሉትን ቡድን በመመስረት ለእያንዳንዱ አባል ከአንድ እስከ አራት ቁጥር ይሰጣል፡፡ ጥያቄዎቹም ለቡድኖቹ በማቅረብ ሁሉም አባል መልሱን ማወቁን ለማረጋገጥ ራሳቸውን አንድ ላይ እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ፡፡ መምህሩም አንድ ቁጥር

በመጥራት ቁጥሩ ያላቸው ተማሪዎች እጃቸውን እንዲያወጡ ወይም መልስ ለመመለስ እንዲቆሙ ይደረጋል፡፡ ይህ ተግባር በጣም ገንቢ የሆነ እርስ በእርስ የመተማመንን ሁኔታ እንዲረጋገጥ የሚያደርግ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በትክክለኛው መልስ ላይ መስማማታቸውን ለማረጋገጥ ጭንቅላታቸውን አንድ ላይ ስለሚያደርጉ ነው፡፡ እንዲሁም ሁሉም የቡድን አባላት መልሱን ማወቃቸውን ከማረጋገጥም በላይ ስማቸው እንዲጠራ በተለየ ሁኔታ ይጠባበቃሉ፡፡

4. **የዙር ውድድር**(Round way)፡- በመጀመሪያ በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ ማነቃቂያ ጥያቄ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎቹ ያላቸውን ሀሳብ እንደ ወረደ ይናገራሉ፣ ነገር ግን ያመነጩትን ሀሳብ አያብራሩም፣ ጥያቄ አይጠይቁም፡፡ የሚሰጡት መልስ በቃል ወይም በሀረግ መልክ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም የራሱን ከተናገረ በኋላ ወደ ተዘረዘሩት ሀሳቦች በመመለስ የቡድን አባላት ተራ ይወስዱና እያንዳንዱን ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ ነገር ምን እንደሆነ አጭር መልስ እንዲሰጧቸው ይጠይቃሉ፡፡ አካሄዱ አንድ ተማሪ ከተጠየቀ በኋላ ሁሉም የቡድን አባል የመናገር ወይም የመጠየቅ እድሉን እስኪያገኝ ድርስ ይቀጥላል፡፡ ብዙ ሀሳብ ለማመንጨት ያበረታታል፡፡ ምክንያቱም በዚሁ ስልት ማንም ለማንም ሂስ፣ አስተያየት ሊሰጥ አይችልም፡፡ ሁሉም የመጣለትን እንዲናገር እድል ተሰጥቶታል፡፡ በዚሁ አይነት ስልት በአንድ በተሰጠ ርእስ ላይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች ጥሩ ለመስራት ይሞክራሉ፡፡

5. **የቡድን ጨዋታ** (Buzzi groups)፡- በዚህ ስልት ቡድን በፍጥነት በተመሳሳይ ሰዓት ይመሰረትና የተለያዩ ወይም አንድ አይነት ጥያቄ በመስጠት የቡድን አባላቱ ሀሳቡን እንዲለዋወጡ እድል መስጠት ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የሚያገለግለው አጠቃላይ የክፍሉ ተማሪ ለማነቃቃት ሲሆን ጥሩ ሀሳብ በማመንጨት የተስተካከለ ስልት ነው፡፡

6. **የቡድን የጥንድና የተናጠል ስልት፡-** (Team paire solo) (TPS) ይህ ዘዴም kagan(2000) የተገኘ ሲሆን አተገባበሩም ተማሪዎችን በአንድ ክፍለ ጊዜ ሶስት ደረጃዎችን ተግባራትን ተጠቅመዉ የማስተማር ስልት መሆኑን ይገልጻል፡፡ ደረጃዎቹም በቡድን፣ በጥንድናበተናጠል (ግላዊ)ስልት የሚያሰራ ትብብራዊ መማር ዘዴ ነዉ፡፡ ተማሪዎቹ የሚሰጣቸዉን ስራ በትግበራዉ በጋራ በመስራት፣ በመረዳዳት በመወያየትና ያለ ፍርሀት ሁሉም ለጋራ ጥቅምና ግብ የሚሰሩበት ዘዴ ነዉ፡፡ kagan(2000) በዚህ ስልት ጥሎ ማለፍ የለም ስኬትም በጋራ፣ ዉድቀትም ቢሆን በጋራ በመሆኑ ማንኛዉም ስራ በጋራ በተነሳሽነት ለጋራ አላማ የሚሰሩት ይሆናል፡፡ ይህን ዘዴ ለመተግበር አካሄዱ መምህሩ አስቀድሞ ግልጽ

አላማ መያዝና ማቀድ፣ ለተማሪዎቹ በትብብራዊ ቡድን አመሰራረትና ትግበራ ዙሪያ እንድሁም አስፈላጊነቱንና ጥቅሙን በደንብ ግልጽ አደርገዉ ተማርዎቹን ማስረዳት የጋራ አቋም መያዝ ይገባል፡፡ በመቀጠል በሚከተለዉ ሁኔታ ሶስት ደረጃዎች እንዳሉትና ይህንንም በትክክል እንዲተገበሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ያስጀምራል፡፡

**ሀ. የቡድናዊ ትግበራ፡-** በዚህ የዘዴዉ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች የሚሰጣቸዉን ስራና ርእስ በጋራ ሁሉንም እኩል በማሳተፍ ይሰሩታል ያነቡታል፡፡ በዚህ ደረጃ ተመልካች አይኖርም ግልጽ ያልሆነለት ሰዉ ሳይታለፍ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ስራ አስቀድሞ ቡድን ሲመሰረት አራት ወይም ስድስት ሆነዉ መመስረት /መዋቀር/ አለባቸዉ፡፡ ምክንያት ዘዴዉ ሶስቴ ስለሚከፍላቸዉ በሁለተኛዉ ደረጃ በጥንድ በመሆን መስራት የግድ ስለሚሆን በሶስተኛዉ ሁለቱም ይነጠሉና ስራዉ በተናጠል(ግላዊ) ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በቡድናቸዉም ለሁሉም ግልጽ እስከሚሆን የተሰጣቸዉን ይሰሩታል፡፡ በዚህ ስልት ሲያነቡ በየቡድኑ በጮክታ ሲነበብ ሁሉም ይከታተላሉ፣ ሲሀተት ሲፈጠር ይተራረማሉ፣ በተራ ስድስቱም እንደቻሉ ለማወቅ እንዲያነቡ ይደረጋል፡፡

**ለ. የጥንዳዊ ትግበራ፡-** በዚህ ደረጃ ቡድኑ በሁለት ሁለት ይከፈልና ቀደም ሲል በጋራ የሰሩትን ግልጽ ስለመሆኑ ዳግም ሰርተዉ በሁለትዮሽ ይገማገሙበታል፡፡ በዚህም እያንዳንዱ ጥንድ ያለበትን የማንበብ ደረጃ በማየት ግልጽ መሆኑን በማረጋገጥ ስራዉን ለክፍሉ ለማቅረብ ዝግጅት የሚደረግበት ነዉ፡፡

**ሐ. ተናጠላዊ(ግላዊ) ተግባር፡-** በዚህ ትብብራዊ ሞዴል ደረጃ ጥንዶች ተለይተዉ ቀደም ሲል በቡድን ቀጥለዉ በሁለትዮሽ የተሰራዉ ስራ ወይም ንባብ ግልጽ ስለመሆኑ በግል ራስን የመገምገሚያ ደረጃ ይሆናል፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ ሁሉም አስቀድመዉ በተነሳሽነት በቡድንና በጥንድ በተሰራዉ ስራ የተዘጋጁበትን ተጠይቀዉ ግላዊ ብቃት ለክፍሉ ሊያቀርቡ ስለሚችሉ በጥንቃቄ በተሻለ እድሰሩና እንድዘጋጁ የሚደረግበት ደረጃ ነዉ፡፡ ይህን ስራ በመምህራቸዉ ጋባጅነት ለክፍሉ ማቅረብ ሲለሚኖር ሁሉም ዝግጁ በመሆን ይጠባበቃሉ፡፡

በዚህ አይነት ተማሪዎች በትብብር ዘዴዉ በመማር በሂደቱም በዚኛዉ ክፍል ሶስቱን ደረጃዎች በመከወን የበለጠ ዉጤታማ እንደሚሆኑ ስለሚያደርጋቸዉ ስልቱ የማንበብ ክሂሎትን ለማሻሻል የሚኖረዉን ለዉጥ ለማየት በዚህ ጥናት ይህ ሞዴል ለሙከራ ቀርቧል፡፡

## 2.11 በትብብር መማር ሂደት የመምህራን ሚና

በትብብር መማር ወቅት የመምህራን ሚና ከልማዳዊ የቡድን ማስተማር (Traditional group Teaching) ከሚኖረው ሚና የተለየ ነው፡፡ በትብብር መማር ወቅት የመምህራን ሚናቸው ብቸኛ የእውቀት ምንጭ በመሆን እውቀትን ለተማሪው ማስተላለፍ ሳይሆን ተማሪዎቹ በራሳቸው ጥረት እውቀታቸውን በመምህሩ የሚያዳብሩበት ሁኔታ መፍጠር ማመቻቸት ነው አለማየሁ (2009፣21) እንደሚገልፁት ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርቱን በግልፅ ከማቅረብ ባሻገር ተማሪዎች በበርካታ ተግባራት እንዲሳተፉ በመምህሩ ታቅዶ የሚተገበር ዘዴ ነው፡፡

ይህ የሚያመለክተው ተማሪ ተኮር አቀራረብ መምህሩ ብቸኛ የእውቀት ምንጭ ነኝ ከሚል ሀሳብ በመላቀቅ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት በመምህሩ ታቅዶ በተዘጋጀው ትምህርት በመመራት በጥረታቸዉ እንዲማሩ፣ እንዲሰሩ የሚያደረግ መሆኑን ነው የትብብር ዘዴዉ ከዚህ አንጻር ሲተገበር የመምህሩም ተግባር ተማሪዎች በምን አይነት መንገድ መማር እንዳለባቸው አቅጣጫ በመጠቆም ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር ጉሊህ ሚና አላቸዉ፡፡

ከተማሪ ተኮር አቀራረብ አንዱ የሆነው ትብብራዊ መማርን የመምህሩ ሚና ለተማሪዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ትምህርታቸውን እንዲማሩ ማድረግ ነው፡፡ በሂደቱም ላይ ተማሪዎቹ ትርጉም ያለው ስራ እንዲሰሩ መምህሩ ተግባሩን በጥንቃቄ በመንደፍ እና ግልፅ በሆነ ሁኔታ ማስቀመጥ ለተማሪዎች ማስረዳት አለበት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በስራው ላይ ተግባር እንዲሳካ ለማመቻቸት እና የመማር ሁኔታን ለመቆጣጠር ከቡድን ቡድን እየተዘዋወረ ማየት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም መምህሩ ለተማሪዎች የተለያዩ ግብረ መልስ እየሰጠ የቡድኑን ተግባር ይፈትሻል (ይመዝናል) ይህ ደግሞ የቡድን አባላት ወደ ጋራ አላማቸው ለማምራት ትምህርታቸውን በንቃት እንድማሩ ያደርጋቸዋል Ogunleye (2011)

## 2.12 በትብብር መማር ወቅት የተማሪዎች ሚና

በትምህርት አለም የሚገኙ አብዛኞቹ መምህራን ስለ ቡድን ስራ ያላቸው አመለካከት እየተቀየረ መጥቷል፡፡ ተማሪዎችን ዝም ብለው የቡድን ስራ /ፕሮጀክት /እንዲሰሩ ከማድረግ ይልቅ መምህሩ እያንዳንዱን ተማሪ በራሱ ሚና እንዲወጣ ሚናዎችን ከፋፍሎ እስከ መስጠት ደርሷል፡፡ የቡድኑ ተማሪዎች ግባቸውን ለማሳካት ሲሉ በህብረት ሆነው አብረው ይሰራሉ ከዚህ በመነሳት የትምህርት ቃሉም በትብብር መማር እየተባለ ይጠራል፡፡ አለማየሁ

(2009፣89-70)ን ዋቢ በማድረግ ዘነበች(2010) እንዳብራሩት በትብብር መማር ቡድን ውስጥ የተማሪዎችን ሚናን በተመለከተ የቡድኑ አባላት ከሌሎች ሚናዎች በተጨማሪ የስራ ክፍፍል ማድረግ እንዳለባቸው ተገልጸዋል፡፡ ዓለማየሁ (2009፣89-70) በትብብራዊ መማር ቡድን ውስጥ የተማሪዎችን ሚና በተመለከተ የቡድን አባላት ከሌሎች ሚናዎች በተጨማሪ የስራ ክፍፍል ማድረግ እንዳለባቸው አስቀምጠዋል በዚህም መሠረት ሚና መከፋፈል አስፈላጊ ነው፡፡ የስራ ክፍፍል ዝርዝሩም የቡድን መሪ፣ ዘጋቢ፣ ተመልካችና ተቆጣጣሪ የሚባሉት ናቸው ብለዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የተሻለ የስራ ዝርዝር ካለ መጨመር እንደሚቻል እና ሚናዉ ያልተገደበ መሆኑን ምሁራኑ ገልፀዋል ዋና ዋናዎቹ ግን በቅደም ተከተል እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

**የቡድን መሪ፡-** ይህ ሰዉ ለቡድኑ ውጤታማነት ሃላፊነት አለበት፣ የቡድኑ አባላት ከተግባራቸው እንዳይዘናጉና ዘወር እንዳይሉ ያደርጋል፣ ለመምህሩ ለቡድኑ አባላት እያወያየ ድርሻቸውን ያከፋፍላል፣ የሚሰሩት ስራ በትክክለኛ አቅጣጫ እየተጓዘ መሆኑን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተጨማሪ ተግባራት ለቡድኑ አባላት በመስጠት እንዲወጡ ያደርጋል፡፡

**ዘጋቢ፡** የቡድኑን የክፍለጊዘዉ ተግባራት አስመልክቶ ማስታወሻ ይወስዳል፣ የሰሩትን የስራ ውጤት ሌሎችን በማስተባበር ለመምህሩና ለክፍሉ ተማሪዎች ሊያቀርቡ የሚችሉበት መንገድ ያመቻቻል፡፡ ለዚህም ለስራው የሚሆነውን ፋይል በሚመለከት ሌሎች የቡድን አባላት የሚያቀርቡት ግብአት መሰረት በማድረግ ያዘጋጃል ይይዛል፡፡

**ተመልካች፡-** በተመልካችነት የተመረጠው ደግሞ ሁሉም የቡድን አባላት በእኩልነት መሳተፋቸውን፣ እኩል የመናገር እድል መኖሩን ጥቂቶች አስተዋፅኦ አድርገው የተቀሩት አድማጭ ብቻ እንዳይሆኑ ተሳትፎአቸው ከፍ እንዲል በአዎንታዊ መንገድ ያነቃቃል በቡድን አባላት መካከል የሚደረጉ ተግባቦቶች ከንትርክ የፀዳና አንዱ በሌላው ላይ የሚያቀርበው አስተያየት አዎንታዊ መሆኑን ያረጋግጣል ይደግፋል፡፡

**ተቆጣጣሪ፡-** የቡድኑ አባላት ሁሉም በንቃት መሳተፋቸውን፣ ለመማር መትጋታቸው የተማሩትን ትምህርት በሚገባ መረዳታቸውን ያረጋግጣል አለማየሁ (2009፣69) ከገለፁት በተጨማሪ (Johonson Et al 1991) በትብብር መማር ወቅት የተማሪዎች ኃላፊነት ብለው ካስቀመጡት እንደሚከተለው የቀረቡት አሉበት፡፡

**ማጠቃለያ ሰጪ፡-** ከቡድኑ ስራ የተገኙት መፍትሄዎችን መደምደሚያ ወይም የመግባቢያ መልሶች በአጭር በአጭሩ ተጽፈው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

**አብራሪ፡-** ለውይይት የቀረቡ ፅንሰ ሀሳቦችን ከቀደመ እውቀት ጋር ተዛምዶ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡ ሌሎች የተማሪ ሚናዎች አለማየሁ (2009፣68-69) እንደሚከተለው ይዘረዝሮታል፡፡

> "ተማሪዎች አዎንታዊ ግንኙነታቸው መደጋገፋቸውን ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል፣ ሁሉም ተማሪዎች በእኩልነት መሳተፋቸውን ማረጋገጥ የአንድ ሰው ወይም የቡድን ብቻ አድራጊ ፈጣሪ እንዳይሆን መከላከል የሌሎችን አስተዋጽኦ ማበረታታት ተነሳሽነት እንዲኖር ማድረግ ይኖርባቸዋል፣ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርቱን በሚገባ የተረዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋቸዋል፣ ሁሉም ተማሪዎች አለመጣመዳቸውን መቆጣጠር ግዴታቸው መሆን አለበት ለቡድን አባላት በሚሰማ መጠን ብቻ መናገር ከቡድን አባላቱ የሚወጣ ድምፅ ሌሎች ቡድኖችን እንዳይረብሽ መጠንቀቅ ይጠበቅባቸዋል" በማለት ምሁሩ ገልጸዉታል፡፡

## 2.13 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ ጥናቱን ከመጀመሩ በፊት ከርዕሱ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች ለመቃኘት ሞክሯል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የንባብን ክሂሎት ለማሻሻል የሚኖረዉ ሚና መመርመር ላይ ሲሆን ከዳሰሳቸው ጥናቶች መካከል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች ቃኝተዋል፡፡

ሀገር በቀል ካልሆኑ ጥናቶች Mustefa Polat(2011) በትብብራዊ መማር ስልት መጠቀም በንባብ ክሂል ላይ መሻሻልን በማምጣት ዉጤታማ ስለመሆኑ በጥናታቸዉ ሲያመለክቱ ይህንንም በስታንቡል ዩኒቨርሲቲ ባካሄዱት ጥናት የስፔን ቋንቋን እንደ ሁለተኛ የሚማሩ የእንግሊዘኛ 40 ተማሪዎችን በማሳተፍ 20ዎቹን በሙከራ 20ዎቹን በቁጥጥር ቡድን ከፍሎ በማስተማር በሙከራ ቡድኑ ላይ የተሻለ ዉጤት ማሳየቱን ያመላከቱ ሲሆን በጥናታቸዉ የጉልህነት ደረጃና ስፋት የገለጹበት ሁኔታ አለመኖሩን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

እንደዚሁም Aluiyamita Abadi(2012) ትብብራዊ መማር ስልትን በመከተል በማስተማር የኮሌጅ ተማሪዎችን የሁለተኛ ቋንቋ የንባብ ክህል ለማሻሻል በሚል ርእስ የተሰራ ጥናትን

በመዳሰስ ይህም ጥናት በከፊል ሙከራዊ ጥናት ችግሩን ያረጋገጠ እና እንድሁም ዘዴዉ የተማሪዎቹን የንባብ ችሎታና ፍላጎት ማሻሻሉን ያመላከተ ጥናት መሆኑ ተረጋግጠዋል፡፡ በዚህ ትብብራዊ ዘዴ ዉስጥ በተተገበረዉ ሞዴል (Team paire solo) ተማሪዎቹን በተዋቀሩት ትብብራዊ ቡድን መሰረት እያንዳንዱ ቡድን የሂደቱን ሶስት ደረጃዎች ተግባራትን በመጠቀም ንባብን የማንበብ ስራን ተግባራዊ በማድረግ የተሻለ ዉጤታማ መሆናቸዉን አጥኚዋ አረጋግጠዋል፡፡ ይህም ጥናት በዚህ ሞዴል መሰረት የተከናወነ ነዉ፡፡

በሌላ ሁኔታ ከሀገር ዉስጥ ጥናቶች ተስፋዬ ሸዋዬ(2001)፡፡ "የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመረጡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች"፡፡ በሚል ርእስ በአድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማስተርስ ድግሪ ማሚያነት ጥናት በማካሄድ የተጠኚዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ሆኖ መገኘቱን ያመላከተ ጥናት ነበር፡፡

ሌላዉ መኮንን ናና (2000) በአዊኛ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን በተመለከተ ባካሄዱት ጥናት የተጠኚዎቹ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በጥናታቸው ውጤት ላይ አመላክተዋል ፡፡

ዘነበች ቃሎሬ በደብረ-ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና (በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት) በሚል ርእስ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፋቸዉ ሙከራዊ የምርምር ስልትን በመተግበር ከመረጃ መተንተኛ አንጻር መጠናዊ ምርምርን ተጠቅመዉ ሁለት በማዘጋጀት አንዱን በቁጥጥር ሌላኛዉን በሙከራ በማስተማር ባረጋገጡት ግኝት መሰረት ትብብራዊዉ ስልቱ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ዘዴዉ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መረዳት ይቻላል፡

ጥናቱ በአካሄድ ከአላማ፣ ከጥናቱ ዘዴ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ልዩነታቸዉ የመጻፍ ክሂልና የማንበብ ክሂል መሆኑ፣ በቦታ እና ከደረጃም አንጻር ነዉ፡፡ ትብብራዊን ከመተግበር አኳያ ጥናታቸዉ ለዚህ ምርምር ጥናታዊ መዋቅር መሻሻል ጥሩ ግብአቶች የተገኙበት ጥናት በመሆኑ የሚደነቅ ስራ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ተዛማጅ ጥናቶቹን በሚመለከት በትብብራዊ ዘዴ የተካሄዱት ሀገር በቀል ያልሆኑ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር በአካሄድ፣ በመረጃ አሰባሰብና በትንተና ጭምር ተመሳሳይነት ሲኖራቸዉ የዉጤታማነት መገለጫ ከጉልህነት ደረጃ አንጻር ግልጽ አይደሉም፡፡ በሶስተኛ እና በአራተኛዉ የታዩት ጥናቶች በንባብ ክሂሎትና አንብቦ መረዳት ላይ የተካሄዱ በመሆኑ

ከክሂሎት ሁኔታ የሚመሳሰሉ ቢሆኑም ከትግበራ አንጻር በተለመደዉ(የገለጻ) ዘዴ ስለሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አላቸዉ፡፡ ይህንን ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች የሚያቀራርባቸዉ በማንበብ ክሂል ትምህርት ዙሪያ የተሰሩ መሆናቸዉን ነው፡፡ ይሁንና ሁሉም ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት የተጠቀሙበት ቦታ፣ ጊዜና የትኩረት አቅጣጫ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህም አንፃር ሲታይ ተስፋዬና የመኮንን በአንብቦ መረዳት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ናቸዉ፣ ሁለቱም ጥናታቸዉ ስለ ትግበራ ያነሱት ነገር ባለመኖሩ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አላቸዉ፡፡ ይህ ጥናት የንባብ ክሂሎት ችሎታ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ጥናቱ ትብብራዊ የመማር ዘዴን በመጠቀም የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ከማዳበር አንጻር የሚኖረዉን ሚና በከፊል ሙከራዊ ጥናት ይፈትሻል፡፡ በአጠቃላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ትኩረት ያደረጉበት በማንበብ ክሂሎት አካባቢ ችግሮችን በንባብ የማስተማር ስልትና ደረጃዎቹን በመተግበር ፈትሸዉ የመፍትሂ አቅጣጫዎችን ማቅረባቸዉ በጠንካራ ጎኑ የሚታይ ስራ ሲሆን ከአተገባበር አንጻር የነበረዉን ክፍተት ማየት ደግሞ የዚህ ጥናት ትኩረት ይሆናል፡፡ የዘነበች ጥናት ትኩረቱን ያደረገዉ በማስተማር ዘዴ ላይ በመሆኑ አካሄዱ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ጥናት አቅራቢዋ ትብብራዊ ዘዴን በሙከራ ጥናት ተግባራዊ በማድረግ ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂል ዉጤታማ መሆናቸዉን ማረጋገጣቸዉ ከዚህ ጥናት ጋር የተለየ ያደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ዘዴና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ክህሎት ለማዳበር የሚኖረዉን ሚና መመርመር ነዉ፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ተግባራዊ ያደረገዉ የምርምር ንድፍ ከፊል ሙከራዊ የምርምር ስልትን ሲሆን ከመረጃ መተንተኛ አንጻር ደግሞ መጠናዊ ምርምርን ተጠቅሟል፡፡ መጠናዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ በከፊል ሙከራዊ ንድፍ ሲካሄድ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎችን በስታቲስቲካዊ ዘዴ የሚያቀርብና መላምትን መሰረት ያደረገ መሆኑ ለዚህ ጥናት አጠቃላይ ሂደትና ስኬታማነት አመቺ ይሆናል ተብሎ በመታሰቡ ነዉ፡፡ የጥናቱ ዉጤትም መጠናዊ በሆነ መንገድ በቲ-ቴስት በማነፃፀር በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የተያዙ ሁለት ተጠኚ ቡድኖችም ቅድመ ልምምድ እና ድህረ ልምምድ ፈተና እና በተጨማሪ የጽሑፍ መጠይቅ ንድፍን ተግባራዊ በማድረግ የተከናወነ ጥናት ነዉ፡፡

## 3.2 የጥናቱ አካላይ

ጥናቱ የተካሄደዉ ከቦታ አንጻር በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በሲግሞ ወረዳ ነዉ፡፡ በወረዳዉ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፣ ከእነዚህም ትምህርት ቤቶች መካከል ጥናቱ የሲግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ነዉ ያተኮረዉ፡፡ በ2013 ዓመተ ምህረት በዚሁ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ያሉትን የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን መሰረት አደርጓል፡፡ ተማሪዎቹም 157 ሴቶችና 184 ወንዶች በድምሩ 341 ሲሆኑ በ11 የመማሪያ ክፍል ተመድበዉ የሚማሩና አንዱ መማሪያ ክፍል በአማካይ 31 ተማሪዎችን የያዘ ነዉ፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት የጥናቱን ተሳታፊዎች ለይተዉና ወስነዉ የችግሩን መፍትሄ ለመፈለግ ይቻል ዘንድ ከሚኖረዉ ጠቀሜታ አንጻር ሁሉንም ተጠኚ ተማሪዎች ማሳተፍ ከገንዘብ፣ ከጊዜና ከሰዉ አቅም አንጻር ስለሚከብድ ከጥናቱ ተተኳሪዎች በናሙናነት በመዉሰድ ጥናቱን ማካሄድ ተችሏል፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱን የናሙና አመራረጥ የትምህርት ቤት፣ የክፍል ደረጃና የተማሪዎች ኒሞና በሚከተለዉ ሁኔታ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

### 3.3.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

በዚህ ጥናት አስቀድመዉ በጥናቱ ወሰን ላይ እንደተገለፀው በወረዳዉ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቢኖሩም ሲግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ቤቱ ከሌሎቹ ከቦታና ከጥናቱ ጊዜ አንጻር አጥኚዉ ስለሚያስተምርበት ለጠጠኚዎች በቂ የመማሪያና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሁኔታዎችን ያሟላ በመሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ጥናቱን ለማሳካት አመቺ ስለሆነ ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡

### 3.3.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

የጥናቱ የክፍል ደረጃ የተመረጠዉ በአላማ ተኮር የናሞና ዘዴ ሲሆን ይህም የሆነዉ ከጥናቱ አላማ አንጻር ካሉት ክፍሎች 9ኞችን ከመምረጥ እነዚህ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ከመጡ የአንድ አመት ልምዱ ስላላቸዉ ጥሩ መረጃ ይገኝባቸዋል፣ እናም በጥናቱ ቢካተቱ የተሻለ መረጃ ይሰጣሉ ከሚል ሲሆን 11ኞች በክፍላቸዉ አነስ ያሉ ስለሆኑ፣ 12ኞች ለማትርክ ዝግጅት ስለሚጨናነቁ አጥኚዉ እነዚህን ሂኔታዎች ከግምት በማስገባት እና በዚህ የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎች ከሌሎች ከፍተኛ የክፍል ቁጥር ያላቸዉ በመሆኑ ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡

### 3.3.3 የተማሪዎች አመራረጥ

በዚህ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በ10ኛ ክፍል ተመዝግበው የሚማሩ ተማሪዎች በድምሩ 341 ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህም በ11 የመማሪያ ክፍሎች መመደባቸዉ ቀደም ሲል ተገልጸዋል፡፡ አንዱ የመማሪያ ክፍል 31 ተማሪዎችን በአማካይ የያዘ ነዉ፡፡ ለጥናቱ አስተማማኝነት እና ተገቢነት ሲባል የተማሪዎቹን ብዛት በመወሰን ጥናቱን ለማካሄድ በሁለት ክፍል የሚማሩ ተማሪዎችን ተጠኚ ለማድረግ በመማሪያ ክፍላቸዉ ዕጣ ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከነዚህም በቀላል ዕድል ሠጪ ናሙና ዘዴ(simple random sampling) በመምረጥ ከአስራ አንዱ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ሁለት ክፍሎችን 10ኛ D እና 10ኛ G ተመርጠዉ በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ጥናቱንም ለመጀመር የትኛው ክፍል ሙከራዊ የትኛው ደግሞ የቁጥጥር ምድብ ይሁን? የሚለውን ለመወሰን ሁለቱን ክፍሎች የማንበብ ችሎታ ለማወቅ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጣቸዉ፡፡ ዉጤቱንም በማረምና ደረጃቸዉን በመለየት ተቀራራቢ መሆናቸዉ ታዉቆ ዳግም በቀላል እጣ ናሙና ዘዴ አማካኝነት 10 D

የቁጥጥር ቡድን 10 G ደግሞ ሙከራዊ ቡድን ሆኑ፡፡ በዚህ ሁኔታ ቡድኖቹን የመለየት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀጣይ ለስድስት ሳምንታት፣ በሳምንት ሁለት ቀን፣ በቀን ለአርባ አምስት ደቂቃዎች ከ13/8/2013 እስከ 04/10/2013 ሙከራ ቡድኑ በትብብር መማር ዘዴና የቁጥጥሩ በተለመደዉ መማር ዘዴ ሥልጠና በወሰደዉና በሌላ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ይህም የጥናቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ነው፡፡ ቁጥጥር የሚደረግባቸውም ሆነ ሙከራዉ የሚደረግባቸው ሁለቱም ቡድኖች የተማሩት መጽሀፍ ተመሳሳይ የንባብ ክህል ትምህርት ይዘቶችን ለደረጃዉ ካለዉ መጽሐፍትና መርሀ ትምህርት ለጥናቱ እንዲመች ተደርጎ በአጥኚዉ የተዘጋጀ ከነፈተናዉ ስድስት ምንባቦችን አራቱን ከነመልመጃቸዉ ተምረዉታል፡፡

## 3.4 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት ውስጥ ዋና የጥናቱ ተተኳሪና የመረጃ ምንጮች ተደርገው የተወሰዱ የመረጃ ምንጮች በሲግሞ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በ10ኛ ክፍል ተመዝግበዉ በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸዉ፡፡

## 3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የማንባብ ክሂሎት ለማዳበር የሚኖረዉን ሚና መመርመር አጥኚው ይህን አላማ መሰረት በማድረግ የተጠቀመባቸዉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በአጠቃላይ ሁለት ናቸዉ፡፡ እነሱም ለተማሪዎች የቀረበዉ የአንብቦ መረዳት ቅድመና ድህረ  ፈተና ዋናዉ ክፍል ሲሆን በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያነት ደግሞ  የጽሁፍ መጠይቅ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 3.5.1 ፈተና

በዚህ ጥናት ፈተና ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ስለመሆኖ አስቀድሞ የተገለጸ ሲሆን የአንብቦ መረዳቱ ፈተና ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የንባብ ትምህርቶች መሰረት በማድረግ የጥናቱን ተሳታፊዎች የንባብ እዉቀትና ችሎታ ለመለካት ነው፤ በዚህም መሰረት የቅድመ ትምህርት ፈተናና የድህረ ትምህርት ፈተና ተዘጋጅተዉ ተጠኚዎቹ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ይህም ፈተና የተዘጋጀዉ ደረጃዉን ይመጥናል ተብለዉ በመርሃትምርቱ ከተዘጋጀዉ የ10ኛ ክፍል መጽሀፍ በወቅቱ ካልተማሩት እና በአጋዥነት ሊመጥኑ ከሚችሉ ጽሁፎች በባለሙያ በማስገምገም በአጋዥነት በማካተት ከተዘጋጀዉ ጽሁፍ የተወሰዱ ናቸዉ፡፡ ጥያቄዎቹ በምሁራን በሚመከረዉ ሁኔታ ከአግባብነት

አንጻር ሁሉም ምርጫ ሆነዉ የንባብ ጥያቄ አዘገጃጀት ሂደት እንዲከተሉ ተደርገዉ የተማሪዉን የአንብበዉ መረዳት ችሎታ ለመለካት በምንባቡ ዋና ዋና ሀሳቦችን፣ ዝርዝር ሀሳቦችን ለመለየት፣ ጥቂምታዎችን እና እንድሁም ትንበያን፣ የቃላትና ሀረጋትን ትርጉም ከመቻል አንጻር ለመለካት እንዲሆኑ ተደርገዉ የተዘጋጁ ናቸዉ፡፡

### 3.5.1.1 ቅድመ ልምምድ ፈተና (pre--test)

የዚህ ጥናት የቅድመ ትምህርት ፈተና ዋነኛዉ አስፈላጊነት እና አላማ ከትብብራዊ መማር ልምምድ በፊት በሙከራዊ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድን መካከል ያለውን የአንብቦ መረዳት እዉቀትና ችሎታ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ እና እንዲሁም በሙከራና ቁጥጥር ቡድኑ መካከል የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ከተዘጋጀዉ ምንባብ የወጡ የምንባቡን አጠቃላይ መልእክት እንዲለዩ፣ የምንባቡን ዋናና ዝርዝር ሀሳብ፣ በምንባቡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የቀረቡ እዉነታዎችን መገንዘባቸዉን መለየት የሚያስችል በአይነቱ ምርጫ ብቻ የሆነ እላይ በተገለጸዉ ሁኔታ የአንብቦ መረዳት ፈተና ከ30% የሚታረም ተዘጋጅተዉ ቡድኖቹ እንዲፈተኑ ቀርቦላቸዋል፡፡

### 3.5.1.2 ድህረ ትምህርት ፈተና (post--test)

ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ በጥናቱ የድህረ ትምህርት ፈተናዉ ዋነኛ አላማና አስፈላጊነት የሙከራ ቡድኑ በትብብራዊ ዘዴ አማካኝነት ከተማሩ በኋላ ዘዴው በሙከራው ቡድን ውስጥ በተካተቱ ተማሪዎች የንባብ ችሎታ ላይ ቀደም ሲል ከነበራቸዉ ሁኔታ አንጻር መሻሻል ማስከተሉን እና አለማስከተሉን በመመርመር ሚናዉን መለየት የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ ስለሆነም የተጠኚ ተማሪዎች የንባብ ክሂልን በተመለከተ የተዘጋጀውን የማስተማሪያ ጽሁፍ በትብብራዊ ማስተማር ትግበራ ለስድስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ቀን በየቀኑ ለአርባ አምስት ደቂቃዎች ተከታትለዉ ከተማሩ በኋላ ቀደም ሲል በተገለጸዉ ሁኔታ የድህረ ትምህርት ፈተናው ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ተዘጋጅተዉ ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ መምህራን እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ እንድሁም የድህረትምህርት ፈተናው እንዳላቸዉና መቼና እንዴት እንደሚፈተኑ እንዳያውቁ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከፈተናዉ አዘገጃጀትና አፈታተን አንጻር ተገቢዉ ጥንቃቄ በማድረግና እንዳይገናኙ የሚደረግበት ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የፈተናዎቹ ተገቢነትና አስተማማኝነት (Releability) ለመቆጣጠር ከአጥኚዉ ዉጪ ሌሎች መምህራንና

ሙያተኞች ፈተናዉን እንድያርሙት ተደርጓል፡፡ የጥያቄዎችን አዘገጃጀት፣ አቀራረብ፣ ግልጽነት፤ የሰዋሰዉና የቃላት ግድፈቶች ተገምግመዉ እንዲታረሙ ሆነዉ፣ ማስተካከያ መደረጉን በጋራ በማረጋገጥ ፈተናዉ እንዲቀርብላቸዉ ተደርጓል፡፡

## 3.5.2 የጽሁፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት የጽሑፍ መጠይቅ ሌላው በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የዋለ ሲሆን የመጠይቁ ዋና ዓላማም ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ከማሻሻል አንጻር ያላቸውን ግንዛቤ ለማየት ነዉ፡፡ ለዚህም የሚሆኑ መጠይቆች Brown(2008)፣ Aldreson (2005) እና አለማየሁ(2009) ያዘጋጁትን መሰረት ያደረገ ሆኖ ከይዘቱ አንጻር አካዳሚካል ጥቅሞችን፣ ማህበራዊ ጥቅሞችን፣ አጠቃላይ ክህሎቶችና እንዲሁም ስለትብብራዊ መማር አሉታዊና ተጨማሪ አስተያቶችን ያካተቱ በዓይነታቸው ዝግ ሆኖ ተዘጋጅተዉ አራት አራት አማራጭ መልሶች የያዙ ናቸዉ፡፡ ከነዚሁ ምላሽ ከሚሆኑት አማራጮች መካከል መላሹ ያመነበትን መርጠዉ መመለስ በሚችል ሁኔታ ተዘጋጅተዉ እንዲፈተኑት ሲደረግ የጥያቄዎቹም ብዛት 20 ናቸዉ፡፡ አማራጭ ምላሾቹም፡-

1.በጣም አልስማማም

2. አልስማማም

3. እስማማለሁ

4. በጣም እስማማለሁ

ሲሆኑ የጽሁፍ መጠይቁ ለተሳታፊ ተማሪዎች ከመቅረባቸዉ በፊት ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በሌሎች ባለሙያዎች ተገምግመዉ በአጥኚዉ አማካሪ አስተያየት ተጠይቀዉ ማስተካከያ ተደርገዉበታል፡፡ የተዘጋጁ ጥያቄዎች የተተኳሪ ተማሪዎቹ ስለ ትብብራዊ የመማር ዘዴ ያላቸውን ግንዛቤ ለመፈተሽ ሲሆን መጠይቁም ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ጋር አብሮ ለተሳታፊ ተማሪዎች እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የንባብ ክሂል ትምህርት ከመማራቸው በፊት በቅድመ ትምህርቱ ስለ ትብብራዊ መማር ዘዴ ያላቸውን ግንዛቤ ለመለካት የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ ሲሆን ይኸው የጽሑፍ መጠይቅ በድጋሚ ተማሪዎች ስለትብብራዊ የመማር ዘዴ ያላቸውን ግንዛቤ

ለመፈተሽ በጥናቱ የተዘጋጀውን ትምህርት ተምረዉ እንደ አጠናቀቁ ከድህረ ትምህርት ፈተናው ጋር አብረዉ ሙከራ ለተማሪዎች እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

## 3.6. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱ ዋና አላማ በጅማ ዞን በሲግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ክሂሎት ለማዳበር የሚኖረዉን ሚና መመርመር ነዉ፡፡ ለዚህም ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን መጠናዊ መረጃ መተንተኛ ዘዴን በመተግበር ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለትንተና በሚመች መልኩ በአግባቡ በማደራጀት፣ በማቀናጀትና በማጣራት ተዘጋጅተዉ ቅድመ ትንተና ሂደት ተከናዉኗል፡፡ በመሆኑም ከማጣራት ስራ በመቀጠል የተማሪዎችን ችሎታ ለመለካትና ስለ ትብብራዊ መማር ዘዴ ያላቸውን ግንዛቤ ለማየት በቅድመ ትምህርትና፣ በድህረ ትምህርት ፈተና፣ እንድሁም በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ የመረጃ ውጤቶችን በመተንተን፣ መጠንን በሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ ዘዴዎች እንዲገለጹ ለማድረግ SPSS version 20 ተክኖሎጂን ከጥቅም ላይ እንዲዉል ተደርጓል፡፡

## 3.7 የጥናቱ አተገባበር ሂደት

የዚህ ጥናት አቅራቢ ሙከራዊ ጥናቱን ከመጀመሩ በፊት በሲግሞ ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት በመገኘት ስለጉዳዩ የሚመለከታቸዉን በማነጋገርና ይሁንታ በማግኘት ሲግሞ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሄድ ከርእሰ መምህሩ ጋር በመገናኘት ፈቃድ ጠይቋል፡፡ ከዛም አብሮ በመሆን በጥናቱ ስራ ድጋፍ የሚሰጡና የሙከራ ቡድኑን የሚያስተምር መምህር ስለሚያስፈልገዉ 10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ሶስት መምህራን ጉዳዩን በማስረዳት ፈቃደኛ ስለመሆናቸዉ በማረጋገጥ ለሙከራ ቡድኑ አንድ መምህር እንዲመረጥ ተደርጓል፡፡ ከዛም በመቀጠል በነጋታዉ ቀጠሮ በመያዝና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ስልጠና እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ እንደ(Nunnan1992፣Johonson&Johnason (1999) አገላለጽ ትብብራዊ መማርን ለመተግበር መምህራን ትብብራዊ መማርን እንዲተገብሩ አስቀድመዉ ስለምንነቱና የትግበራዉ ሂደት በቂ ስልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ሁኔታ አመቺ ይሆን ዘንድ አጥኚዉ የስልጠና ጽሁፉን አስቀድሞ በማዘጋጀት መምህሩ እንዲደርሳቸዉና አንብበዉ በመምጣት ርእሰጉዳዩ በዉይይት ሊዳብር በሚችል መልኩ ስልጠናዉ እንዲጀመር ተደረገ፡፡ በዚህ መልኩ ተጀምሮ አምስት ሰአታትን የወሰደ ስልጠና በተለያየ ቀን

እንዲጠናቀቅ ተደርጓል፡፡ የስልጠና ማንዋሉ የተዘጋጀው አጥኚዉ ትብብራዊ መማርን አስመልክቶ ከላይ በተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ ውስጥ ከዘረዘራቸው ይዘቶች እና በርዕስ ጉዳዩ ዙሪያ Johnson & Johnson (1990) ና ሌሎች የዘርፉ ምሁራን የጻፏቸውን መርሆችን መሠረት ያደረገ ነዉ፡፡ የስልጠና ማኑዋሉም አራት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን የትብብራዊ መማር ምንነት፣ የትብብራዊ መማር ጥቅሞች፣ ትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆች፣ ትብብራዊ መማር ስልቶች እንዲሁም በትብብራዊ መማር የተማሪዎችና የመምህራን ሚናን እንድሁም ትብብራዊ መማርና በተለመደዉ (ቡድን) መማር መካከል ያለው ልዩነት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

### 3.7.1 የትብብራዊ መማር ቡድኑ አደራጃጀት

ስለትብብራዊ መማር ማስተማር ግንዛቤ ስልጠና ተሰጥቶ እንደተጠናቀቀ ቀጣዩ ተግባር ተጠኚ ተማሪዎችን ማዘጋጀት ነበር፡፡ ለዚህም ቀደም ሲል በተገለጸዉ ሁኔታ የየክፍሎቹን ተማሪዎች የችሎታም ሆነ ሌሎች ስብጥርና ምደባን በማረጋገጥ የተጠኚ ክፍሎቹን በቀላል እጣ ናሙና የመለየት ስራ ተከናዉኗል፡፡ በቀጣይ የተተኳሪ ተማሪዎችን የንባብ ክህሎት ዳራ ለማወቅ በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ ለሚሳተፉት ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና በመስጠት ፈተናው ከታረመ በኋላ ምድቦቹ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተብለው ዳግም በቀላል ዕጣ ንሞና ዘዴ ተለይተዋል፡፡ ከዛም በመቀጠል የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎች ውጤታቸውን መሠረት በማድረግ በቡድን በቡድን ሲደራጁ እያንዳንዱ ቡድን ስድስት ስድስት አባላት እንድይዝ ተደርገዉ እንዲዋቀሩ ተደርጓል፡፡ ትብብራዊ ቡድኑን ስድሰት ስድሰት እንድሆኑ የተደረገበትም ዋናዉ ምክንያት በዚህ ዘዴ ዉስጥ ይህን ሞዴል(Team paire solo) በመተግበር ንባብና ተያያዥ የመልመጃ ስራዎች ደረጃዎቹን ጠብቀዉ እንዲሰሩ ለማድረግ አስቀድመዉ በቡድኑ፣ ከዛም በሁለትዮሽ ቀጥለዉ በተናጠል(በግል) ለሚከናወኑ የንባብ፣ የዉይይትና የመገማገም ትግበራ ስራዎች አመቺ እንድሆን ታሳቢ በማድረግ የተከናወነ ሲሆን በአጠቃላይ የክፍሉ ተማሪዎች በአምስት ቡድን እንድደራጁ እና ትምህርታቸዉን እንዲከታተሉ ተደርጓል፡፡

### 3.7.2 በትብብራዊ ቡድን ሚና የመከፋፈልና የስራ ድርሻ ሁኔታ

በትብብራዊ መማር ቡድን ውስጥ የተማሪዎችን ሚናና ተግባርን በሚመለከት የቡድን አባላት ከሌሎች ሚናዎች በተጨማሪ የስራ ክፍፍል ማድረግ እንዳለባቸው ዓለማየሁ (2009) ይገልጻሉ፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ ሚና መከፋፈል አስፈላጊ በመሆኑ እላይ በተጠቀሰዉ

ሁኔታ ቡድኑ ከተዋቀረ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ በቡድኑ ዉስጥ የሚተገብራቸዉን ሚና እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡ በትብብረዊ መማር ለእያንዳንዱ ቡድን አባል የተለያዩ ሚናዎችን ማከፋፈል ትብብራዊ መማርን በቡድን ከመማር እንዲለይ ከሚያደርጉት ባህሪያት አንዱ ነው፡፡ በትብብራዊ ቡድን ውስጥ ያሉ ስድስት ስድስት አባላት የተዋቀሩት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እንዲቀያየሩ ተደርገው ነው፡፡ ምክንያቱም በትብብር ተግባር ወቅት እኩል ተሳትፎ እንድኖራቸው በማድረግ የተለያዩ ሀላፊነቶች እንዲጋሩ ለማድረግ ሲባል ሚናዎቹን በመቀያየር ተማሪዎች በመካከላቸው ተደጋጋፊነት እንዲኖር ያደርጋል ዓለማየሁ (2009፡፡ ለእያንዳንዱ ተማሪ ሚና ማከፋፈል የተሠጣቸው ሀላፊነት ምን እንደሆነ እንዲገነዘቡ ያስችላል፡፡ የሚከፋፈሉት ሚናዎቹም አላይ በምእራፍ ሁለት ስር በትብብር መማር ዳሰሳ ዉስጥ የተማሪዎች ሚና ስብራራ ከተግባራቸዉ ጭምር የተገለጸዉ ይሆናል፡፡

የሙከራ ቡድኖቹ ከተዋቀሩና ሚና ክፍፍሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የተዘጋጀዉን መማሪያ ጽሁፍ መሰረት በማድረግ የንባብና የክሂሉን መልመጃዎች መሠረት በማድረግ አተገባበሩ እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ ለጥናቱ ሥራ ላይ የዋለውን የማስተማሪያ ይዘት ጽኁፉን ለማዘጋጀት በቅድሚያ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የክህሉን ተግባራት ማየት አስፈላጊ ነበር፡፡ ይህም በክፍል ደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች ተመጣጣኝ ተግባራትን ለማዘጋጀት አመቺ ሲለሚሆን አጥኚዉ የቁጥጥር ቡድኑንም ሆነ የሙከራ ቡድኑን ለማስተማር ከመማሪያ መጽሀፍ ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ ተጨማሪ ጽሁፎችን ያማከለና መርሀትምህርቱን መሠረት በማድረግ አዘጋጅተዋል፡፡ መምህሩም እነዚህን የንባብ ተግባራት በሙከራ ቡድን ውስጥ ለተካተቱ ተማሪዎች ለማስተማሪያነት እንዲተገብር ሲያደረግ  በተመራማሪዉ በተዘጋጀለት የትብብራዊ መማር የትምህርት ዕቅድ አማካይነት ነው፡፡ እንደምሁራኑ አገላለጽ የንባብ ክሂሎት ትምህርት በትብብራዊ መማር ዘዴ ሲቀርብ ራሱን የቻለ የትብብራዊ መማር የትምህርት ዕቅድ መዘጋጀት አለበት ዓለማየሁ(2009)፡፡ ምክንያቱም እንደ አገላለጻቸዉም በመተባበር መማር ስኬታማ የሚሆነው ሁለት አስፈላጊ ነገሮች ሲሟሉ ነው፡፡ እነሱም በመጀመሪያ ተማሪዎች በንቃትና በሙሉ ተሳትፎ ለመማር ዝግጁ እንዲሆኑ መምህሩ የትምህርት ዕቅዱን ሲያዘጋጅና ተማሪዎችንም በተገቢው ለመማር እንዲችሉ ሲያደርጋቸው ነው፡፡  ዓለማየሁ(2009) በመተባበር መማር ራሱን ችሎ ከታቀደና ከተተገበረ በተማሪዎች ላይ የውጤት መሻሻል ሊታይ ይችላል፡፡ ተማሪዎችም ሌሎችን የመረዳት ክሂሎታቸው ይጨምራል በማለት ገልጾታል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ አጥኚዉ

ዓለማየሁ (2009፣104) መሠረት በማድረግ የትምህርት ዕቅዱን አዘጋጅቶታል፡፡ ዕቅዱም ሲዘጋጅ የትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆችን በመከተል ሲሆን የትምህርት ዕቅዱ ትምህርታዊ ዓላማዎችን፣ ትብብራዊ ዓላማዎችን፣ በትብብር መማር ጊዜ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ባህሪያትን፣ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ሚናዎችን፣ ግለሰባዊ ተጠያቂነትና አዎንታዊ ተደጋጋፊነትን፣ እንዲሁም የስኬት መስፈርቶችን በማካተት የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በትብብራዊ ቡድናቸው አማካኝነት ሚናዎችን ተከፋፍለው እንዲሰሩ ተደርገዉ የተዘጋጀ ነዉ፡፡ በዝግጅቱም ሙከራዊ ቡድኑ በትብብራዊ መማር አማካይነት በተዘጋጀው የትምህርት እቅድ ስማሩ የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደዉ(ቀደምሲል በሚሰራበት) የትምህርት እቅድ እንድማሩ በማድረግ የተከናወ ነዉ፡፡

## 3.7.3 በትብብራዊ መማር የግልና የቡድን ጽብረቃ ሂደት

በሙከራ ቡድን የተሳተፉት ተማሪዎች ትብብራዊ ተግባር መጨረሻ ላይ ባለ ሰባት ነጥብ የመገምገሚየ ቅጽ የያዘና እያንዳንዱ ተማሪ በቡድን ሥራው ወቅት የነበረውን ግላዊ ተሳትፎ እንዲገልጽበት የሚያስችል ነዉ፡፡ ትብብራዊ መማር በሚተገበርበት ጊዜ ተማሪዎች ከትግበራው በኋላ ስለስራቸው ሁኔታ እንዲያንፀባርቁ ማድረግ የትብብራዊ መማር አንድ አካል ነው Nunan (1997)፡፡ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል በግምገማ ቅጹም በትብብራዊ መማር ጊዜ የነበረውን ጠናካራና ደካማ ጎን የተገነዘበዉን እንድያንፀባርቅ እና ለሚቀጥለው የትብብራዊ መማር ተግባር እራሱን አርሞና ዝግጁ ሆነዉ እንዲቀርብ ያስችሉታል፡፡ በተጨማሪም መከናወን ያለበት ተግባር በሙከራ ቡድን ውስጥ የተሳተፉ ተማሪዎች በትብብራዊ ቡድኑ ውስጥ የነበራቸው ግላዊ ተሳትፎ ከመገምገም በተጨማሪ የቡድኑን ጠንካራና ደካማ ጎን እንደ አንድ ቡድን ሆኖ መገምገምና ማንፀባረቅም ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ተግባር የሚሆን የቡድኑ አባላት እራሳቸውን እንዲገመግሙና እንዲያንፀባርቁ የሚያስችል አምስት ነጥቦችን የያዘ የቡድኑን ጠንካራና ደካማ ጎን የመገምገሚያ ቅጽ በእያንዳንዱ የንባብ ማለቂያ ላይ ለእያንዳንዱ ቡድን እንድታደል ተደርጓ ይሞሉታል፡፡ ሁለቱም ቅጾች ከትምህርት ዝግጅት ጋር አባሪ ዉስጥ ማየት ይቻላል፡፡

## 3.8 የቅድመ እና ድህረ ፈተና አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት

በአንድ የጥናት ሂደት ውስጥ ትክክለኛነት እና አስተማማኝነት ሰፊ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ መሰረተዊያን ጉዳዮች ናቸው፡፡ አስተማማኝነት የአንድ ባህሪ ወይም ነገር በአንድ መለኪያ በመጠቀም በተደጋጋሚ በመለካት የሚገኝ የውጤት ወይም የልኬት ተመሳሳይነት፣

ቋሚነት፣ ወጥነትን ወይም አይለወጤነትን ማመልከቱ ሲሆን ትክክለኛነት ደግሞ አንድ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለመሰብሰብ የታቀደውን መረጃ በታሰበው መንገድ በተቃና፣ በተሟላና በተገቢ ሁኔታ ለመሰብሰብ ማስቻሉን የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የቅድመ ፈተና አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የጥንቃቄና አግባብነት ያላቸዉ ስራዎች በተጨማሪ ለተጠኚ ተማሪዎች ፈተናው ከመቅረቡ በፊት ቢጋታ በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ በሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ፈተናውን በመስጠት በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቶ 0.87 በማስመስገቡ አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ ድህረ ፈተናውም እንደ ቅድመ ፈተናው ሙከራው ከሚካሄድበት ትምህርት ቤት በቅርብ ርቀት ለይ በሚገኝ ቢጋታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኑ ተደርጎ በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቶ 0.95 በመምጣቱ ፈተናው አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለበት ነዉ፡፡

## 3.9 የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝነትና ትክክለኛነት

ከጥናቱ ድህረ ፈተና ጋር ተማሪዎቹ የሞሉትን የጽሁፍ መጠይቅ የአስተማማኝነት ደረጃjውን ለማስላት ክሮንባኽ አልፋ የቀመር ስሌት ተግባር ላይ በማዋል በዚህም 20 ጥያቄዎች በSPSS ውስጥ ኮድ በመስጠት እንዲገባ ተደርገዉ የአስተማማኝነት ደረጀው ሲሰላ የጽሁፍ መጠይቅ የክሮንባኽ አልፋ ውጤቱ 0.87 ሆኗል፡፡ ይህም ለተማሪዎቹ የቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝነት ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

## 3.10 የናሙና ሙከራዉ ጥናት አካሄድ

በከፊል ሙከራዊ የምርምር ሂደት የናሙና ሙከራ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊና በርከት ያሉ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ ከነዚህም የተወሰኑትን ለመጥቀስ የተወሰዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመለየት፣ ከጥናቱ አብይና ዝርዝር ዓላማዎች አንጻር ከተሰበሰበው የመረጃ አተናተን የተሻለ ስልትን መርጠዉ ለመጠቀም እና ለዋናው ጥናት አመች የሆነ የአተገባበር ሂደት ለመወሰን ከመርዳት አልፈዉ ከተያዘዉ የጥናቱን ጊዜ ከሌሎች ተግባራት ጋር በማቀናጀት ለመስራት የሚያስችል ልምድ ይገኝበታል፡፡ እንድሁም የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ያላቸው ተስማሚነት ለመገምገም የሚረዳና በዋናው ጥናት ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ተረድተዉ መፍትሄ እየሰጡ ለመሄድ እና የፈተናዎችን አስተማማኝነትና ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የሚያግዝ ይሆናል፡፡ ለዚህም ሲባል በዚህ ጥናት ወደ ሙከራ ጥናት ከመገባቱ በፊት የናሙና ጥናት ተካኸዷል፡፡ የናሙና ጥናቱም የተካኸደው በዚሁ ትምህርት ቤት ዙሪያ ከሚገኙት ዉስጥ ቢጋታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ትምህርት ቤቱ የተመረጠው ካሉት 3 ትምህርት ቤቶች መካከል

በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ ነው፡፡ በዚሁ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ካሉት 6 የ10ኛ መማሪያ ክፍሎች መካከል አንድ ክፍል በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ እዚሁ ክፍል ውስጥ ከሚገኙ 40 ተማሪዎች መካከል 30 ተማሪዎች በናሙና ጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዉ የናሙና ሙከራዉ ተከናዉኖዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት፤ የመረጃ ትንተና እና የወጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

በዚህ ጥናት ቀደም ሲል በምእራፍ ሶስት ላይ እንደተገለጸው የጥናቱ መረጃዎች አሰባሰብ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተከናወኑ ነበሩ:: መረጃዎቹም ከታለሙለት ዓላማዎች እና ከተነደፈዉ መላምት አንጻር ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ይህ ጥናት ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት የቁጥጥርና በሙከራ ቡድን ዉስጥ የነበሩትን ተጠኚዎች የቅድመና የድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ዉጤቶች ለማነጻጸር በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ ይህንን ስታስትክሳዊ ትንተና ለማከናወን SPSS Version 20 ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡ የጥናቱ ዓላማዎች ትኩረትም የንባብ ችሎታን በሚመለከት በትብብራዊ መማር ዘዴና በተለመደዉ መማር ዘዴ መካከል የታየው የተማሪዎች ውጤት ምን እንደሚመስል በመመርመር መግለጽ እና እንዲሁም በትብብራዊ መማር ዘዴ ዙሪያ ተማሪዎች ከግንዛቤ አንጻር ምን አስተያየት እንዳላችዉ ማየት ናቸዉ፡፡ በዚሁም መሰረት በዚህ ጥናት “ትብብራዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረዉን ሚና ለመመርመር” የሚለዉን አላማ ለማሳካት የተነደፈዉ መላምት፡-

ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የሚያመጣዉ መሻሻል አለ ወይም ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የሚያመጣዉ መሻሻል የለም

የሚል ሲሆን በሙከራዉ የዉጤቱን አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት ለማረጋገጥ በቅድሚያ የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራዊ ቡድኑ ተሳታፊዎች ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ያላቸውን የንባብ ችሎታ እና ልዩነት ለማወቅ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ በዚህም ያመጡትን የፈተና ውጤት ለመተንተን ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 1 ተጠቃሎ በሚከተለዉ ሁኔታ በገላጭ ስታስቲክስ ተገልጸዋል፡፡

### 4.1.1 የቁጥጥር ቡድኑ እና የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና ትንተና

በዚህ ክፊል ሙከራዊ ጥናት የቅድመ ልምምድ ፈተና ዋና አላማ ሙከራዉ ከመከናወኑ በፊት የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚገኙበትን ደረጃ ለማወቅ፣ እንዲሁም በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል ጉልህ የሆነ የችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ እንዲረዳ ነዉ፡፡ ለዚሁ አላማ ሲባል የተሰጣቸዉ የቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት በባኢድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ታይቶ በሚከተለዉ ሁኔታ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡- የቁጥጥርና የሙከራዉ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት መግለጫ፡-

| ቡድን | ናሙና | አማካይ ዉጤት (m) | መደበኛ ልይይት (SD) | መደበኛ የጉልህነት መጠን | የቲ-ዋጋ (ቲ) | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ (በባለሁለት ጫፍ) (2tailled |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር | 31 | 14.5484 | 3.639 | .65447 | --0.389 | 60 | 0.699 |
| ሙከራ | 31 | 14.2258 | 2.839 | .50997 | | | |

እላይ ከሰንጠረዥ 1 ላይ ለመመልከት እንደተሞከረዉ በጥናቱ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና ያገኙትን አማካይ ውጤት መግለጫ ነዉ፡፡ በሠንጠረዡ ላይም ከገላጭ ስታቲስቲክስ (descriptive statstics) መረጃዉ መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥሩ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት 14.5484 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ 14.2258 መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተጨማሪ የቁጥጥር ቡድኑ መደበኛ ልይይት 3.639 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ መደበኛ ልይይት ደግሞ 2.7105 መሆኑን እናያለን፡፡ ይህ የገላጭ ስታስቲስትካል ዉጤት እንደሚገልጸዉ በሁለቱ ቡድኖች ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ከልምምድ በፊት የነበራቸዉ የንባብ ችሎታቸዉ በሚቀራረብ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አማካይ ውጤታቸውን በማየት ብቻ በመካከላቸው ስላለው የማንበብ ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር አስቸጋሪ ሲለሚሆን አማካይ ውጤታቸው መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን በስታቲክስ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህንንም

ለማወቅ መረጃው በሁለት አማካይ ውጤታቸው መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅና ድምዳሜ ላይ ለመድረስ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተሰልቷል፡፡ በዚህም ውጤቱ በ 60 የነፃነት ደረጃ የቲ=-0.389, የpዋጋ=.699 ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ በንባብ ችሎታ ረገድ ሲገለጽ በሁለት ቡድኖች አማካዮች መካከል ስታስቲክስ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም የpዋጋ ከ0.05 በልጦ ተገኝቷል እና(p=0.699>0.05)፡፡ በመሆኑም በዉጤቱ መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የቅድመ ትምህርት የንባብ ችሎታቸው የጎላ ልዩነት አለመኖሩን አይተናል ማለት ነዉ፡፡ ስለሆነም ከዉጤቱ መገንዘብ የሚቻለዉ፣ በዚህ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የሁለቱም ቡድኖች ተማሪዎች ሙከራዉ ከመጀመሩ በፊት ተቀራራቢ የንባብ ችሎታ ያላቸዉ መሆኑን ያሳየናል፡፡ ይህ ዉጤት ከታወቀ በኋላ በቀጣይ የመጣዉ ተግባር የሙከራዊ ቡድኑ በትብብራዊ መማር ዘዴ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለመደዉ(የገለጻ) የመማር ማስተማር ዘዴ እንዲማሩ በማድረግ ቀደም ሲል ለመግለጽ በተሞከረዉ ሁኔታ በተከታታይ ለስድስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ቀን በቀን ለአርባ አምስት ደቂቃዎች ሲማሩ ቆይተው ድህረ ትምህርት የማንበብ ችሎታ ፈተና እንዲሰጣቸዉ ተደርጓል፡፡ ይህንኑ የፈተና ዉጤት መነሻ በማድረግ ሁለቱም ቡድኖች በድህረ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት ደግሞ ቀጥለን ከዚህ በታች በቀረበዉ በሠንጠረዥ፡- 2 ላይ ስታትስትካል መግለጫዉን መመልከት እንችላለን፡፡

## 4.1.2 የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና ትንተና ማሳያ

በዚህ ከፊል ሙከራዊ ጥናት የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ የድህረ ልምምድ ፈተና ዋና አላማዉ በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች መካከል ቀደም ሲል ከነበራቸዉ አቅም በተሻለ ሁኔታ በትብብራዊ ዘዴዉ ልምምድ ምክንያት በአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉ ላይ መሻሻል መኖሩን ወይም አለመኖሩን ፈትሸዉ ለማወቅ እንደመሆኑ መጠን ዘዴዉ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በማዳበር ረገድ ያሳየዉን ሚና በሚመለከት፣ በቅድመ ልምምዱና በድህረ ልምምዱ የተሰበሰቡ የአንብቦ መረዳት የመረጃ ዉጤቶች ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሚከተለዉ ሁኔታ እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና የንባብ ችሎታ ውጤት ንጽጽር በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲገለጽ

| ቡድን | ናሙና | አማካይ ዉጤት (m) | መደበኛ ልይይት (SD) | መደበኛ የጉልህነት መጠን | የቲ-ዋጋ (ቲ) | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ(በባለሁለት ጫፍ) sig(2tailled |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁጥጥር | 31 | 14.8817 | 2.46689 | .44307 | -2.425 | 60 | 0.018 |
| ሙከራዊ | 31 | 16.804 | 2.7395 | .353715 | | | |

ከላይ በሠንጠረዠ 2 ላይ ከተገለጸዉ ስታስትክሳዊ መግለጫ መረዳት እንደሚቻለዉ በድህረ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና የሙከራዊ ቡድኑ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት 16.5592 ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ 14.8817 ዉጤት አስመዝግቧል፡፡ ይህ ስታስቲስትካዊ ዉጤት የሚያሳየዉ የሙከራዊ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከቁጥጥሩ ቡድኑ አማካይ ውጤት በ1.6675 በልጦ መገኘቱን እናያለን፡፡ ይህ ደግሞ በሁለቱም ቡድኖች መካከል በማንበብ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ሁለቱም ቡድኖች ያስመዘገቡት መደበኛ ልይይት በሚታይበት ጊዜ የቁጥጥር ቡድኑ 3.639 ሲሆን ሙከራዊ ቡድኑ ደግሞ 2.839 ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ቡድኖች ካስመዘገቡት አማካይ ዉጤት መረዳት እንደሚቻለዉ የሙከራ ቡድኑ ዉጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ዉጤት ብልጫ እንዳለዉ ያመላክታል፡፡ እንዲሁም የሁለቱን አማካይ ዉጤት በማየት ብቻ በመካከላቸው ስለላው የንባብ ችሎታ ልዩነት በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም ልዩነታቸውን በስታቲስቲክስ ስሌት ለማረጋገጥ በሁለቱም አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት አማካኝነት ተሰልቶ ውጤቱም (ቲ 60=-2.425, p=.018) ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ በንባብ ችሎታ ረገድ ሲገለጽ በቡድኖቹ ድህረ ትምህርት የንባብ ችሎታ መካከል በስታቲስቲክስ ስሌቱ የጎላ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡

ምክንያቱም የተገኘው የp ዋጋ 0.018  ከ0.05አንሶ መገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም(0.018<0.05) ይህ ውጤት እንደሚያሳየው የሙከራ ቡድኑ የንባብ ችሎታ ውጤት የተሻሻለ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ከዚህም የሚንረዳው በትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሩት ተማሪዎች ውጤታማ መሆናቸውን እና በሁለቱ ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት መኖሩን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከዚህ በመነሳት በትብብራዊዉ ማስተማር ዘዴ የዚህን ጥናት ሞዴል ደረጃዎችን ተግባራዊ አደርገዉ የተማሩ ተማሪዎች ዉጤታማ መሆናቸዉን እንረዳለን፡፡

## 4.1.3 የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የሚኖረዉ ሚና መመርመር ሲሆን ከዚሁ አንጻር የጽሁፍ መጠይቁ አላማና አሰፈላጊነት ተማሪዎቹ ከሚወስዱት የንባብ ችሎታ ፈተና በተጨማሪ ስለትብብራዊ መማር ዘዴዉ የንባብ ችሎታቸዉን ከማሻሻል አንጻር ያላቸውን ግንዛቤ ለማየት ነዉ፡፡ ለዚህም 20 ዝግ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዉ የቀረቡ ሲሆን ተማሪዎቹ ከቀረበላቸዉ አራት የመልስ አማራጮች መካከል የተስማሙበትን እንዲመርጡ በማድረግ ምላሻቸዉ ተቀነባብሮ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሚከተለዉ ሁኔታ በሰንጠረዥ 3 እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽኁፍ መጠይቅ በዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት

| የጥያቄዉ ዓይነት | የጥያቄ ብዛት | ናሙና S | አማካይ (m) | መደበኛ ልይይት (SD) | መደበኛ የስህተት መጠን | የቲ-ዋጋ (ቲ) | የነጻነት ደረጃ (ቲ) | የጉልህነት ደረጃ (በባለሁለት ጫፍ) Sig(2tailled) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመትምህርት የንባብ መጠይቅ | 20 | 31 | 2.4032 | .46457 | .8344 | | 30 | |
| ድህረ ትምህርት የንባብ መጠይቅ | | | 2.6613 | .16619 | .02985 | -2.912 | | .005 |

እላይ ከሰንጠረዡ መግለጫ ላይ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎቹ በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ያገኙት አማካይ ውጤት2.4032 ሲሆን በድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ያመጡት አማካይ ዉጤት ደገሞ 2.6613 ነዉ፡፡ ይህ ዉጤት የሚያሳየን ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ ከቅድመ ልምምዱ የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት በልጦ ታይተዋል፡፡ መደበኛ ልይይቱ ከቅድመ ትምህርት ይልቅ በድህረ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ ዝቅተኛ የመደበኛ ልይይት ውጤት መገኘቱን እላይ ከተገለጸዉ ከሰንጠረዡ መግለጫ መገንዘብ ይቻላል(0.166619<0.46457)፡፡ በሰንጠረዥ 3፡የተመለከትነው መረጃ ዉጤት በቅድመ የጽሁፍ መጠይቅ እና በድህረ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት በስታቲስቲክስ ጉልህ መሆኑን ለማረጋገጥ የዳግም ልኬታ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ተደርገዉ ሲረጋገጥ በ60 የነፃነት ደረጃ (ቲ=-2.330) የp ዋጋ (.005) ሆኗል፡፡ ይህም ዉጤት በንባብ ችሎታ ረገድ ሲገለጽ የሚያሳየው በቅድመ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቁ እና በድህረ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ አማካዮች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል፡፡ በመሆኑም ይህን ዉጤት መሰረት በማድረግ ትብብራዊ መማር ዘዴዉ የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በዚህ ከፊል ሙከራዊ ጥናት የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ ትብብራዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ እንዲሁም ከዝርዝር ዓላማዎቹም አንጻር ተማርዎች በትብብራዊ ዘዴዉ ትግበራ አኳያ ያላቸዉን ግንዛቤ በማየት፣ በዚህም የተማሪዎች የቅደመ እና የድህረ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነበር፡፡ የነዚህን ዓላማዎች ስኬታማነት ለማረጋገጥ ጥናቱ የሁለት ቡድን ቅድመ ትምህርትና ድህረትምህርት ከፊል ሙከራዊ (two group quasi experimental design) የተገበረ በመሆኑ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን አለዉ፡፡ ከመነሻዉ ጥናቱ የነደፈዉ መላምትን ለማረጋገጥ በፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በተገቢዉ የስታስትስቲክስ ዘዴ እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ከማሻሻል አንጻር በሙከራና በቁጥጥር ቡድን የተካተቱት የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው በምን አይነት ደረጃ ላይ እንደሆነ ለማወቅ ወደ ሙከራዉ ሳይገባ የሁለቱም ቡድኖች ቅድመ ትምህርት ተፈትኗል፡፡ ቅድመ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች መስጠት ያስፈለገበት

ዋናዉ አላማ ከሙከራዉ በፊት በሁለቱም ቡድን የተካተቱ ተጠኚ ተማሪዎች የንባብ ችሎታቸዉ ተቀራራቢ መሆኑን እና ያለመሆኑን ለማረጋገጥ እና የሁለቱን ቡድኖች የሚገኙበትን ደረጃ ለማወቅ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት በሁለቱም ቡድኖች መካከል በቅድመ ትምህርቱ የንባብ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን በባዕድ ናሙና ቲ-ቲስት ፍተሻ ስተስቲካዊ ስሌት የተገኘው አማካይ የጉልህነት ደረጃ ውጤት (በ60 የነጻነት ደረጃ የቲ=-0.389, የp ዋጋ=0.669) ያሳያል፡፡ ይህ የሰንጠረዥ 1 ዉጤት በሁለት ቡድኖች አማካይ ዉጤት መካከል ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ምክንያቱም (0.669>0.05) የp ዋጋ በልጦ መገኘቱን ነዉ፡፡ ይህም የጉልህነት ማሳያ ዉጤት ከ0.05 በልጦ ተገኝተዋል፡፡ ስለሆነም ይህ መረጃ የሙከራዉ ጥናት ከመከናወኑ በፊት በቁጥጥርና በሙከራ ቡድን መካከል ጉልህ የሆነ የንባብ ችሎታ ልዩነት አለመኖሩን እና ሁለቱም ቡድኖች ተቀራራቢ የሆነ የማንበብ ችሎታ እንዳላቸው የሚያመላክት ነዉ፡፡

በቀጣይም የቁጥጥር ቡድኑን በተለመደዉ የመማር ዘዴ በማስተማር የሙከራ ቡድኑን ደግሞ ትብብራዊ መማርን በመጠቀም እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በዚህ መልኩ ሁለቱም ቡድኖች ውስጥ ያሉ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በተጠቀሱት ዘዴዎች አማካይነት ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ትምህርት ሲማሩ ከቆዩ በኋላ የንባብ ችሎታ መለኪያ ድህረ ልምምድ ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተናዉ ቲ-ቴስት ስሌት ዉጤትም እንደሚያሳየው በሙከራ ቡድኑ የተሳተፉ ተማሪዎች የንባብ ችሎታቸዉ አማካይ ውጤት በቁጥጥር ቡድኑ ካሉ ተማሪዎች አማካይ ውጤት በልጦ መገኘቱን አሳይተዋል፡፡ ሁለቱም ቡድኖች በድህረ ትምህርት ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡ በዚህም መሠረት በሁለቱም ቡድኖች መካከል በድህረ ንባብ ፈተና ጉልህ ልዩነት መኖሩንና የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት በልጦ መገኘቱን እንረዳለን ይህንንም (ሠንጠረዥ፡2 ላይ ማየት ይቻላል)፡፡ ዉጤቱም በጥናቱ መነሻ የተነደፈዉን “ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የሚያመጣዉ መሻሻል አለ” የሚለዉን መላምት በመደገፍ “ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የሚያመጣዉ መሻሻል የለም” የሚለዉን ደግሞ ዉድቅ ያደርጓል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በትብብራዊ መማር ቡድናቸዉ ሆነዉ ሶስቱን የዚህን ሞዴል (Team Paire Solo) የቡድን፣ የሁለትዮሽና የተናጠል(የግል) ደረጃዎችን በመተግበር የተማሩባቸውን የንባብ ክሂል ትምህርት

በትብብራዊዉ ዘዴ ሲማሩ ከወትሮዉ በተሻለ ያለፍርሀት እርስ በርስ ሀሳብ መለዋወጥ፣ በመረዳዳት፣ በመደጋገፍና የማያዉቁትን እየጠየቁና ያወቁትን ነገር ለጓደኞቻቸዉ በመግለጽ በመማራቸው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ፡፡ በመሆኑም የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ትብብራዊ መማርን ተጠቅሞ ንባብን ማስተማር በሙከራ ቡድኑ ለተሳተፉ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ መሻሻል ማስገኘቱን ያመለክታል፡፡

ስለዚህም ከጥናቱ ውጤት ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ከፍተኛ ሚና እንዳለው መረዳት ይቻላል ይህም የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት የበለጠ ሆኖ በስታትስቲክስ ሲታይ ቲ=-2.424 የp =ዋጋ (0.018) ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ ከ 0.05 ያነሰ መሆኑን ሲያረጋግጥ ሙከራዊ ቡድኑ የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት የጎላ ልዩነት እንዳለዉ የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የንባብ ችሎታን ለማሻሻል በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር ከፍተኛ ሚና እንዳለው መረዳት እንችላለን፡፡

የዚህ ጥናት ግኝት ትብብራዊ መማርን በክፍል ውስጥ መተግበር ለተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን የትምህርት ግብዓቶች ግልጽና ሊረዱት እንደሚችሉት ሊያደርግላቸው ይችላል ከሚለው ከkagan (1995) እና Jacobs (2004) ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ ለዚህም አስተዋጽኦ ያላቸዉ ምክንያቶችን ለመግለጽ ያክል የመጀመሪያዉ በትብብራዊ የቡድን ተግባር ውስጥ በሚኖር በተለይም በዚህ ሞዴል ሶስት ደረጃዎችን በመከወን የእርስ በርስ ሀሳብ ልዉዉጥ ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ነገር ግልጽ እንዲሆንላቸው እንዲብራራላቸው ይጠያየቃሉ፣ ይወያያሉ፡፡ ተማሪዎች በሚጠይቁበት እና በሚወያዩበት ጊዜ ተጨማሪ ግብዓት እንዲያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ አስፈለጊ በሆነ ጊዜ ይህንን ግብዓት አውጥተው እንዲጠቀሙበት እድሉን ያመቻቻል፡፡ ይህን በሚያግዝ መልኩ  አለማየሁ(2009) ሲገልጹ በመተባበር መማር ሂደት የሚኖር ድርጊትና እንቅስቃሴ በአዕምሮአቸው ውስጥ ሊታወስ በሚችል መንገድ ተቀርጾ ስለሚኖር፣ ይህንን በአዕምሮ ውስጥ ተቀርጾ የተቀመጠ እውቀትና ክህሎት ደግሞ አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ተማሪዎች አፍልቀው ሊጠቀሙበት ይችላሉ በማለት ገልጸዉታል፡፡

እንዲሁም ለዚህ ግኝት አስተዋጽኦ ያደረገው ሌላኛው ምክንያት ተማሪዎች በትብብራዊ መማር ቡድናቸዉ የተለያዩ ሚናዎችን ተከፋፍለው በመስራታቸውና እነዚህን ሚናዎች በየክፍለ ጊዜው እንዲቀያየሩ በመደረጋቸው ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በእኩል ተሳትፎ እንዲያከናውኑ፣ የቋንቋ ክህሎቻቸውን እንዲያጎለብቱና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያስችሏቸዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ተግባር መጨረሻ በትብብራዊ ቡድን ሥራው ወቅት ስለነበራቸው ግላዊ ተሳትፎና እነሱ የተመደቡበት ቡድን ስለነበረው ጠንካራና ደካማ ጎን በተከታታይ በየምእራፉ መጨረሻ እንዲያንጸባርቁ በመደረጋቸው ድክመቶቻቸውን እንዲያርሙና የበለጠ እንዲሰሩ አድሉን ሰፊ አደርጎላቸዋል፡፡

በተጨማሪም ለግኝቱ መምጣት እንደ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው ጉዳይ እያንዳንዱን የትብብር መማር ተግባር በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚየደርጉበት ወቅት ተማሪዎች እርስበርሳቸው እንዲደጋገፉና እንዲተጋገዙ ለማድረግ የግለሰባዊ ተጠያቅነትና የአዎንታዊ ተደጋጋፊነት መርህን (ብዙ ለአንድ አንድ ለብዙ) መሰረት አድርገው ተግባራትን እንዲያከናውኑ በመደረጋቸው ነው፡፡ ይህ ሁኔታም ‹‹የቡድን አላማ መሳካት የሚወሰነው እያንድንዱን የቡድን አባል በቡድን ውስጥ ለመማርና የቡድኑን ዓላማ ለማሳካት በሚያደርገው ጥረት ነው›› ከሚለው ከJolliffe (2007፣3) ሀሳብ ጋር መስማማቱ ነዉ፡፡ እንዲሁም በእያንድንዱ የትብብራዊ መማር ተግባር መጀመሪያ ላይ የስኬት መስፈርቶቹን ለይተዉ እንዲሰሩ ስለሚነገራቸው ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ የተቀመጠላቸውን መስፈርት መሰረት አድርገው ስኬት ላይ እንዲደርሱ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያበረክቱና ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛቿል፡፡

ስለሆነም በዚህ ከፊል ሙከራዊ ጥናት ግኝት በድህረ ትምህርቱ የንባብ ችሎታ የተገኘው ውጤት ጉልህ በመሆኑና ትብብራዊ መማር በተማሪዎች የንባብ ችሎታ ላይ አዎንታዊ ለውጥ እንዳለው በማሳየት ግኝቱ ካሁን በፊት በተመሳሳይ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ካከሄዱ ሰዎች ማለት Amold(1997)፣ Ghaith (2003)፣ Alyuiamita(2012) እና ዘነበች(2012) ግኝት ጋር የሚመሳሰል እና በተዛማጅ ጥናት ዳሰሳ ወቅት በተጠቀሱት ጥናቶች ያልተብራሩ የትግበራ ጉዳዮችን ለመመለስ ጥረት አደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ከፊል ሙከራዊ ጥናት የትብብር መማር መሰረታዊ መርሆች የሆኑት የአዎንታዊ ተደጋጋፊነት፣ ግለሰባዊ ተጠያቂነት፣ የፊት ለፊት ሀሳብ መለዋወጥ፣ የማህበራዊ ክህሎትና የቡድን ጽብረቃ መሰረታዊ መርሆች በሙከራ ቡድኑ ውስጥ በተካተቱት ተማሪዎች ላይ በትክክል እንዲተገበሩ በመደረጋቸው የሙከራ ቡድኑ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ውጤት ብልጫ እንዲያሳይ ያደረጉ ምክንያቶች መሆኑን አጥኚዉ እምነቱ ነዉ፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

ይዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ ትብብራዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና መመርመር ሲሆን ዝርዝር አላማዎችም በትብብራዊ የመማር ዘዴዉ በተማሪዎች ዉጤት ላይ የሚመጣዉ መሻሻል ስለመኖሩ እና በትብብራዊ ዘዴ የመማር ትግበራ አንጻር ያለዉን ግንዛቤ ማየት  የሚሉት ናቸዉ፡፡ ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ከፈተናና ከጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በፈተና አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ መሠረት በማድረግ በትብብራዊ መማር ዘዴ መማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታን ለማሻሻል ሚና እንዳለው ለማረጋገጥ መረጃው በባዕድ ናሙና ቲ-ቴሰት ሲተነተን የሙከራዊ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ በድህረ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ የጎላ ልዩነት በመታየቱ በትብብራዊ መማር ዘዴ መማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ጉልህ ሚና እንዳለው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በተለመደዉና በትብብራዊ ዘዴ በተማሩት ተማሪዎች መካከል የታየው የተማሪዎች ውጤት ስሌት መሠረት የድህረ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና የሙከራዊ ቡድኑ አማካይ ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት በ1.669 በልጦ ተገኘቷል፡፡ ይህንን (በሠንጠረዥ 2 ላይ ይመልከቱ) በዚህ ዉጤት መሰረት በሁለቱ ቡድኖች በማንበብ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን እንረዳለን፡፡ እንድሁም በትብብራዊ መማር ዘዴ ዙሪያ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ ማየት እንደተቻለዉ  በቅደመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ አማካዮች መካከል በስታትስቲክስ ስሌት ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡ (ይህን ከሠንጠረዥ 3 ማየት ይቻላል) በዚህም መሰረት ትብብራዊ መማር ዘዴ በተማሪዎች የንባብ ችሎታና ግንዛቤ ላይ ለውጥ ማሳየቱንና ሚና እንዳለዉ እንረዳለን፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ከመረጃ መተንተኛ ዘዴዎቹ ዉጤት መረዳት እንደሚቻለዉ የሙከራዉና የቁጥጥር ቡደኑ በቅድመ ትምህርት የንባብ ችሎታ ፈተና ያስመዘገቡት አማካይ ዉጤት መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ነዉ፡፡ ሆኖም ግን የሁለቱ ቡድኑ ተማሪዎች የድህረ የንባብ ችሎታ ፈተና ዉጤት እንደሚያሳየዉ የሙከራ ቡድን የንባብ ችሎታ ዉጤት ብልጫ እንዳለዉ አሳይተዋል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

ይዚህ ጥናት አላማ ትብብራዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና መመርመር ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት በከፊል ሙከራዊ ጥናቱ የተሰበሰበዉ መረጃ ተተንትኖ የተደረሰበትን ውጤት መሠረት በማድረግ በአጥኚዉ የሚከተለው የመደምደሚያ ሀሳብ ተሰጥቷል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳሳየው ከተለመደዉ የቡድን መማር ዘዴ ይልቅ ትብብራዊ መማር ዘዴዉ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታን ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ ተማሪዎችን አሳታፊ የሆነው ትብብራዊ መማር ዘዴ ተማሪዎች በትብብራዊ ቡድናቸዉ የዚህን ጥናት ሞዴል(Team Paire Solo) ተግባራዊ በማድረግ እርስ በእርሳቸው በመረዳዳት፣ በመወያየት፣ በማንበብ፣ በመደማመጥ፣ በመጠያየቅ ችግሮቻቸውን በመፍታት የተሻለ ደረጃ ያለው አስተሳሰብ ባለቤት እንዲሆኑ የሚያደርግ በመሆኑ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ሚና እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡

ትብብራዊ መማር ዘዴ በክፍል ውስጥ በሚኖረዉ ሀሳብ መለዋወጥ ወቅት በሙከራ ቡድኑ የተካተቱት ተማሪዎች በተዘጋጀላቸው ማለማመጃ ጽሁፍ ማለትም የቀረበዉን ምንባብ የንባብ ደረጃዎችን ተግባራዊ በማድረግ፣ በትብራዊ ስልት ትግበራ በዚህ ከፊል ሙከራዊ ጥናት የቀረበዉን ሞዴል 3 ደረጃዎችን በመተግበር ማለትም (የቡድን፣ የጥንድዮሽ እና የተናጠል) ስልት(Team Paire Solo) ሂደቱን ጠብቀዉ በማንበብ የጽሁፉን አጠቃላይ መልእክት መለየት፣ የምንባቡን ዋናና ዝርዝር ሀሳብ መለየት፣ በቀጥታና በተዘዋዋሪ በጽሁፉ የቀረቡ እዉነታዎችን መረዳት በመቻላቸዉ፤ እንዲሁም በቀረቡት መልመጃዎች በመጠቀም መስራት መቻላቸዉ ችሎታቸው መሻሻሉን ያሳያል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችል መንገድ(አንዱ ለሀሉም፣ ሁሉም ለአንድ) በሚል መርህ ጓደኞቻቸውን መደገፍና ማበረታታት ሲችሉ እንደሆነ የትንተና ውጤቱ የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡

## 5.3 አስተያየት

የዚህ ጥናት አቅራቢ ትብብራዊ መማር ዘዴን በከፊል ሙከራዊ ጥናት በመተግበር በሙከራ ቡድኑ የተካተቱ ተማሪዎች የማንባብ ችሎታ በማጎልበት ረገድ ሙከራዉ ካስገኘዉ ጠቀሜታ አንጻር ለወደፊት ለዘዴዉ ትግበራና ቀጣይ የምርምር ስራዎች ይሆናሉ የሚሉዋቸዉን ሀሳቦችና አስተያየቶች እንደሚከተለዉ አቀርቧል፡፡

በዚህ ጥናት ግኝት መሠረት የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ጉሊህ ሚና ያለዉ ዘዴ መሆኑን በመገንዘብ፡-

1. በየደረጃዉ ለዘዴው መተግበር ትኩረት በመስጠት ዘዴውን ቢጠቀሙ፣
2. በየደረጃዉ ያሉ የትምህርት ባለሙያዎች ስለ ትብብራዊ መማር ዘዴ ምንነትና አተገባበር ስልጠና እንዲሰጥ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተማሪዎችን በንባብ ክህሎት በመማር ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ ለማድረግ ጥረት ቢደረግ፣
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የትብብራዊ መማር ዘዴን በክፍል ውስጥ በተገቢው መንገድ እንዲጠቀሙ በማበረታታት ስለ ትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆችና አተገባብሩ ስለዘዴው በሰለጠኑ ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት የሚቻልበት ስልት ቢፈለግ፡፡
4. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ረገድ የንባብ ችግር በየትኛውም የክፍል ደረጃ የሚያጋጥም ችግር በመሆኑ የመጽሀፍ አዘጋጆች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ የንባብ ችሎታን ሊያዳብሩ የሚችሉ መልመጃዎች ንባብን የሚያበረታቱ እንዲሆኑ በማድረግ እንዲዘጋጁ የሚደረግበት ስልት ቢቀየስ፣
5. በመማሪያ መጽሐፍ የክፍል ውስጥ ተግባራት ባብዛኛዉ ሁሉንም ክህሎቶች በማመጣጠን የቀረቡ አይመስሉም፡፡ ይህ ሁኔታ ክህሎቶቹን በጥምረት ይዘዉ ተማሪዎችን ውጤታማ ከማድረግ አንጻር ክፍተት ሊፈጥር ይችላል የሚል ሀሳብ ይኖረኛል፡፡ ምክንያቱም ክህሎች በመማሪያ መጽሀፍት ዉስጥ ሲቀርቡ በተመጣጠነ መልኩ ለተማሪዎች ካልቀረቡ ተማሪዎች ውጤታማ ላይሆኑ ሲለሚችሉ፤ በመሆኑም ለንባብ ክሂሉ መሻሻል በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንደሚገባዉ አጥኚዉ ይገነዘባል፡፡በዚህም መሠረት በመማሪያ መጽሐፍት ውስጥ በትብብራዊ መማር ዘዴ ሊያሰሩ የሚችሉ በርካታ የመልመጃ ጽሁፎች መካተት የሚችሉበት ሁኔታ ቢመቻች፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት ያተኮረው በ10ኛ ክፍል በሁለት መማሪያ ክፍል በተመደቡ ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ጥናቱ በሙከራ ቡድን ውስጥ የታቀፉ ተማሪዎችን የንባብ ችሎታ በማሳደግ ረገድ ጉሊህ ሚና ቢያስመዘግብም በነዚሁ ውስን ተማሪዎች ብቻ የተገኘውን አዎንታዊ ውጤት መሰረት አድርጎ ዘዴው ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰራና ወጤታማ ነዉ በማለት ድምዳሜ ወይም ማጠቃለያ መስጠት አስቸጋሪ ስለሚሆን፤ የዚህን ጥናት አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በተመሳሳይ ርዕስና በተቀሩት ክሂሎቶች ላይ ተጨማሪ ሙከራዊ ጥናቶች የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ጥናቶች ሊካሄዱ እንደሚገባ መታወቅ አለበት በማለት አጥኚዉ አስተያየቱን ይሰጣል፡፡

# ዋቢዎች


*መሪነሽ ነጋሽ* (2004) ‹‹*የማንበብ ተነሳሽነትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ፡፡››* *የድግሪ ማሚያ የቀረበ ጽሁፍ፡ በባህርዳር ዩንቨርስቲ (ያልታተመ)፡፡*

*መአዛ ደጀኔ* (1999) ‹‹በ9ኛ ክፍል የንባብትምህርት አሰጣጥ ለንዑሳን የንባብ ክሂሎች የሚሰጣቸው ትኩረት ፍተሻ፡፡›› የኤም ኤ ድግሪ ማሚያ ጥናታዊ ጽሁፍ፡ አድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ማረው አለሙ ፡፡ (1998) ፡፡ ***የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡*** አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላምማተሚያ ድርጅት፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር (2004) ***አማርኛ፤ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ 10ኛ ክፍል፡፡*** አዲስ

አበባ፣የአል-ጉሬር አሳታሚ ድርጅት።

ግሩም ጥበቡ (2003) “የታችላይ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ለማዳበር ያለዉ ውጤታማነትና ተተግባሪነት፡፡›› አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኤም ኤ ድግሪ ማሚያ ጥናታዊ ጽሁፍ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ(1981) ስነ ልሳን እና ቋንቋን ማስተማር፡፡ (ያልታተመ)

አለማየሁ ተክለማሪያም ፡፡ (2009)፡፡ ***በመተባበር መማር፡፡*** አዲስ አበባ፤ ፈርሲ ትሬዲን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

እንግዳ ዘውዳ (1992) “የቶፕ ዳውን” የንባብ ማስተማሪያ ሞደል በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለው ተተግባራዊነትና ውጤታማነት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካኼደ ጥናት፡፡›› አድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኤም ኤ ዱግሪ ማሚያ ጥናታዊ ጽሐፍ (ያልታተመ)፡፡

ያለዉ እንዳወቀ፡፡ (2001)፡፡ ***የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር::*** ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፡፡

ያለዉ እንዳወቀ፡፡ (2009)፡፡ ***የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡*** ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፡፡

ዘነበች ቃሎሬ (2011) ‹‹ትብብራዊ የመማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት›› ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)

Aebersold, J. Ann & Mary.L.F(1997) ***From Reader to Reading teacher***. New York: Cambridge university press.

Anderson, J.(1965) ***Research in Readability for the classroom Teachers***.Journal of Reading.vol.18 No.6.International Reading Assocition.

Ariningsih, D. (2010) ***The Effectiveness of using picture Series to Improve the Studentes writing skill viewed from their Learning Motivatiion.*** Thesis submitted for Graduate degree in English Eduction, sehelas Maret University

Grabe, W .and L.F.Stoller.(2002) ***Teaching and Researching Reading***. Hariow: Pearson Education.

Grellet,F. (1981) ***Developing Reading Skills***. Cambridge, University Press.

Isaacs,B. (2008) ***Cooperative learning implementing an altrnitive teaching and learing strategy in grade 7 technolgy clss 2008 cupt theses and dissertaions***. Avaliable at http//dk.oput.ac.2a/tdoput/19.

Jacobs,G. and Hannah, D.(2004) ***Combining cooperative learning with reading aloud by teachers.*** International journal of English studies. Vol4, No. 1, pp. 97-118.

Jalilifar, A. (2010). ***The Effect of Cooperative Learning Techniques on College Students Reading Comprehension.*** System.Vol. 38, pp. 96-108.

Jollife, WW2007 ***cooperative learning in the class room***. Putting in to practice London Chapman.

Johnson,k.(2005) eds ***Experties in Language Learning and Teaching.*** Palgrave macmillan.

Jollife,WW 2007 ***cooperative learning in the class room. Putting in to practice.*** London Chapman. Kagan,S. (1995) <<Grup Grade Miss the mark>> Educational Leader ship, 52 (8); 68-71.

Kagan, and Kagan, M (2009), kagan ***cooperative learing*** san clementer CA Kagan publishing

Karsak, H .G.O, Far, S, and Orhan,F(2014) ***Effective of using cooperative and individual Webing to Enhance writing performance***. Education and socity, 17 (14), 229-241

Ghaith, G (2003) ***Effects of the Learning Together Model of Cooperative Learning on English as a Foreign Language Reading Achievement*** TheJournal of Na tional Association for Bilingual Education. 27 (3), pp. 451-474.

Meiryun, Y. (1995) "***Teaching Efficient EFL Reading***" Inkral, Tomas Leds. Teacher Development Making the Right Moves. Washington,DC.PP.

Natall,C.(1982) ***Teaching reading skill in foreighn Language***. London helnemann educational Books Ltd

Norrish H.J.(1983) ***Language Learners and their errors***. London and Basing stoke.Memillan Publishers Ltd.

Nunan, D. (1991) ***Language Teachinig methodology***. aTextbook for Teachers. New York Prentice Hall Inc.

Piaget,J. (1966) ***Psychology of intelligence***. Totowa,NJ: Littelfield, Adam

Richards, .J.(1990) ***The langusge teaching matrix***. Cambridge: Cambridge university press.

Slavin, R.E.(1995) ***Research on cooperative learning: Consensus and controversy.Educational leadership,*** 47(4), 52-54.

Smith, F.(1971) ***Understanding Reading***.New York, NY: Holt, Rinehart and Winston.

USAID /Ethiopia.(2003) ***Improving Quality of Primary Education Program*** (USAID/IQPEP) in Ethiopia. Addis Ababa.

Vygotsky, L.S.(1978) ***Mind in society*** (M.Cole,V.John-Steiner,S.Scribner,&E. Souberman, Eds.)

Williams, E.(1984) ***Reading in the Language Class room***. London: Macmillan Publishing

Johnson D.and Johnson,R (2009) *An Overview of Cooperative Learning* from http://www.cooperation.org/page/overviewpaper.htmal

Abadi (2012) *improving Students Reading comprehension through cooperative Learning using team paire solo*. http://www:Research Gate.Com et,

Rita Rani-mandal. (2009) *Cooperative Learning Strategies to enhance writting skill.* themodern Journal of applied linguistic Volume 1:2 http://www.coop.

.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ፡- የናሙና ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የንባብ ችሎታ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤቶች

| ኮድ | የቅድመ ልምምድ ፈተና ዉጤቶች ከ 30% | | | | የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤቶች ከ 30% | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አራሚዎች | | | | አራሚዎች | | | |
| | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ወጤት | አራሚ 1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ወጤት |
| 1 | 13 | 12 | 12 | 12.33333 | 14 | 12 | 9 | 11.667 |
| 2 | 15 | 16 | 15 | 15.33333 | 14 | 15 | 14 | 14.333 |
| 3 | 12 | 10 | 10 | 10.66667 | 16 | 13 | 14 | 14.333 |
| 4 | 11 | 10 | 12 | 11 | 17 | 29 | 17 | 21 |
| 5 | 14 | 14 | 15 | 14.33333 | 13 | 15 | 14 | 14 |
| 6 | 20 | 17 | 17 | 18 | 12 | 12 | 19 | 14.333 |
| 7 | 18 | 19 | 20 | 19 | 19 | 22 | 21 | 20.667 |
| 8 | 12 | 15 | 19 | 15.33333 | 14 | 12 | 12 | 12.667 |
| 9 | 9 | 10 | 10 | 9.666667 | 13 | 16 | 12 | 13.667 |
| 10 | 13 | 15 | 14 | 14 | 15 | 13 | 15 | 14.333 |
| 11 | 10 | 13 | 14 | 12.33333 | 20 | 16 | 15 | 17 |
| 12 | 9 | 8 | 7 | 8 | 14 | 9 | 14 | 12.333 |
| 13 | 10 | 10 | 9 | 9.666667 | 18 | 20 | 14 | 17.333 |
| 14 | 9 | 10 | 10 | 9.666667 | 18 | 17 | 16 | 17 |
| 15 | 11 | 11 | 12 | 11.33333 | 10 | 15 | 11 | 12 |
| 16 | 13 | 15 | 14 | 14 | 12 | 18 | 12 | 14 |
| 17 | 12 | 10 | 11 | 11 | 15 | 18 | 16 | 16.333 |
| 18 | 7 | 8 | 8 | 7.666667 | 15 | 22 | 17 | 18 |
| 19 | 10 | 12 | 12 | 11.33333 | 17 | 18 | 15 | 16.667 |
| 20 | 18 | 17 | 16 | 17 | 13 | 12 | 13 | 12.667 |
| 21 | 15 | 13 | 14 | 14 | 16 | 13 | 15 | 14.667 |
| 22 | 12 | 10 | 11 | 11 | 17 | 13 | 14 | 14.667 |
| 23 | 12 | 10 | 10 | 10.66667 | 10 | 13 | 11 | 11.333 |
| 24 | 11 | 10 | 12 | 11 | 14 | 15 | 14 | 14.333 |
| 25 | 14 | 14 | 15 | 14.33333 | 13 | 15 | 16 | 14.667 |
| 26 | 20 | 17 | 17 | 18 | 20 | 17 | 18 | 18.333 |
| 27 | 18 | 19 | 20 | 19 | 16 | 11 | 12 | 19 |
| 28 | 12 | 10 | 11 | 11 | 15 | 14 | 16 | 15 |
| 29 | 7 | 8 | 8 | 7.666667 | 14 | 17 | 16 | 15.667 |
| 30 | 10 | 12 | 12 | 11.33333 | 19 | 12 | 12 | 14.333 |
| 31 | 18 | 17 | 16 | 17 | 16 | 10 | 10 | 12 |

አባሪ ለ፡ የሙከራ ቡድኑ የንባብ ችሎታ የቅድመ ትምህርትና የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤቶች

| ኮድ | የቅድመ ልምምድ ፈተና ዉጤቶች ከ 30% | | | | የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤቶች ከ30% | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አራሚዎች | | | | አራሚዎች | | | |
| | አራሚ1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ወጤት | አራሚ1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ወጤት |
| 1 | 11 | 13 | 10 | 11.33333 | 15 | 14 | 16 | 15 |
| 2 | 10 | 14 | 13 | 12.33333 | 22 | 22 | 23 | 22.333 |
| 3 | 14 | 11 | 12 | 12.33333 | 20 | 18 | 18 | 18.667 |
| 4 | 18 | 18 | 19 | 18.33333 | 12 | 15 | 14 | 13.667 |
| 5 | 12 | 13 | 11 | 12 | 15 | 13 | 16 | 14.667 |
| 6 | 13 | 11 | 12 | 12 | 22 | 16 | 16 | 18 |
| 7 | 20 | 19 | 21 | 20 | 21 | 21 | 18 | 20 |
| 8 | 11 | 12 | 11 | 11.33333 | 21 | 20 | 19 | 20 |
| 9 | 13 | 11 | 15 | 13 | 10 | 16 | 17 | 14.333 |
| 10 | 12 | 11 | 13 | 12 | 13 | 13 | 12 | 12.667 |
| 11 | 16 | 20 | 20 | 18.66667 | 18 | 23 | 21 | 20.667 |
| 12 | 9 | 10 | 10 | 9.666667 | 11 | 10 | 9 | 10 |
| 13 | 18 | 20 | 19 | 19 | 15 | 16 | 16 | 15.667 |
| 14 | 15 | 17 | 19 | 17 | 12 | 13 | 14 | 13 |
| 15 | 12 | 10 | 10 | 10.66667 | 15 | 14 | 16 | 15 |
| 16 | 10 | 12 | 11 | 11 | 14 | 13 | 14 | 14.333 |
| 17 | 16 | 15 | 15 | 15.33333 | 16 | 15 | 17 | 16 |
| 18 | 18 | 20 | 15 | 17.66667 | 21 | 22 | 21 | 21.333 |
| 19 | 16 | 16 | 14 | 15.33333 | 19 | 19 | 18 | 18.667 |
| 20 | 9 | 11 | 12 | 10.66667 | 14 | 13 | 15 | 14 |
| 21 | 13 | 18 | 17 | 16 | 20 | 18 | 18 | 18.667 |
| 22 | 11 | 15 | 12 | 12.66667 | 12 | 15 | 14 | 13.667 |
| 23 | 12 | 16 | 14 | 14 | 15 | 13 | 16 | 14.667 |
| 24 | 13 | 13 | 18 | 14.66667 | 15 | 16 | 16 | 15.667 |
| 25 | 15 | 14 | 12 | 13.66667 | 15 | 14 | 18 | 15.667 |
| 26 | 13 | 15 | 15 | 14.33333 | 17 | 16 | 16 | 16.333 |
| 27 | 20 | 19 | 18 | 19 | 19 | 21 | 20 | 20 |
| 28 | 14 | 13 | 13 | 13.33333 | 16 | 15 | 14 | 15.333 |
| 29 | 13 | 15 | 15 | 14.33333 | 17 | 13 | 17 | 16.333 |
| 30 | 17 | 15 | 11 | 14.33333 | 21 | 19 | 20 | 20 |
| 31 | 15 | 16 | 14 | 15 | 18 | 18 | 19 | 18.667 |

,

አባሪ ሐ፡ የቁጥጥር ቡድኑ የንባብ ችሎታ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤቶች

| ኮድ | የቅድመ ልምምድ ፈተና ዉጤቶች ከ 30% | | | | የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤቶች ከ 30% | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አራሚዎች | | | | አራሚዎች | | | |
| | አራሚ1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ወጤት | አራሚ1 | አራሚ 2 | አራሚ 3 | አማካይ ወጤት |
| 1 | 13 | 11 | 10 | 11.333 | 12 | 9 | 14 | 11.667 |
| 2 | 18 | 19 | 18 | 18.333 | 25 | 18 | 17 | 20 |
| 3 | 11 | 13 | 12 | 12 | 12 | 19 | 12 | 14.333 |
| 4 | 12 | 11 | 14 | 12.333 | 13 | 16 | 14 | 14.333 |
| 5 | 20 | 19 | 21 | 20 | 21 | 22 | 19 | 20.667 |
| 6 | 11 | 13 | 15 | 13 | 13 | 16 | 12 | 13.667 |
| 7 | 20 | 17 | 18 | 18.333 | 15 | 20 | 16 | 17 |
| 8 | 11 | 12 | 10 | 11 | 10 | 15 | 11 | 12 |
| 9 | 13 | 10 | 14 | 12.333 | 14 | 10 | 15 | 13 |
| 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 13 | 10 | 14 | 12.333 |
| 11 | 16 | 16 | 15 | 15.667 | 16 | 17 | 16 | 16.333 |
| 12 | 20 | 20 | 18 | 19.333 | 20 | 13 | 17 | 16.667 |
| 13 | 18 | 20 | 15 | 17.667 | 17 | 23 | 15 | 18.333 |
| 14 | 24 | 23 | 27 | 24.667 | 13 | 14 | 14 | 13.667 |
| 15 | 24 | 23 | 21 | 22.667 | 12 | 14 | 12 | 12.667 |
| 16 | 15 | 15 | 16 | 15.333 | 17 | 15 | 17 | 16.333 |
| 17 | 12 | 11 | 10 | 11 | 13 | 12 | 17 | 14 |
| 18 | 12 | 11 | 10 | 11 | 22 | 18 | 12 | 17.333 |
| 19 | 12 | 11 | 15 | 12.667 | 13 | 13 | 17 | 14.333 |
| 20 | 13 | 18 | 13 | 14.667 | 14 | 15 | 19 | 16 |
| 21 | 12 | 13 | 12 | 12.333 | 15 | 13 | 15 | 14.333 |
| 22 | 17 | 11 | 15 | 14.333 | 12 | 19 | 12 | 14.333 |
| 23 | 15 | 16 | 15 | 15.333 | 10 | 10 | 16 | 12 |
| 24 | 14 | 13 | 13 | 13.333 | 15 | 15 | 16 | 15.333 |
| 25 | 15 | 13 | 15 | 14.333 | 14 | 17 | 16 | 15.667 |
| 26 | 10 | 9 | 10 | 9.6667 | 9 | 15 | 12 | 12 |
| 27 | 14 | 13 | 15 | 14 | 20 | 17 | 18 | 18.333 |
| 28 | 15 | 12 | 14 | 13.667 | 13 | 15 | 12 | 13.333 |
| 29 | 17 | 13 | 17 | 15.667 | 16 | 13 | 15 | 14.667 |
| 30 | 15 | 13 | 14 | 14 | 10 | 18 | 11 | 13 |
| 31 | 11 | 10 | 12 | 11 | 12 | 17 | 12 | 13.667 |

አባሪ መ፡- በናሙና ሙከራ ጥናቱ ተማሪዎች ስለትብብራዊ መማር ያላቸውን አስተያየት በተመለከተ በቅድመ የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ

| ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 1 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 |
| 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 |
| 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| 5 | 4 | 3 | 1 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 6 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 |
| 7 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 2 |
| 8 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 |
| 9 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 10 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 |
| 11 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 |
| 12 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 |
| 13 | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 4 |
| 14 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 |
| 15 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 16 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 1 | 3 |
| 17 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 |
| 18 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 |
| 19 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 20 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 |
| 21 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| 22 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 |
| 23 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 | 1 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| 24 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 25 | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 |
| 26 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 |
| 27 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 4 |
| 28 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 |
| 29 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 30 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 1 | 3 |
| 31 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 32 | 3 | 2 | 1 | 1 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 |

አባሪ ሠ፡- በናሙና ሙከራ ጥናቱ ስለትብብራዊ መማር ያላቸውን አስተያየት በተመለከተ በድህረ ትምህርት  የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ

| ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 |
| 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 |
| 5 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 |
| 6 | 3 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 4 |
| 7 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 8 | 1 | 2 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 |
| 9 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 | 3 |
| 10 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 |
| 11 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 4 | 2 | 3 |
| 12 | 2 | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 13 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 |
| 14 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 |
| 15 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 4 |
| 16 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 |
| 17 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 |
| 18 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 19 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 |
| 20 | 3 | 1 | 1 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 |
| 21 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 22 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 |
| 23 | 1 | 2 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| 24 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 |
| 25 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 1 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 |
| 26 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 4 |
| 27 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 |
| 28 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 |
| 29 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 30 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 |
| 31 | 3 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 |

አባሪ ረ፡ የሙከራ ጥናቱ ስለትብብራዊ መማር ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ የሰጡት ቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 1 | 1 | 1 | 4 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 4 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 |
| 2 | 1 | 2 | 3 | 43 | 4 | 1 | 1 | 3 | 4 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 | 4 | 2 |
| 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 5 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 1 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 4 | 1 |
| 6 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 7 | 3 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 8 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 |
| 9 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 10 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 4 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 | 4 |
| 11 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 12 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 1 | 1 | 3 | 1 |
| 13 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 |
| 14 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 | 4 |
| 15 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 |
| 16 | 2 | 4 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 17 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 18 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 19 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 |
| 20 | 2 | 1 | 1 | 4 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 |
| 21 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 22 | 1 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 |
| 23 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 1 | 2 |
| 24 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 4 |
| 25 | 1 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 4 |
| 26 | 1 | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 1 | 2 |
| 27 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 28 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 29 | 1 | 4 | 4 | 4 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 4 |
| 30 | 1 | 4 | 1 | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | 1 | 4 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 4 | 1 | 2 | 3 | 2 |
| 31 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 |

አባሪ ሰ፡የሙከራ ጥናቱ ስለትብብራዊ መማር ያላቸውን ግንዛቤ በተመለከተ ለቀረበላቸዉ ጥያቄ የሰጡት ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

| ኮድ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 |
| 2 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 |
| 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 |
| 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 |
| 5 | 2 | 2 | 2 | 4 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| 6 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 7 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| 8 | 2 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| 9 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 |
| 10 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 |
| 11 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 |
| 12 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 13 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 14 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 |
| 15 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 16 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 2 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 |
| 17 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 1 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | |
| 18 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 19 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 |
| 20 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 |
| 21 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| 22 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 |
| 23 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 |
| 24 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| 25 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 26 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 4 |
| 27 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 28 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 |
| 29 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 |
| 30 | 4 | 3 | 4 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 |
| 31 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |

# አባሪ ፡ ሸ ሰንጠረዥ 5

## የንባብ ችሎታ ለመለካት በቅድመና ድህረ ፈተና እንድሁም ስለ ትብብር መማር የተሰበሰቡ መረጃዎች በSPSS versione 20 ተሰልተዉ የወጡ መረጃዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

**Group Statistics**

| | Expermental and control group | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | T | DF | p-value |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| pretest | Experimental Group | 31 | 14.2258 | 2.83939 | .50997 | -0.389 | 60 | 0.699 |
| | Control group | 31 | 14.5484 | 3.64396 | .65447 | | | |

**Group Statistics**

| | Expermental and control group | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | T | DF | p-value |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| pretest | Experimental Group | 31 | 16.5592 | 2.96067 | .53175 | 2.424 | 60 | 0.018 |
| | Control group | 31 | 14.8817 | 2.46689 | .44307 | | | |

**Group Statistics**

| | Expermental and control group | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | T | DF | p-value |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| pretest | Pre-test | 31 | 2.4032 | .46457 | .08344 | -2.912 | 60 | .005 |
| | Post test | 31 | 2.6613 | .16619 | .02985 | | | |

## አባሪ ቀ፤- ለተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ልምምድ የጽሁፍ መጠይቅ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀግብር

ኮድ ________

ይህ መጠይቅ ትብብራዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና መመርመር በሚል ርዕስ ለሚጠናዉ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከናንቱ የሚሰበሰበዉ መረጃ ለዚሁ ጥናት አገልገሎት የሚውል በመሆኑ ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡ የእናንተ ትክክለኛ ምላሽ መረጃ የጥናቱ ውጤት ትክክለኛና ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ እገዛ ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቀጥታ ምላሽ እንድትሰጡ መልካም ትብብራችሁን ሲጠይቅ ስለትብብራችሁ በቅድሚያ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ**

ዉድ ተማሪዎች በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አስፈላጊ አይሆንም፣ መጠይቁ በየግል የሚሞላ በመሆኑ ከጓደኛ ጋር ወይም በኩረጃ መሙላት በእናንተ ምላሽ ላይ የተመሰረተውን ጥናት ውጤትን ሊያዛባ ሲለሚችል በጥንቃቄ መስራት ይጠበቅባቿል፡፡

**መመሪያ፡** ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው አራት አራት አማራጭ መልሶችን ይዘዋል፡፡ እያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ በማንበብ ከፊት ለፊት ከተሰጡት አራት አማራጮች መካከል የተስማማቹበትን በአንዱ አማራጭ ትይዩ ይህን “×” ምልክት አድርጉ፡፡ ከ 1- 4 ያሉት ቁጥሮች ዉክልናም እንደሚከተለው ነው ፡፡

1. በጣም አልስማማም
2. አልስማማም
3. እስማማለሁ
4. በጣም እስማማለሁ

| ተ.ቁ | ስለ ትብብራዊ መማር የቀረቡ ጥያቄዎች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ትብብራዊ መማር ለንባብ ችሎታዬ መሻሻል ረድቶኛል | | | | |
| 2 | ትብብራዊ መማር በንባብችሎታ አንጻር መረጃ ለመለዋወጥ ረድቶኛል | | | | |
| 3 | ትብብራዊ መማር በንባብ ክሂሎት ትምህርት ረገድ የሚያጋጥመኝን ችግር መፍትሄ ለመፈለግ ረድቶኛል፡፡ | | | | |
| 4 | ትብብራዊ መማር በክፍል ዉስጥ ያለፍርሀት የመማር ድባብ እንዲፈጠር ይረዳል፡፡ | | | | |
| 5 | ትብብራዊ መማር ከጓደኞቼ እገዛና ድጋፍ እንዳገኝ ረድቶኛል፡፡ | | | | |
| 6 | ትብብራዊ መማር የማሰብና የማሰላሰል ችሎታዬሰን ለማሻሻል ድቶኛል፡፡ | | | | |
| 7 | ትብብራዊ መማር በትምህርት ደከም ያሉ ተማሪዎችን ለማገዝናለመደገፍ ይረዳል፡፡ | | | | |
| 8 | ትብብራዊ መማር ከግል ጥረት ለጋራ ጥረት ትኩረት እንዲሰጥ አደርጎናል፡፡ | | | | |
| 9 | ትብብራዊ መማር በቡድን ስራ የጋራ ሀላፍነት እንዲወጣ ረድቶኛል፡፡ | | | | |
| 10 | ትብብራዊ መማር የተግባቦት ችሎታ ለማዳበር ጠቅሞኛል፡፡ | | | | |
| 11 | ትብብራዊ መማር የንባብ አቅሜን ለማሻሻል ረድቶናል፡፡ | | | | |
| 12 | ትብብራዊ መማር በመማር ማስተማር ሂደት ያዝናናል፡፡ | | | | |
| 13 | ትብብራዊ መማር አዳድስ ጓደኞችን ለመተዋወቅ ረድቶኛል፡፡ | | | | |
| 14 | ትብብራዊ መማር ለማህበራዊ ግንኑነት ይረዳል፡፡ | | | | |
| 15 | ትብብራዊ መማር በመምር ማስመተማር ሂደት በንቃት ለመሳተፍ ይረዳል፡፡ | | | | |
| 16 | ትብብራዊ መማር አዳድስ ግንዛቤዎችን ለማግኘት ይረዳል | | | | |
| 17 | ትብብራዊ መማር የቡድን ስራን ያፋጥናል፡፡ | | | | |
| 18 | ትብብራዊ መማር በአዎንታዊ መደጋገፍ የንባብ ችሎታ እንዲጨምር ረድቶኛል፡፡ | | | | |
| 19 | ትብብራዊ መማር የንባብ አቅም ለማጎልበት ግዜን አይሻማም፡፡ | | | | |
| 20 | ትብብራዊ መማር የጥንደና የቡድን ሰራዎች ሊበረታቱ የረገባል፡፡ | | | | |

አባሪ፡ በ  ቅድመ ትምህርት ፈተና

ጅማ ዩኒቨበ ርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀግብር

ኮድ_______

ለ10ኛ ክፍል ተጠኚ ተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ትምህርት ፈተና(ከ30%)

ፈተናው የሚጀምርበት ስዓት 2፡30 ስዓት

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ2፡00 ስዓት

አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች፤ የዚህ ፈተና ዋና አላማ ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ከማሻሻል አንጻር ያለውን ሚና ለመፈተሽ ለታቀደው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፤ ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሆነው ሶስት ንዑሳን ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ የመጀመሪያዉ በምንባቡ መሰረት የቃላትና ሀረጋትን ፍች ማዛመድ ከዛም ትክክለኛዉን ሃሳብ እዉነት ስህተት የሆነዉን ሀሰት በማለት፣ በቀጣይ የምንባቡን ዝረዝርና ዋና ሃሳብ የያዘ ትክክለኛ ሃሳብ መግለጽ ናቸዉ፡፡

እያንዳንዱን ምንባብ መሰረት ያደረጉ አስር አስር በድምሩ 20 ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በመሆኑም የቀረቡትን ምንባቦች መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ ነው የምትሉዋቸውን ለመልስ መስጫ በተሰጠው ቦታ በመምረጥ ሙሉ ፡፡

## ምንባብ 1

ቆሻሻ ከመኖሪያ ቤታችን፣ ቢሮዎችና ከእንድስትሪዎች እያወጣን የምንጥለዉ የማይፈለግ ነገር ነዉ፡፡ ቆሻሻ ሲባል ቤቦታዉ ተዝረክርኮ ወይም በየቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ዉስጥ ያለ ደረቅ ቆሻሻ፣ ከዚያም እርጥብ የእንድስትሪ ቆሻሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁላችንም ቁርጥራጭ ወረቀቶችን፣ የምግብ ትርፍራፊዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን በምንጥልበት ወቅት ቆሻሻ እንፈጥራለን፡፡ የኢንዱስተሪ ምርቶች በሚመረቱበት ጊዜም ቆሻሻ ይፈጥራሉ፡፡

ቆሻሻ ቁጥጥር ካልተደረገበትና በማንኛዉም ቦታ የሚጣል ከሆነ፣ በአከባቢና በሰዉ ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህም አፈርን ወይም ዉሃን በማይበክልበት ቦታና ሰዎችም በዚሁ ሳቢያ ለአደጋ በማይጋለጡበት ሁኔታ ማስወገድ አለብን፡፡

ማንኛዉም የቆሻሻ  አይነት በአግባቡ ካልተያዘ እኛንና አከባቢን ሊጎዳ ይችላል በአግባቡ የአከባቢን እይታ ያበላሻል፤ መጥፎ ጠረን ያስከትላል፡፡ ለዝንቦች፣ ለአይጦችና ልዩ ልዩ ተዋስያን መራቢያ በመሆን በሽታ እንዲሰራጭ ያደርጋል፡፡ ዕጽዋትን፣ እንስሳትንና ሰዎችን ይመርዛል፡፡ አየርና ዉሃን ይበክላል፡፡ የረዥም ጊዜ ጎጂ ተጽእኖዉ ደግሞ መርዛማ ኬሚካሎች በአከባቢዉ ዉስጥ ሳይሰባበሩ መቆየታቸዉና በአየርና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ ነዉ፡፡

ሁላችንም ብንሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቆሻሻ ስለምንፈጥርናይህም ቆሻሻ ብክለትን ስለሚያስከትል፣ በአግባቡ የመያዝ ሀላፍነት አለብን፡፡ የቆሻሻ አያያዝ በአራት ደረጃዎች ይካሄዳል፡፡ ይክም የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ ይባላል፡፡ የመጀመሪያዉ ደረጃ እንዱስተሪዎች በተቻለ መጠን አነስተኛ ቆሻሻ የሚፈጠርበትን የአመራረት ሂደት መከተላቸዉ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ እርምጃ ተመልሶ ጥቅም ላይ ሊዉል የሚችለዉን ማንኛዉንም ነገር ከቆሻሻ መለየት ነዉ፡፡ ይህ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ወይም ሀብት እንዲያገግም ማድረግ  ይባላል፡፡ ሶስተኛዉ እርምጃ እያንዳንዱን የቆሻሻ አይነት አነስተኛ ቦታ እንዲይዝ አደርጎ ማጨቅ እና ጉዳቱ እንዲቀንስ ማጣራት ነዉ፡፡ አራተኛዉ እርምጃ ከላይ የተጠቀሱት ተግባሮች ከተከናወኑ በኋላ የሚቀረዉን ማንኛዉንም ቆሻሻ በአግባቡ ተጠንቶ ወደ ተሰራ የቆሻሻ መጣያ ወስዶ መጣል ነዉ፡፡

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ቆሻሻን ከምንጩ ጀምሮ እስከሚወገድበት ስፍራ ድረስ የሚደረግ ክንዉን፣ ቆሻሻን ከምንጬ እስከ መቀበሪያዉ የመቆጣጠር መርሆ ይባላል፡፡ ይህንን

መርሆ በመተግበር የምናልመዉን ንጹህ አከባቢ መፍጠር ፋይዳዉ ብዙ ነዉና ዛሬዉኑ ለተግባር እንነሳ፡፡

*(ተፈጥሮ መጽሄት፣ የካቲት 1997፣ ማሻሻያ ተደርጎበት የቀረበ)*

**ትእዛዝ አንድ፡-** ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ በመምረጥ የመልሱን ፊደል ብቻ በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፍ/ፊ። (9%)

---------------------1. ተዝረክርኮ ሀ.ተጠራቅሞ ለ.ተበትኖ ሐ. ተወገደ መ. ሁሉም

---------------------2. ማጨቅ ሀ.መወተፍ ለ. መለየት ሐ. መስቀል መ. መምታት

---------------------3. ብክለት ሀ.ማሳመር ለ.ማጽዳት ሐ.መመረዝ መ.አይታወቅም

ትእዛዝ ሁለት፡- በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ሀሳብ የሚያስተላልፉትን እዉነት ስህተት የሆነዉን ሀሰት በማለት መልሱ (9%)

4. ቆሻሻን የትም በየቦታዉ መጣል ለአፈርና ዉሃ ብክለት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

5. መርዛማ ኬሚካሎች አየርና ዉሃን ቢበክሉም በተፈጠሮ ሀብት ላይ የሚየመጡት ተጽእኖ የለም፡፡

6. በአነስተኛ ቦታ ለጊዜዉ ቆሻሻን አችቆ ማቆየት ጉዳትን ይቀንሳል፡፡

ትዕዛዝ ሦስት ፡- በምንባቡ መሠረት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጽሁፍ ግለጽ/ጪ፡፡(12%)

7. ስለ ቆሻሻ ትክክል ያልሆነዉ? ሀ. የእንዱስተሪ ፍሳሽ ለ. በየቦታዉ የተጣለ ደረቅ ቆሻሻ ሐ. ቁርጥራጭ ወረቀት መ. አልተመለሰም

8. ቆሻሻ የሚያስከትለዉን ጉዳት የሚገልጸዉ አንቀጽ የትኛዉ ነዉ፡፡ ሀ.የመጀመሪያዉ ለ. ሁለተባዉ ሐ.የመጨረሻዉ መ. አልተመለሰም

9. የቆሻሻ አያያዝ ደረጃዎች ስንት ናቸዉ? ሀ.አራት ለ. ሁለት ሐ. ሶስት መ.ሁሉም

10. የቆሻሻን ብክለት ለመቀነስ? ሀ/ማጠራቀሚያ መስራት ለ. ቅንጅት መፍጠር ሐ. አያዝ ማሻሻል መ/ሁሉም

## ምንባብ 2

ከሰላሳ አመት በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር 19 ሚሊዮን ነበር። የህዝቡ ቁጥር ከ1950ዎቹ ጀምሮ በ1.9 በመቶ አደገ፤ በ1980 መገባደጃ ወደ 3.0 በመቶ፣ ከ1986 ወዲህ ደግሞ ወደ 3.2 በመቶ አሻቀበ። በዚህ አካሄድ ከ20 ዓመታት በኋላም የዚህን እጥፍ ሊሆን እንደሚችል ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የተገለጹት ቀደምት ቆጠራዎችና የመጪዎቹ ዓመታት ስሌቶች እንደሚጠቁሙት ከአስራ አምስት አመታት በታች ያሉት ታዳጊ ህፃናት በቁጥር የህዝቡን 50 በመቶ ይሆናሉ። እርግጥ ነው ህዝብ በህዝብነቱ ሀገር ያፈራውን ሁሉ ተካፍሎ ሊኖር ይገባዋል። ይህ ደግሞ ተግባራዊ እንዲሆን በሁሉም ዘርፍ ምጣኔ ያስፈልጋል፤ ዳሩ ይህን ምጣኔ የሚፈታተነው የመዋለ ፍጥነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱ ነው። ይህ ሸቅብ ጉዞ በአጠቃላዩ የእድገት ሂደት ላይ ጥገኝነትን ፈጥሮ ልማት እንዳይፋጠን በማድረግ የአገር ሀብትን ያቆረቁዛል።

የህዝብ ቁጥር መጨመር የፍጆታ ፍላጎትን ስለሚያሳድግ በቋሚ ልማት ላይ ሊውል የሚገባው መዋዕለ ንዋይ በአስተማማኝ ልማት ላይ ሳይሆን በምግብ አቅርቦት፣ በመጠለያ፣ በጤና፣ በትምህርት፣ ወዘተ ላይ ይውላል፤ ይህ ድግሞ ምርታማነትን በመቀነስ የህዝቡ ዓመታዊ የነብስ ወከፍ ገቢ እንዲያሽቆለቁል ያደርገዋል።

የህዝብ ቁጥር ጨምሮ ስራ ሊፈጥር የሚችል ኢኮኖሚ ሲታጣ፣ ሊያመርት የሚችልን ግን ደግሞ የሚያመርተውን ያጣ ህዝብ ያበዛል። ይህም የስራ አጡን ቁጥር ያበረክታል። ከዚሁ ጎን ለጎን ትምህርትን ስንመለከት ለመማር ፈላጊውን በየጊዜው ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ እየበዛ ይመጣል። የተማሪዎች ቁጥር መጨመር ለትምህርት የሚወጣውን ገንዘብ ያበረክተዋል፤ የትምህርትንም ጥራት ያዘቅጠዋል።

(ለተማሪው መማሪያ መፅሀፍ፤ በሚያመች መልኩ ተስተካክሎ የተወሰደ1997)

ትዕዛዝ አንድ፡ - ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ በመምረጥ የመልሱን ፊደል ብቻ በተሰጠው ክፍት ቦታ ፃፍ/ፊ። (9%)

-----------1. አሻቀበ ሀ/ ባከነ ለ/ ጨመረ ሐ/ አንጋጠጠ መ/ አቀና

----------2. ነፍስ ወከፍ ሀ/ቡድን ለ/ ጀምላ ሐ/ አንዳንድ መ/ ሞኝድ

------------3. ሀገር ያፈራውን ሀ/ የሀገር ፍቅር ለ/ ከሀገር የወጣ ሐ/ ከሀገር የተገኘውን መ/ ከሀገር የተሸሸ

ትእዛዝ ሁለት፡- በምንባቡ መሰረት ቃላትና ሀረጋቱ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ ምረጡ(9%)

4. ስሌት ሀ.ጥሎሽ ለ.ግምት ሐ.ብዛት መ.አልተመለሰም

5. ሽቅብ ጉዞ ሀ. እየቀነሰ መሄድ ለ.ባለበት መቆየት ሐ. እየጨመረ መሄድ ሐ. ሁሉም ናቸዉ

6. መዋለ ንዋይ ሀ. ገንዘብ ለ. ሸቀጥ ሐ. ቀረጥ መ. አልተመለሰም

ትእዛዝ ሶስት፡- በምንባቡ መሠረት የጥያቄዎቹን ትክክለኛ መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጽሁፍግለጽ/ጭ።(12%)

7. ልማት እንዳይፋጠን ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው? ሀ. የህዝብ ብዛት መቀነስለ ለ. የህዝብ ብዛት መጨምር ሐ. ሁለቱም መ. አልተመለሰ

8. በህዝቡ ላይ የፍጆታ ፍላጎት መጨመር የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? ሀ.የዋጋ ንረት ለ. የዋጋ መቀነስ ሐ. የአገልግሎት መሻሻል መ. ሁሉም

9. የአራተኛው አንቀጽ የሚገልጸዉ ሀ. የኢኮኖሚ እድገት ለ. የትምህርት ጥራት መጓደል ሐ. የትምህርት ጥራት መጠበቅ ሐ. ሁለቱም መ. አይታወቅም

10. የህዝብ ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ያደረገው ምንድን ነው? ሀ.ትምህርት ለ.ሀብት ሐ. የምጣኔ ትግበራ ችግር መ. ሁሉም

አባሪ ተ፡የትብብራዊ መማር ዘዴ ትግበራ ስልጠና የተዘጋጀ ማንዋል

## ክፍል አንድ

### 1.1 መግቢያ

የዚህ ጥናት ዓላማ ትብብራዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረዉን ሚና መመርመር ነው፡፡ ትብብራዊ መማር ደግሞ ዝም ተብሎ የሚተገበር ሳይሆን መምህራን ይህን ዘዴ ለመተግበር ስለምንነቱና አተገባብሩ በቂ የሆኔ ግንዛቤና ስልጠና ሊወስዱ ይገባል፡፡(በOunnan1992፤Johonson&Johnason (1999) መሰረት ትብብራዊ መማርና አተገባበሩን በሚመለከት ከስድስት ሰዓታት ያላነሰ ስልጠና እንደሚያስፈልግ ስለሚገልጽ የማሰልጠኛ ማንዋሉን ለማዘጋጀት አጥኚዉ ትብብራዊ መማርን አስመልክቶ ተዛማጅ ፅሁፎች ዳሰሳ ውስጥ ከተዘረዘሩ ይዘቶች በመነሳትና ርዕስ ጉዳዩን አስመልክቶ Johnson & Johnson (1990) እና ሌሎች የመስኩ ምሁራን የጻፏቸውን መርሆችን መሠረት በማድረግ የተሰሩ ጽሁፎችን በመጠቀም አዘጋጅቷል፡፡ የስልጠናው ማንዋል አራት ክፍሎችን የያዘ ነዉ፡፡ በማንዋሉ ውስጥ የተካተቱት የስልጠናው ዋና ዋና ይዘቶች የትብብራዊ መማር ምንነት፣ የትብብራዊ መማር ጥቅሞች፣ ትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆች፣ ትብብራዊ መማር ስልቶች፣ በትብብራዊ መማር የተማሪዎችና የመምህራን ሚና፣ ትብብራዊ መማርና በተለምዶ (ቡድን) መማር መካከል ያለው ልዩነት የሚሉ ሀሳቦችና የተማሪዎች የግልና የቡድን ፅብረቃ ማድረጊያ ቅፆች የተካተቱበት የስልጠና ማንዋል ነው፡፡

ጥናቱ ሙከራዊ ጥናት በመሆኑ የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን ለማስተማር ለሚመረጠው መምህር ከላይ የተብራሩ የማኑዋሉ ይዘቶች ስለ ትብብራዊ መማር ምንነት፣ ትብብራዊ መማር ዘዴ ጥቅሞች፣ ትብብራዊ መማር ዘዴ መሰረ.ታዊ መርሆች፣ ትብብራዊ መማር ዘዴ ስልቶች፣ በትብብራዊ መማር የተማሪዎችና የመምህራን ሚና ፤የትብብራዊ መማርና በግል መማር ያላቸውን ልዩነቶች የሚሉ ሀሳቦችና የትብብራዊ መማርና አተገባብር ዙሪያ ባሉት ሁኔታዎች ላይ ስልጠና ይሰጠዋል፡፡ ስልጠናዉን መሰረት በማድረግም መምህሩ የሙከራ ቡድን ትምህርቱን በትብብራዌ መማር ይመራል የሚፈለጉ ሁኔታዎችን ይተገብራል፡፡ ለዚህም አጥኚዉ ወደ ሙከራ ጥናቱ ከመግባቱ በፊት ስለ አጠቃላይ የሙከራ ቡድንና ትግበራን በሚመለከከት ስልጠናዉ ተዘጋጅተዋል፡፡

## 1.2 ለስልጠናዉ አስፈላጊ መመሪያ

ስለምርምር ሲነሳ በአካሄዱ ዙሪያ የሚፈለጉ ስነምግባሮችን መለየትና ማወቅና መተግበር አስፈላጊ ነዉ፡፡ ከነዚህም ስነምግባሮች መካከልም ዋነኛው የተሳታፊውን ስምምነትና ይሁንታ ማግኘት ነው፡፡ ይህ ሙከራዊ ጥናት በተሳካ ሁኔታ ይከናወን ዘንድ በአጥኚዉ የቀረበዉን ጥያቄ ወይም ሀሳብ በመቀበል ስልጠናውን ለማካሄድ ፈቃደኛ መሆን ለጥናቱ መጠናከር ወሳኝነት ስላለው አጥኚዉ የሚሰማዉን አክብሮት ከወዲሁ ይገልጻል፡፡

የዚህ ስልጠና ዋና ዓለማ የትብብራዊ መማር ምንነትን፣ ትብብራዊ መማር ጥቅሞች፣ ትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆች፣ ትብብራዊ መማር ስልቶች፣ ትበብብራዊ መማር የተማሪዎችና የመምህራን ሚና፣ በትብብራዊ መማርና በቡድን መማር መካከል ስላለው ልዩነትና ስለ አተገባበሩ ሀሳብና መረጃ በመለዋወጥ ግንዛቤን ማስጨበጥ ነው፡፡ ይህ የማሰልጠኛ ማንዋል ጽሁፍ የተዘጋጀው ትብብራዊ መማርን አስመልክቶ Gohith(2003) ፣ ዓለማየሁ (2009) እና የተለያዩ የመስኩ ባለሙያዎች የፃፏቸውን ፅሁፎች መሠረት በማድረግ ነዉ፡፡ የስልጠናው ዋነኛ ዓላማ ለሰልጣኙ ስልጠና ከተሰለጠነ በኋላ ሙከራዊ ቡድን ሆኖ ለሚመረጠው ክፍል የማንበብ ክሂል በማስተማር ትግበራ ጊዜ ዘዴው በተሳካ ሁኔታ እንዲተገበር ለማስቻል የመምህሩ ንቁ ተሳትፎና ፍላጎት ጉሊህ ሚና ይኖረዋል፡፡

## 1.3 ለስልጠናዉ የተመደበ ጊዜ

በስልጠናው ወቅት ለእያንዳንዱ ርእስና የስልጠናይዘት የተመደበው ጊዜ መጠን በሚከተለው ሁኔታ ተቀምጠለታል፡፡

| ተ.ቁ | ይዘት | የተመደበ ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የትብብራዊ መማር ምንነት | 40 ደቂቃ |
| 2 | የትብብራዊ መማር ጥቅም | 40 ደቂቃ |
| 3 | የትብብራዊ መማር መሠረታዊ መረሆች | 50 ደቂቃ |
| 4 | የትብብራዊ መማር ስልቶች | 40 ደቂቃ |
| 5 | በትብብራዊ መማር የተማሪዎችንና የመምህራን ሚና | 30 ደቂቃ |
| 6 | ትብብራዊ መማርና በተለምዶ ቡድን መማር መካከል ያለው ልዩነት | 30 ደቂቃ |
| 7 | ለትግበራዉ መከናወን የሚኖሩት ቅደም ተከተሎች | 50 ደቂቃ |

## 1.4 የስልጠናው ዓላማዎች

የዚህ ስልጠና ዋነኛዉ ዓላማ ሙከራዊ ቡድኑን ለሚያስተምረው መምህር ስለ ትብብራዊ መማር አተገባበሩ አጠቃላይ የሆነ ግንዛቤን በማስጨበጥ ጥናቱ እንዲሳካ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ስልጠናው ሲጠናቀቅ ሰልጣኙ መምህር

- ስለ ትብብራዊ መማር ምንነት ይገልፃል
- ትብብራዊ መማር ጥቅሞችን ይገነዘባል
- በትብብራዊ መማርና በተለምዶ(ቡድን) መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራል
- የትብብራዊ መማር መሠረታዊ መርሆች ይገልፃል
- በትብብራዊ መማር የተማሪዎችንና የመምህራን ሚና በመለየት ይዘረዝራል
- የትብብር መማር የክፍል ዉስጥ አተገባበር ቅደም ተከተሎችን ይለያል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 3.1 የተማሪዎች የራስን ተሳትፎ መገምገሚያ ቅፅ

ውድ ተማሪ! ከዚህ በታች  በትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ በትብብራዊ ቡድን የነበረውን ግላዊ ተሳትፎ በተመለከተ የግል ግምገማ የምትገማገሙባቸው ጥያቄዎች የቀረቡ በመሆኑ ጥያቄዎቹን ካነበብክ/ሽ በኋላ ከቀረቡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ አመልክት/አመልክቺ

| ቁጥር | ጥያቄ | ሁልጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | በፍጹም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በትብብር መማር ከልብ የሆነ የመረዳዳት ስሜት ፈጥሮልኛል | | | |
| 2 | ከቡድኑ የተረዳሁትና ያለኝን መረጃ ለጓደኞቸ አካፍያለሁ | | | |
| 3 | የተማርኩትን ትምህርት ማጠቃለል ችያለሁ | | | |
| 4 | በቡድናችን ውስጥ ያሉትን እያንዳንዱ አባላት የተሠጠንን ስራ መስራታቸውን አረጋግጣለሁ | | | |
| 5 | የተማርኩትን ትምህርት በሚገባ ተረድቻለሁ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | የተለያዩ መረጃዎችን በማስታወሻ በመያዝ የቡድን አባላቶችን ማስረዳት ችያለሁ | | | |
| 7 | በቡድናችን የተሠጠውን ሥራ ትኩረት አድርጌ እንዲሠራ አደርጋለሁ | | | |

### 3.2 የቡድን አባላት መገምገሚያ ቅጽ፡

ውድ የቡድን አባላት! ከዚህ በታች ቡድናችሁ በትብብራዊ መማር ሂደት የነበረውን አጠቃላይ ተሳትፎ በተመለከተ የምትገመግሙባቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል እና ጥያቄዎችን በማንበብ ከቀረቡት አማራጮች መካከል አንዱን ምረጡ

| ቁጥር | ጥያቄ | ሁልጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | በፍጹም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አብሮ መማር በስምና በመልኩ ከመተዋወቅ ባለፈ ጠንካራ አዎንታዊ ግንኙነት ፈጥሯል | | | |
| 2 | በቡድናችን የያዝነውን ማስታወሻ ለሌሎች ቡድን አባላት ማካፈል ችለናል | | | |
| 3 | ሁላችንም ከልብ የሆነ የመረዳዳት ስሜት ፈጥሮብናል | | | |
| 4 | በአንድ ላይ በውይይት ያጠናከርነውን ለቡድን አባሎቻችን እንናገራለን | | | |
| 5 | በቡድናችን ውስጥ ጥያቄዎችን ወይም መልሶችን መገንዘብ ካልቻልን በጋራ ሆነን ሀሳቡን ግልፅ ለማድረግ እንሞክራለን | | | |

አባሪ፡ቸ ለሙከራ ቡድኑ መማሪያ የተዘጋጀ የትምህርት እቅድ

የትምህርት ቤቱ ስም ፡- ሲግሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ት/ቤት የመምህርቷ ስም ፡ -______________________________

የትምህርቱ አይነት ፡- አማርኛ

ክፍልና ሴክሽን 10 ኛ G

የትምህርቱ ርዕስ፡- ምንባብ________________________________

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ፡- 45 ደቂቃ

ቀን _______________________

ስለ ትምህርቱ አጭር መግለጫ

የትብብራዊ ቡድን አባላቱ በትብብር መማር አመካይነት "የሴቷ መንገድ" የሚለዉን ምንባብ በቡድናቸዉ በጮክታ በማንበብ ከዛም ምንባቡን መሰረት በማድረግ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በትብብራዊ ቡድናቸዉ አመካይነት ይሰራሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች

1. ትምህርታዊ ዓላማዎች ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ስለ ምንባቡ መልእክት ለመገንዘብ በጮክታ ተራ በተራ ያነባሉ፣ ለሚከሰቱ የአነባብ ስህተቶች እርማት ያደርጋሉ፣ በዋና ዋና ሀሳብና ዝዝር ሀሳብ በመለየት ይወያያሉ፡፡ የውይይታቸውን ሀሳብ ለቡድን አባሎቻቸውና ለሌሎች ቡድኖች ያካፋላሉ፡፡ የንባብ ደረጃዎችን ተጠቅመዉ የተሰጣቸዉን ስራ ይፈጽማሉ፡፡

2. ትብበራዊ ዓላማዎች፡- ሚናዎችን በቡድናቸዉ በመከፋፈል የስራ ድርሻቸውን ይለያሉ የሚጠበቅባቸዉን ይወጣሉ፡፡

ከተማሪዎች የሚጠበቁ ባህሪያት

- እርስ በዕርስ በመረዳዳት ሂደት ከአንድ ቡድን ወደ ሌላ ሄዶ አለመረበሽ
- ከመምህራቸው ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር

- እርስ በርስ መረዳዳት

ወሳኔዎች

በቡድን ውስጥ ያባላት ብዛት ፡- በአንድ ቡድን 4-6 ተማሪዎች ይኖራሉ ተማሪዎች እያንዳንዱ ተማሪ ውጤት መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የሚያስፈልጉ የትምህርት ቁሳቁሶች ፡- የተዘጋጀ ማስተማሪያ፣ ጥቁር ሰሌዳ

የተማሪዎች ሚና፡- በእያንዳንዱ ቡድን የሚከተሉትን ሚናዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉ አባላት ሊኖሩት ይገባል የቡድኑ አባላት ስራዎችን መከፋፈላቸውን የሚከታተልና ቡድኑን

- በበላይ ሆኖ የሚመራው **መሪ**፣
- የቡድኑን ሀሳብና ውሣኔ የሚጽፍና ሪፖርት የሚያጠናክር **ዘጋቢ** ፣
- ተማሪዎች በየትብብራዊ ቡድናቸው በመሆን የተወያዩትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው የሚያሰማ **አቅራቢ**፣
- እያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠውን የስራ ድርሻ ማከናወኑና አለማከናወኑን የሚከታተል አረጋጋጭ
- አባላቱ ለሚያከናውኑት ተግባር ተገቢውን የሀሳብ ማበረታቻ እየሰጠ የበኩላቸውን አስታዋጾ እንዲሚያበረክቱ የሚያነቃቃ **አበረታች**
- ለቡድነ ውይይት ተግባሩ የተመደበውን ሰዓት የሚከታተል ጊዜ **ተቆጣጣሪ**

በትምህርት አቀራርብ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት

ቅድመ ንባብ

መምህሩ የትምህርቱን ዓላማና በትምህርቱ መጨረሻ የሚጠበቀውን ባህሪ ይነግራል፤ የእለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋውቃል፤ ስለ ንባብ መንደርደሪያ ትንበያና የሃሳቡ ምንነት ተማሪዎችን በየቡድናቸው እንዲወያዩ ያደርጋል፤ በውጤታቸው ወቅት ግልጽ ያልሆነላቸው ሀሳብ ካለ በመቀበል ምላሽ ይሰጣል፤ የቀረበውን ጽሁፍ መሠረት በማድረግ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው በማስረዳት የአሰራር መመሪያዎችን ያስተላልፋል፡፡ ተማሪዎቹም የትምህርቱን ዓላማና መጨረሻ የሚጠበቅባቸውን ባህሪ ይለያሉ፤ የእለቱን ትምህርት ርዕስ ያገናዝባሉ፤ ስለ ንባብ መልእክት ትንበያ በየቡድናቸው ይወያያሉ፤ በውይይታቸውም ወቅት ግልጽ

ያልሆነላቸው ሃሳብ ካለ ይጠይቃሉ፤ ስለ ንባብ የቀረበውን ጽሁፍ መሠረት በማድረግ ማንበብ እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡

**የንባብ ጊዜ**

መምህሩ ስለ እለቱ ትምህር የሰጣቸውን ሀሳብ መሠረት በማድረግ በመጀመሪያ በጋራ እንዲያነቡ ያደርጋል፤ በቡድናቸዉ በተራ ያነባሉ፣ ሲያነቡ ስህተት ቢፈጠር ይተረራማሉ፣ በመቀጠል በሁለት ሁለት ተከፍለዉ እንዲገማገሙ እንዲያሳዩ ያደርጋል፤ ሁሉም ተማሪዎች የደረሱበት የንባብ አቅም በአንድ ላይ በቡድናቸው በውይይት እንዲያጠናክሩ ያደርጋል፤ በመቀጠልም ከሌላ ቡድን ጋር በመቀያየር እንዲተራሩሙ ያደርጋል በግልጽ እንዲያመለክቱ ያደርጋል፡፡

**ድህረ ንባብ**

በዚህ ክፍል ለግምገማ የሚዘጋጁ መልመጃዎችን መምህሩ በቡድን ተግባራቸውን እንዲገመግሙ ያደርጋል፤ ተማሪዎች ስለ ሰሯቸው ስራዎች ግብረመልስ ይሰጣል፤ ተማሪዎችም ተግባራቸውን ይገመግማሉ፤ ግብረ መልስ ይቀበላሉ፡፡

# ክፍል ሶስት

## 4.1.የትብብር መማር የክፍል ዉስጥ ቅደም ተከተላዊ ስራዎች

ቡድን መመስረት፡- ቡድን መመስረት የተለያዩ ስራዎችን በዉስጡ የያዘ ሲሆን ተግባሮቹም መምህሩ የተማሪዎችን የስብጥር ሁኔታ ከግምት ማስገባት፣ የጾታ፣ የችሎታ፣ የአባላት ቁጥር የቆይታ ጊዜ የስራ ክፍፍሎችን ጭምር ጥንቃቄ በማድረግ መከናወን ይኖርበታል፡፡

የክፍል አደረጃጀት፡- ተማሪዎች በቡድኖቻቸዉ ሆነዉ ሲሰሩ መምህሩ በቀላል እየተንቀሳቀሰ ለመቆጣጠር እንዲያመች ተደርገዉ ክፈሉ መመቻቸት አለበት፣ ተማሪዎቹ ፊት ለፊት እየተያዩ በመወያየት እንዲሰሩ መቀመጫቸዉ መመቻቸት አለበት፣ ይህም ይበልጥ ተቀራርበዉ ቁሳቁሶችን እየተዋዋሱ አብረዉ እንዲሰሩ የሚረዳቸዉ ሁኔታ ስለሆነ ይበልጥ ተጠቃሚ መሆኑን ከድርሳናት መረዳት ይቻላል፡፡

የተማሪዎችን የሚና ክፍፍል ማካሄድ፡- በትብብር መማር ወቅት ተማሪዎች በየጊዜዉ የሚቀያየሩባቸዉ ሚናዎች እንዲከፋፈሉ ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡ እነዚህም መሪ፣ ዘጋቢ፣ ተቆጣጣሪ፣ ታዛቢና የመሳሰሉትን ድረሻዎች መከፋፈል አለባቸዉ፡፡ ይህ ሚና መከፋፈል ትብብራዊ ክህሎችን የማስተማርና አዎንታዊ ተደጋጋፍነትን የማሳለጥ ሁኔታን የሚረዳ መሆኑን ምሁራኑ ይገልጻሉ፡፡

ከተማሪዎች የሚጠበቁ ባህሪያትን መግለጽ፡- በትብብር መማር ጊዜ ለተማሪዎቹ የሚጠበቅባቸዉን ባሂሪ ማሳወቅ ለስራዉ ስኬት አጋዥ ይሆናል፡፡ እነዚህም ባህሪያት

- በቡድናቸዉ ሆነዉ ስራዎችን እንዲሰሩ እኩል ተሳትፎ ማድረግ
- ድምጻቸዉ ሌሎችን እንዳይረብሽ ማድረግ
- ተራ በተራ በመነጋገር በመወያየት እንዳለባቸዉ ማሳወቅ
- እርስበርስ መረዳዳት እንዳለባቸዉ ማረጋገጥና ወዘተ.ናቸዉ

በትብብራዊ ቡድኑ አዎንታዊ ተደጋጋፊነት እንዲኖር የማድረጊያ ዘዴ፡- በቡድን አባላት መካከል አዎንታዊ ተደጋጋፊነት እንዲኖር ሁሉም ተማሪዎች በየትብብራዊ ቡድኖቻቸው አንዱ ሌላውን በማገዝ መስራት እንዳለባቸው መንገርና በትብብር በሚሰሩበት ጊዜም አዎንታዊ ተደጋጋፊነታቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የቡድን አባል የተስማሙባቸው ለሁሉም ጥያቄዎች መልሶችን ለመፈለግ መተግበር

በትብብራዊ ቡድኑ ግለሰባዊ ተጠያቂነት እንዲኖር የማድረጊያ ዘዴ፡- ለሁሉም የንባብ ክሂል ጥያቄዎች መልሶችን የቡድን አባሎቻቸው በደብተሮቻቸው ላይ እንዲጽፉና በንባብ እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ሀላፊነት አለባቸው እንዲሁም መልሶችን እንዲመልሱ የማድረግ ሀላፊነት አለባቸው ለመልሶቹ ለምን የሚል ጥያቄ ቢጠየቁ ምክንያታዊ ሆነው መመለስ መቻል አለባቸው፡፡ በመልሶቹ ዙሪያ መግባበት መፈጠሩን ማረጋገጥ፡፡

የስኬት መስፈርት መግለጽ፡- ሁሉም የቡድን አባላት ውጤታማ የሚሆኑት የቀረበላቸውን የንባብ ችሎታ መገምገሚያ መልመጃዎችን በትክክል በመተግበር፣ በመረዳት ከሰሩ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ለመለሷቸው መልሶች እጅግ በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ጥሩ በማለት ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

መከታተልና ጣልቃ መግባት፡- ተማሪዎች በቡድን ሆነው የተሰጣቸውን የማንበብ ችሎታ ተግባራት በሚሰሩበት ጊዜ ተግባራቱን ምን ያክል እየሰሩ ወይም እያከናወኑ እንዳሉ መከታተል ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ጣልቃ በሚገቡበት ጊዜም ችግሩን መለየትና ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሀሳብ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

የአባሪ፡ ነ የማስተማሪያ ጽሁፍ

ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን ችሎታ ለማሻሻል የሚኖረዉ ሚና ፍተሻ በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ጽሁፍ፡፡

## ትምህርት አንድ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1.ስለ ባህል ምንነት ግለጹ?

2.የሴቶችና የባህል ግንኙነት እንዴት ይገለጻል?

3.በአከባቢያችዉ ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጂ ባህሎችን ተናገሩ?

4.እንዝህን ጎጂ ባህሎች ለማስወገድ መፍትሄዉ ምን ይመስላችዋል?

## “የሴቱዋ መንገድ”

ባህል ሰፊና ብዙ ጉዳዮችን የሚያካትት ማእቀፍ ነዉ፡፡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጉዳዮችም አሉት፡ ፡ ባህል አንድ ማህበራዊ ቡድን የሚገለገልባቸዉ ቁሶችን እንዲሁም ማህበራዊ መተዳደሪያ ደንቦችን ያጠቃልላል፡፡ በዚህም ዉስጥ አስተሳሰቦች፣ ጥበቦች፣ እምነቶች፣ ልማዶች ይነሳሉ፡፡ እነዚህ በሰዉ ልጅ አከባቢያዊ እዉቀት ላይ የተመሰረቱ ፈጠራዎች በዘልማድ በማህበረሰቡ እየተተገበሩ ለዘመናት ቆይተዉ የአኗኗር ዘይቤዉ ይሆናሉ፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች ለመልካም ብለዉ የሚተገብሩዋቸዉ ልማዳዊ ድርጊቶች አንዳንድ ጊዜ ከጥቅማቸዉ ይልቅ ጉዳታቸዉ ሲያመዝን ይታያል፡፡ በተለይ በሴቶች ላይ ሲፈጸሙ የኖሩት አንዳንድ ልማዳዊ ድርጊቶች ሴቶች ለረዥም ዘመናት የጨለማ ህይወትን እንዲገፉ ያስገደዱዋቸዉ ነበሩ፡፡ ለአብነትም ያክል የሴት ልጅ ብልት ትልተላ፣ ጠለፋ፣ የዉርስ

ጋብቻ፣ ሴትን ልጅ በማጀት ዉስጥ ብቻ ወስኖ ማስቀመጥን… መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ጎጂ ልማዶች ሴቶችን ለከፋ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት እየዳረጉ ዘመናት አስቆጥሯል፡፤ የሚገርመዉ ግን ድርጊቶቹ ቀጣይነት እንዲኖራቸዉና ለትዉልድ እንዲተላለፉ የሴቶቹ ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ ሴቶች በባህል ስም የሚፈጸምባቸዉን ጎጂ ድርጊቶች በዝምታ ተቀብለዉና ጉዳታቸዉን በዉስጣቸዉ አምቀዉ፤ የድርጊቶቹን አስፈላጊነት ለልጆቻቸዉ እየሰበኩ ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ያላቸዉን ክብርና ታማኝነት ያሳያሉ፡፡

ከዚህ በተቃራኒ እነዚህ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በመቃወም አንገታቸዉን ቀና አደርገዉ ሽንጣቸዉን ገትረዉ የሚሟገቱ ጥቂት ደፋር ሴቶችም አልታጡም፡፡ ወደዚህ አስቸጋሪና ዉስብስብ ትግል ገብተዉ ድልን ከተቀዳጁ ትቂት ጀግና ሴቶች መካከል የአንዷዋን ተሞክሮ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**ተማሪዎች ካነበባችሁት አንቀጾች ምንተረዳችሁ? የሚቀጥሉት አንቀጾች በበለጠ በምን ጉዳይ ላይ ያተኩራል ብላችሁ ትገምታላችሁ?**

ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ “ሴት ልጅ አደባባይ ልትዉል አይገባትም“ በሚባልበት ዘመን ተፈጥረዉ፤ የባህሉን ጫና በጥረትና በትጋት አልፈዉ ለስኬት የበቁ ኢትዮጵያዊት ናቸዉ፡፡ የኚህ ጠንካራ ሴት መንገድ ምን ይመስል ነበር?

ቦጋለች (የአከባቢዋ ሰዎች እንደሚጠሯት ቦጌ) የተወሰደችዉ ከአድስ አበባ 325 ኪ.ሜ በስተደቡብ ምእራብ የከንባታ ጠንባሮ ዞን ‘ዛቶ‘ በተባለች ትንሽ መንደር ነዉ፡፡ ቦጌ በተወለደችበት ዘመን በዛቶ የትኛዋም ሴት ወደ ትምህርት ቤት እንድትሄድ አይፈቀድላትም፡፡ ሴት ልጅ ከማጀት ጉዳዮች አልፋ ለትልቅ ቁምነገር ትደርሳለች ተብሎ በማህረሰቡ አይታሰብም፡፡ ይልቁንም ሴቶችን የሚጫኑ ልዩ ልዩ ጎጂ ልማዶች የሚከወኑበት በተለይ የሴት ልጅ ግርዛት በእጅጉ ተስፋፍቶ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡

የትንሽዋ ቦጌ መንገድ ግን የተለየ ነበር፡፡ ከቢጤዎቿ ፈጥና የነቃችዉ ቦጌ ወደ አጎቱዋ ቤት ጎራ እያለች ፍደል ከቆጠሩ ዘመዶቿ ፍደል ለየች፣ ማንበብና መጻፍ ቻለች፡፡ የቤት ዉስጥ ስራዋን ካጠናቀቀች በኋላ ቤትዉስጥ ለምግብ ማብሰያ በሚቀጣጠለዉ እንጨት ብርሀን ሥራዬ ብላ ጥናቱዋን ተያያዘችዉ፡፡ ትጋቷን የተመለከቱ አባቷ ትምህርት ቤት እንድትሄድ ፈቀዱላት፡፡ በቀን እስከ 6 ማይል ርቀት በእግሯ እተጓዘች ትምህርቷን ቀጠለች፡፡ በግምት የዘጠኝ አመት ልጅ ስትሆን አራተኛ ክፍልን አጠናቅቃ ወደ አምስተኛ ክፍል ገባች፡፡ ይህም በመንደሯ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአራተኛ ክፍል በላይ የደረሰች ሴት አደረጋት፡፡

በተማረቻት እዉቀት ለአባቷና ለመንደሯ ሰዎች ማመልከቻ በመጻፍ በቀናነቷ የተመሰገነችና የታወቀች ሆነች፡፡ ይህም አንድ ማእረግ አሰጣት፡፡ በከምባታ ባህል አባት ለክብሩ መግለጫ የሚጠራዉ የመጀመሪያ ወንድ ልጁ ሲሆን እናት የሚትጠራዉ ደግሞ በመጀመሪያ ሴት ልጇን ነበር፡፡ ቦጌ ግን ነገሩን የተገላብጦሽ እንዲሆን አደረገች፡፡ የአከባቢዉ ሰዉ አባቷን በሷ ስም "የቦጋለች አባት" እያለ መጥራት ጀመረ፡፡

ቦጌ ትምህርቷን ለመከታተል ወደ አድስ አበባ ከመጣች ቦኋላ ባገኘችዉ የነጻ ትምህርት እድል ወደ አስራኤል ሀገር ተጓዘች፡፡ እሰራኤል ሀገር ስትማር ከሚከፈላት የኪስ ገንዘብ በመቆጠብ ወደሀገሯ በመመለስ ለአባቷ በዛቶ መንደር የመጀመሪያ የተባለ የቆርቆሮ ቤት ሠራች፡፡ ቦጌ በአከባቢዋ አሁንም አስደናቂ የአስተሳሰብ ለዉጥ እንዲመጣ ምክንያት ሆነች፡፡ ቤቱን ከሩቅም ከቅርብም ሰዎች እየመጡ ጎበኙት፤ "ሴት ልጅ እድሉን ካገኘች ለካ ቁም ነገር ትሰራለች"ተባለ፡፡ ባይጻፍም "ሴት ልጅ መደቧ ማጀት ነዉ" የሚለዉን ባህላዊ ህግ የሻረች የመጀመሪያዋ የከምባታ ወጣት ሆነች፡፡

ቦጌ በተለያዩ የዉጭ  ሀገራት በመዘዋወር ትምህርቷን ስትከታተል ቆይታ 'ኢፒዲሚዮሎጂ' በተባለ የትምህርት ዘርፍ የዶክተሬት ድግሪዋን ተቀበለች፡፡ በዉጭ ሀገራት ለ፳ ዓመታት ከቆየች በኋላ በትዉልድ አከባቢዋ ያሉትን ሴቶች ለማገዝ፣ በተለይ በሚፈጸሚባቸዉ ባህላዊ ልማዶች/ግርዛት/ ሳቢያ በተለያየ ሁኔታ በእጅጉ የሚጎዱ እህቶቿን ለመታደግ፣ "ምናልባትም አንዲት ሴት ልጅ እንኳ ከግርዛት ባድን" በሚል ተስፋ ወደ ኢትዮጵያ ጠቅልላ መጣች፡፡ እንደ ኤ.አ. በ1998 አከባቢ ከታናሽ እህቷ ፍቅርቴ ገብሬ ጋር በመሆን "ከንባቲ ሜንቲ ጌዝማ "ቶጼ (ከሜጌ)" የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት አቋቋሙ፡፡ "ሴት ልጅን መገረዝ ቆሻሻ ማስወገድ ነዉ" ብሎ ፍጹም ከሚያምነዉ የአከባቢዉ ማህበረሰብ እምነት ጋርም ፍት ለፍት መጋፈጥ ጀመሩ፡፡ ምንም እንኳ ፍቅርቴ ገብሬ ከዝህ ዓለም በሞት በመለየት በአሸሩ መንገድ ላይ ብትቀርም ቦጌ የእህቷን አላማ ጭምር አንግባ ወደ ትግሉ ገባች፤ ትግሉ ቀላል አልነበረም፡፡ ፍትም በመንደሯ ስመመልካም የነበረችዉ ቦጌ በትእግስትና በዘዴ የአከባቢዋን ማህበረሰብ እሷ ወደምትፈልገዉ መንገድ ማስገባት ቻለች፡፡ እንደ አዉሮፓዉያን አቆጣጠር በ2008 ዓ.ም ተጠንቶ ይፋ በሆነዉ የዩኔሰፍ ጥናት በአከባቢዉ 97% ያህል ግርዛት መቀነሱ ተገልጸዋል፡፡

በተለያዩ በጎ አድራጊ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚደገፉዉ ከምባቲ ሜንቲ ጌዝማ - ቶጼ (ከሜጌ) ያገኘዉ ድል በከምባታ አከባቢ ብቻ ላለመገደብ እየተንቀሳቀሰ ነዉ፡፡ በእናቶች

ጤና እና ስነተዋልዶ፣ በኤች አይቪ ኤድስ እና በአከባቢ ጥበቃ ዙሪያ ማህበረሰብን በማሳተፍ በርካታ ሽልማቶችንና ምስጋና አተርፏል፡፡

ቁርጠኝነት፣ የዓላማ ጽናት፣ ለሌሎች በጎ ለማድረግ እዉነተኛ ፍላጎት መኖር ይህችን ትንሽ ስራ ለወገኖቼ ለመስራት አብቅቶኛል በሚሉት ጠንካራዋ ሴት በተለይ ሴቶችን ከተለያዩ የባህል ተጽእኖዎች ለማዉጣትና ጤናማና ነጻ ማህበረሰብ ለመገንባት፣ ሰላማዊ እኩልነትን የሚያስብ ዜጋ መፈጠር አለበት ይላሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነዉ ማህበረሰቡን በማዳመጥና በማስተማር ነዉ ብለዉም ያምናሉ፡፡

*(ምንጭ"ከሜጌ" ቢሮ አድስ አበባ ቅርንጫፍ 2003ዓ.ም)*

## ትምህርት ሁለት

**2.ሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ ጥያቀዎችን በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነዉን እዉነት ትክክል ልሆነዉን ሀሰት በማለት መልስ/ሺ**

1.ቦጋለች የነጻ ትምህርት እድል በማግኘት ትምህርቷን በራሽያ ተማረች፡፡

2. በከምባታ ባህል አባት ለክብሩ መግለጫ የሚጠራዉ የመጀመሪያ ወንድ ልጁ ነዉ፡፡

3. የቦጋለች የትምህርት ዘርፍ የዶክተሬት ድግሪዋ 'ኢፒዲሚዮሎጂ' ይባላል፡፡

4. ልማዳዊ ድርጊቶች ሴቶችን ለረዥም ዘመናት የጨለማ ህይወትን እንዲገፉ ምንም ሚና አልነበራቸዉም፡፡

5. ቦጌ "ሴት ልጅ መደቧ ማጀት ነዉ" የሚለዉን ባህላዊ ህግ የሻረች የመጀመሪያዋ የከምባታ ወጣት ነበረች፡፡

**ለ. ቀጥለዉ ለቀረቡ ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ፍችያቸዉን ስጡ**

1.ትጋት 6. በዘልማድ

2.ብጤዎች 7.ስመ መልካም

3.ቁምነገር 8.ግብረሰናይ

4.አነገቦ 9.ሽንጣቸዉን ገትረዉ

5.ቁርጠኝነት 10. ስነተዋልዶ

## ትምህርት አራት

### ሐ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የቀረቡት ጥያቄዎችን በቃል መልሱ

1. ባህል ካቀፋቸዉ ሰፊ ማእቀፎች የተወሰኑትን በመዘርዘር በንባብ አቅርቡ ?
2. ቦጌ በተማረችባት መነረደር ና ለአባቱዋ ምን አይነት ዉለታ አደርጋለች?
3. "ሴት ልጅን መገረዝ ቆሻሻ ማስወገድ ነዉ" ብሎ የሚያምነዉን ማህበረሰብ አመለካከት እንዴት መለወጥ ቻለች?
4. አራተኛና አምስተኛ አንቀጾች ያተኩሩባቸዉን ሀሳቦች በማሳጠር በንባብ አቅረቡ?

## ትምህርት አምስት

ቅድመ ንባብ ስራዎች

1. ስራና የምርት ግንኙነት እንዴት ይመስላቹሃል? ተወያዩበት?

2. ጠንካራ ሰራተኛ መሆን ይቻላል? ከሆኑስ ለራስ፣ ለወገንና ለሀገር ምን ጥቅም ያስገኛል?

### "የሠራ ያገኛል!"

ኢትዮጵያ በርካታ ሕጻናትና ወጣቶች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህን ወጣቶች የሚያሳድጉ ወላጆች፣ አከባቢዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፖሊሲ አዉጪዎችና ፖለትከኞች ስራ ፈጣሪዎችን የማብዛት ግዴታ አለባቸዉ፡፡ ልጆች ትልልቅ ራእይና አላማ እንዲይዙ በቂ ችሎታና ራኢይ እንዲኖራቸዉ ከሁሉም በላይ ወላጆች ሀላፍነት አለባቸዉ፡፡ በሁሉም መስፈርቶች እያደገ የሚሄድ ቤተሰብ ኀላፊ የሆኑ ወላጆች ያሉዋቸዉ ልጆች፣ ዉስጣቸዉን እመረመሩ የቤተሰቦቻቸዉን እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ህይወት የሚቀይሩና ለልጆቻቸዉ ሚሳሌ መሆን የሚችሉ ወላጆች ያሉዋቸዉ ልጆች ከወላጆቻቸዉ የበለጠ ባለ ራእይ ይሆናሉ፡፡ ሕይወት የተለያዩ አማራጮች እንዳሏት ልጆቻቸዉን ሲያስተምሩ፣ በሂደት የነሱ ህይወት ከእለት ወደእለት ለዉጥ እያመጣ ሲሄድ፣ በየቤተሰቡ ያለ አንድ ሁለት ሰዉ የራሴ የሚለዉ ሥራ ሲፈጥር ተነሳሽነት ያድጋል፡፡ "ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸዉ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸዉ!"

አሁን አሁን እንደሚታየዉ ወላጆች በጣም ዉስን የሆነ ህልምና ራእይ አላቸዉ፡፡ የሚያገጥሙዋቸዉን ችግሮች ሁሉ ከቤተሰብ አባላትና ከልጆች መኖር ስለመኖር ጋር የሚያይዙ አሉ፡፡ በመሰረቱ ህጻናት የተወሰዱ አይደሉም፣ ህጻናትን የሚንወዳቸዉ እኛ ነን፣

በየትኞቹም ሀላፍነቶች በአብዛኛዉ እኛ ወላጆች ነን፡፡ ከምንጠቀምበት በላይ ገቢ ለመፍጠር የምንንቀሳቀስ ወላጆች ስንበዛ በየቤቱ ያለ ድህነት ቀስ በቀስ ይጠፋል፡፡ ኢትዮጵያ የሚታድገዉ እያንዳንዱ ቤተሰብ የተሻለ ደረጃ ሲደርስ ነዉ፡፡

**ጊዜ ንባብ ስራዎች**

**ተማሪዎች ከላይ ካነበባችሁት ምን እንደተረዳችሁ በቡድናችሁ ተወያዩበት**

የኢትዮጵያ ትልቁ ሀብት ወጣቱ ነዉ፡፡ ወጣቱአስተሳሰቡ ብሩህ ነዉ፤ ትኩስ ጉልበት አለዉ፡ ከፍተኛ የመፍጠር ችሎታ አለዉ፤ ፈጣን ነዉ፤ አንድ ጊዜ የጀመረዉን ነገር ደጋግሞ በመስራት ለማሸነፍ ሰፊ የእድሜ ገጸ-በረከት ያለዉ የህብረተሰባችን ክፍል ነዉ፡፡ ከማንም የተሸለ መኖር የሚፈልገዉ ወጣቱ ነዉ፡፡ ይህንን ሁሉ ለማደረግ ብዙ መስራት ያለበትም ወጣቱ ነዉ፡፡

በጥቂትች የኢኮኖሚ ነጻ መዉጣት ብዙ ሰዉ ጥሩ ኑሮ መኖር አይችልም፡፡ የአስተሳሰብ ድህነትን የሚወርሱት ልጅ ባለጸጋ አይሆንም፤ አትሆንም፡፡ ስለዚህ ስራ ፈጣሪ ለመሆን የበለጠ እድል ላለዉ ለወታቱ የህብረተሰብ ክፍል የስራ ተነሳሽነትን ማስተማር ከሁሉም የሚጠበቅ ግዴታ ይሆናል፡፡

*(ወሮታዉ በዛብህ፣ እንትረፕረነርሽፕ፣1998፣109፣ለማስተማር እንዲመች ተብሎ የተወሰደ፡፡)*

ትምርት ስድስት

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች

ሀ. ቀጥለዉ ከምንባቡ የወጡ ዐረፍተ ነገሮችን በመመርመር ትክክል የሆኑትን “እዉነት” ያልሆኑትን “ሀሰት” በማለት መልሱ፡፡

1.ወጣቶች የስራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉ የማድረግ ሀላፍነት የወላጆች ብቻ ነዉ፡፡

2.ሀገር የሚያድገዉ እያንዳንዱ ዜጋ በኢኮኖሚ ስሻሻል ነዉ፡፡

3.የሀገርን እድገት በሚመለከት ትልቁን ድርሻ መወጻት የሚገባዉ ወጣቱ ነዉ፡፡

4.ወላጆች ለልጆቻቸዉ ማዉረስ ለባቸዉ ቀና አስተሳሰብና ታታርነትን ነዉ፡፡

5.ወጣቶች በሀገር ግንባታ ዘርፍ ሚናቸዉ አናሳ ነዉ፡፡

**ለ.ከዝህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጎች በምንባቡ መሰረት ፍችያቸዉን በመፈለግ በንባብ አቀርቡ፡፡**

1. የአስተሳሰሰብ ድህነት
2. ዉስን ህልምና ራእይ
3. ለልጆች ሚሳሌ መሆን
4. የእድሜ ገጸ-በረከት
5. ልምድ ያካበተ
6. ባለጸጋ
7. ፖሊሲ አዉጪዎች

**ትምህርት ሰባት**

ሐ.ቀጥለዉ የቀረቡ ጥያቄችን በምንባቡ መሰረት በቡድናቸሁ ተገቢዉን ምላሽ በመስጠት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በምንባብ አቅርቡ፡፡

1.ሥራ ፈተሪዎች ተባሉትን አካላት በመዘርዘር አብራሩ፡፡

2.ወጣቶች በሀገር ግንባታ ወሳኝ ሚና አላቸዉ፤ ስለዝሁ ሀሳብ ምክንያት አቅርቡ፡፡

3.ቀና አስተሳሰብ ያላቸዉን ወጣቶች ለማፍራት የወላጆች ሚና ከፍተና መሆኑ ተገልጸዋል፡፤ይህን ሀሳብ ከራሳችሁ ልምድ በመነሳት አስተያየት አቅርቡ፡፡

4.”ልምድ ያካበቱ ወላጆች ለልጆቻቸዉ ዩኒቨረስቲዎች ናቸዉ“ሲል ምን ለምለት ተፈልገዉ ነዉ?

5. የዚህ ምንባብ አጠቃላይ መልእክት ወይ ጭብጥ ምን ይመስላችሃል?

## ትምህርት ስምንት

## ምንባብ 3.

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ትረካዉ ስለምን ይመስላችዋል?

2. ባለታርኩ እየሰራ ለመማር ለምን የፈለገ ይመስላችዋል?

3. ቸ አይቨ. ኤድስ የሚያስከትለዉን ተጽእኖ ተወያዩበት

"እንዲህም ተኖረ!"

የተወለደዉ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህረቱን አጠናቅቆ ወደ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ስዛወር ወደ አዲስ አበባ በመሄድ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ትምህርቱን ተከታትለዋል፡፡ በትምህርቱ ጎበዝ ባይባልም ከሰነፎች ተርታ የሚመደብ አልነበረም፡፡

አዲስ አበባ ሰው ሱቅ ውስጥ ግማሽ ቀን እየሰራ ስማር በሥራው ምክንያት ገንዘብ ለመደና ትምህርቱን ዳር ሳያደርስ አሥራ አንደኛ ክፍል ለተወሠኑ ወራት ከተማረ በኋላ ትምህርቱን አቋርተዋል፡፡ የሚስራበት ሱቅ የሚገኘው መሀል መርካቶ ስለነበር የተለያዩ የንግድ ስራዎችን እንድያውቅ፣ እንዲቀርብና የተለያዩ ዕቃዎችን እንዲለይ አስችሎታል፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ዕቃዎች ከውጭ ሲገቡ እየተረከበ ለሌሎች ባለሱቆች መሸጥ ጀመር፡፡ በዚህ አይነት መንገድ ጠቀም ያለ ትርፍ ማግኘት ስለጀመር ሰው ሱቅ መስራቱን ተወና በድለላ ስራ ተሰማራ፡፡

ሱቅ ውስጥ እየሰራ በነበረበት ጊዜ ምንም ዓይነት ትርፍ ሰዓት አልነበረዉም፡፡ የሱቁን ስራ ከተወ በኋላ ግን፣ ትርፍ ጊዜ ማግኘት በመቻሉ የመጥፎ ሱስ ተገገር መሆን ጀመረ፡፡ ቀስ በቀስ ጫት ቃሚ ጓደኛኞችን አፈራና ከምሳ ሰዓት በኋላ የምዉለው ጫት ቤት ሆነ፡፡ ከጫት በኋላ ደግሞ እንቅልፍ አይወስደኝም በሚል ፈሊጥ ወደ መጠጥ ቤት ይሄዳል፡፡ አንድ ቤት መጠጥ ይጀምርና በሞቅታ ሳያውቀው ወደ ተለያዩ ቤቶች እየሄደ ሲጠጣ ያመሻል፡፡ ሰዓቱ እየገፋ ሲሄድ ወደ ቤት የመሄድ ነገር ያከትማል፡፡ መጠጡ ሲያደክመዉ ከአንዱ ሆቴል ውስጥ ከአንዷ ሴተኛ አዳሪ ጋር ማደር ጀመር፡፡ በዚህ ምክንያት ብዙ የቡና ቤት ሴቶች

ያውቁት ነበር፡፡ ስለዚህም ሞቅ ያለ ሰላምታ በማቅረብ ያስተናግዱት ጀመር፡፡ በስካር መንፈስ ብዙ ሴቶች እየጋበዘና እየተላፋ ያመሽና ስሰክር ከአንዷ ደንበኛ ጋር ያድራል፡፡ የሚገርመው ነገር በማግስቱ ጠዋት ካልሆነ በስተቀር አንዳንድ ጊዜ ያደረበትን ሆቴል እንኳን አያውቀውም ነበር፡፡

ጊዜ ንባብ ስራ

ተማሪዎች ከዚህ በላይ ያነበባችሁት አንቀጾች ስንት ናቸዉ?

በንባቡ የተገለጹ ሀሳቦችን ተነጋገሩባቸዉ?

በዚህ ሁኔታ ከቆየ በኋላ በ1988ዓ.ም መጨረሻ ላይ ሚስት ማግባት አለብህ የሚል ጥያቄ ከቤተሰብ ቀረበለት፡፡ በሃሳባቸው ተስማምቶ በ1988ዓ.ም መስከረም ወር ሚስት አገባ፡፡ ከአገባ በኋላ የመጠጡ ነገር በመጠኑም ቢሆን ልቆጣጠረው ሞከረ፡፡ ነገር ግን ባለቤቱ በቅርብ ስላልነበረች ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ አልቻለም፡፡ እንደ አጋጣሚ ከትዳር ውጭ ሌላ ቋሚ ጓደኛ በማግኘቱ ከዚህች ልጅ ጋር ብዙ ጊዜ አብረዉ ያሳልፍ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ 1989 ዓ.ም እና 1990ዓ.ምን አሳለፈ፡፡ ባለቤቱም ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጁን፤ ሚስቱንና ቤተሰቦቹን እየተንከባከበ ከመጥፎ ሱስ ተቆጥቦ መኖር ጀመር፡፡ ምን ያደርጋል ታዲያ ተቀድሞ ኖሯል! አንዳንድ የህመም ምልክቶች ማለት ሳል፣ ብርድ ብርድ የማለት ስሜት የሰማዉ ጀመር፡፡

የህመም ስሜት ሲደጋገምበት ሀኪም ቤት ሄዶ ተመረመረና የሳንባ በሽታ እንዳለበት ተነግሮት ህክምናውን መከታተል ጀመር፡፡ የታዘዘለትን መድሃኒት በትክክል ጨረሰ፡፡ የጤንነቱ ሆኔታ ለውጥ አሳየ፡፡ ሆኖም ግን ሥራዉን እንደበፊቱ ተሯሩጦ መስራት አልቻለም ከዚህ የተነሳ ሥራዉ ተዳከመበት፡፡

እየቆየ ከሣንባዉ ህመም ብያገግምም ሌሎች ተጓዳኝ ሽታዎችን ማስተዋል ጀመር፡፡ አልፎ አልፎ ያስቀምጧል፡፡ ትንሽ አየሩ ሲለወጥ ብርድ ብርድ እያለ ትኩሳት ይደጋገምበታል ሰውነቱም ቀነሰ፡፡ የሚሰማዉ የህመም ስሜት ለጓደኞቹ ስነገራቸው ምናልባት ኤችአይ-ቪ ሊሆን ይችላል በሚል የደም ምርመራ እንዲያደርግ መከሩት፡፡ እሱም በነገሩ ተስማምቶ ሁኔታዉን ለማረጋገጥ ሀኪም ቤት ሄዶ ደም ሰጠ፡፡ ውጤቱን ለመቀበል ሄዶም በደሙ ውሰጥ ኤችአይ-ቪ መኖሩ ተነገረዉ፡፡

ውጤቱን ሲሰማ ያለበትን አላወቀም ነበር፡፡ በኋላም ዶክተሩ አረጋግጦ ምክር ሰጠዉና መኖር እንደሚችል ነግሮት ሸሸዉ፡፡ በምክሩ ተጠቅሞ ቀስ በቀስ እየተረጋጋ መጣ፡፡ በጣም ያሳሰበዉና ዕረፍት የነሳዉ ነገር ቢኖር የባለቤቱ ጉዳይ ነበር፡፡ እሱም ኤች-አይ-ቪ በደሙ ውስጥ እንዳለ ሲነገረዉ እሷ ነፍሰጡር ነበረች፡፡ በልቡ እያዘነ መወለጃዋ ሲቃረብ ገጠር ሄዱ፡፡ አብሮዋት ሳምንት ያህል ከቆየ በኋላ ምጥ ሲጀምራት ሀኪም ቤት ይዞዋት ሄደ፡፡ ትንሽ በምጥ ከተቸገረች በኋላ ሴት ልጅ በሠላም ተገላገለች፡፡

ትንሽ ቆይታ ግን ህፃኗ በማታወቀው ምክንያት ሞተች፡፡ አስቀድሞ ግን ሆኔታውን ለሀኪሞች አማክሮዋቸው ስለነበር ለባለቤቱ ምርመራ አድርገዉላት ኖሮ እሷም ኤችአይ-ቪ በደሟ ውስጥ እንደሚገኝ ገለፁለት፡፡ ይህንን ግን ልነግራት አልደፈረም፡፡ ምንም ማድረግ አልቻለም ከልቡ ብያዝንም የምጠብቀው ውጤት ነበር፡፡ ቀደም ሲል እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ቋሚ ጓደኛ ይዞ እንደነበር ገልጾ ነበር፡፡ እሷም ስትመረመር እንደዚሁ ኤች-አይ-ቪ በደሟ ውስጥ መገኘቱ ተገለፀላት እንግዲህ ከሷ ሌላ በየቀኑ አብሮዋቸው ያድር የነበሩ ብዙ የተለያዩ ሴቶች ነበሩ፡፡ ቫይረሱ ወደ ደሙ መች እንደገባ የሚታወቅ ነገር ስለሌ በእሱ ምክንያት የስንቱ ህይወት እንደተበላሸ ቤት ይቁጠረው፡፡ እሱ የህግ ባለቤቱን በጓደኘነት የያዝኩት ልጅ ሌሎችም ቁጥራቸውን በውል የማናውቃቸው በቫይረሱ መበከላቸው በጣም ያሳዝናል በማለት ገለጸ፡፡

አሁን ወላጆቹ እርጅና እየተጫናቸው ነው፡፡ ረዳት ይፈልጋሉ፡፡ ግን ይረዳቸው ቀባሪ ማጣት ማለት እንዲህ ነው፡፡ የመጀመሪያው ልጅም ቫይረሱ ይኖርበታል ብሎ ይገምታል፡፡ እሱን ለዚህ ችግር አጋልጠው የሰጡት ጫትና የመጠጡ ሱሶች ናቸው፡፡ የሴተኛ አዳሪ ጓደኛ ማብዛቱ ደግሞ ለዚሁ ዳርጎታል፡፡

*ምንጭ፡- አለሙ ሳህሌ የሚናፍቅ ለውጥ 2003 አዲስ አበባ ኮድ ኢትዮጵያ ለማስተማሪያ ተደርጎ የተመቻቸ፡፡*

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

ትምህርት ዘጠኝ

ሀ.ከዚህ በታች የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆኑትን "እዉነት" ያልሆኑትን 'ህሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. የባለታርኩ አድስ አበባ መምጣት አላመዉ ለንግድ እንጂ ለትምህርት አልነበረም፡፡

2. ባለታርኩ በንግድ ሰራ ምክንያት ገንዘብ መልመዱ በትምህርቱ ላይ ምንም ተጽእኖ አላስከተለም፡፡
3. ለመጥፎ ሱሶች ተገዢ መሆን በራስና በቤተሰብ ላይ ለኤች አይ ቪ ኤድስ መጋለጥን አስከትለዋል፡፡
4. ከቡና ቤት ሴቶች ጋር ለመተዋወቁ ዋናዉ ምክንያት የቻትና መጠጥ ሱሰኛ መሆኑ ነበር፡፡
5. በዚህ ምንባብ ባለታርኩ በሚገርም ሁኔታ እየሰከረ ሆቴል ማደሩን ያዉቅ ነበር፡፡

**ለ. ቀጥለዉ የቀረቡ ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ፍችያቸዉን ስጡ፡፡**

1. ተቀድሞ ኖሯል፤፤
2. ማገገም
3. እርጅና እየተጫናቸዉ
4. ቀባሪ ማጣት
5. ተጓዳኝ በሽታ

ትምህርት አስር

ሐ. ቀጥለዉ የቀረቡ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በቡድናችሁ አመካኝነት በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አቅርቡ፡፡

1. በዚህ ንባብ ባለታርኩ ለተለያዩ ሱሶችና በሽታዎች መጋለጡ ምን መስላችሃል ?
2. ምንባቡ ስንት አንቀጾች አሉት ? የመጀመሪያዉን የመሀልና የመጨረሻ አንቀጾችን ሀሳብ አሳጥራችሁ አቅርቡ፡፡
3. ኤች አይ ቪ ኤድስ በግለሰብ በቤተሰብና በማህበረሰቡ ላይ ሚያስከትለዉን ችግር በመወያየት በንባብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
4. ለ ኤች አይ ቪ ኤድስ የሚያጋልጡ ነገሮችን በመዘርዘር ግለጹ፡፡
5. በምንባቡ ተጓዳኝ በሽታ በመባል የተጠቀሱት እነማን ናቸዉ?

አባሪ፡ ነ የድህረ ልምምድ ፈተና

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ ትምህርት

ኮድ_______

ለ10ኛ ክፍል ተጠኚ ተማሪዎች የተዘጋጀ ድህረ ትምህርት ፈተና(ከ30%)

ፈተናው የሚጀምርበት ሰዓት 2፡30 ሰዓት

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ2፡00 ሰዓት

አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች፤ የዚህ ፈተና ዋና አላማ ትብብራዊ ዘዴን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና ለመፈተሽ ለታቀደው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፤ ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት የሚመለሱ ሆነው ንዑሳን ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

ቀዳሚው ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ በምንባቡ መሰረት ትክክለኛዉን ሀሳብ መምረጥ፣ በቀጣይ የምንባቡን ዋና ዋና ሀሳቦች የያዘዉን በመለየት ማውጣት፣ ሶስተኛው የቃላትና ሀረጋትን ፍች መግለጥ ናቸው። ሁለት ምንባቦች ቀርበዋል። እያንዳንዱን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በመሆኑም የቀረቡትን ምንባቦች መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ ነው የምትሉዋቸውን ለመልስ መስጫ በተሰጠው ቦታ አመልክቱ፡፡

## ምንባብ1

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1ሰዎች ወደ ሱስ ለምን ይገባሉ? ሱስን እንዴት ትገልጹታላችሁ?

2.በአከባቢያችሁ የተለመደ ሱስ ምን ይመስላችዋል? ምክንያቱስ?

3.የሱስን አስከፊ ባህሪ ግለጹ?

"የጉለሌዉ ሰካራም"

"በጉለሌ የነበረዉ የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማንዉ?" ብለዉ ከገፈርሳ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቁ ሰዎች "ተበጀ/ ሰካራሙ ተበጀ/ ዶሮ ነጋዴዉ ተበጀ ነዉ/" ብለዉ ይነግራቸዋል፡፡ የህይወቱ ታርክ ፍጹም ገድል ነዉ፡፡ጢም ያለዉ ሽማግሌ ሰዉ ነዉ፤ የራሱን ጸጉር ዉሀ ወይም መቀስ ነክቶት አያዉቅም፡፡ማለዳ አይናገርም፤ በጠርሙስ ሞላዉን ከጠጣ በኋላ ማታ ሲራገም ወይም ሲሳደብ፣ ሲፎክር ወይም ሲያቅራራ ድምጹ ከፈረንጅ ዉሻ ድምጽ ይወፍራል፡፡ ቢያዉቀዉም ባያዉቀዉም ካገኘዉ ጋር ሁሉ ማታ ይስቃል፡፡የሰላምታዉ አይነት እንደ ወታደር ወይም እንደ ሲቪል ቢሆን ለርሱ እንደተመቸዉ ነዉ፡፡ ከሰላምታዉ ጋር ድምጽ ትሰማላችዉ ከአፉ የሚወጣዉን አንድ ቃል ግን መለየት አትችሉም፡፡

**ተማሪዎች ከላይ ካነበባችዉት አንቀጽ ተበጀ ምን አይነት ሰዉ ነዉ? ማህበረሰቡ ስለሱ ያለዉ አመለካከት ምን አይነት ይመስላችዋል?**

ከሚያሰክር ነገር ሁሉ ለመታረም አስቦ ነበር፡፡ ሰክሮ ያደረበት ሌሊት አልፎ ብርሀን በሆነ ጊዜ "ከእንግዲህ መጠጥ አልቀምስም እያለ በየቀኑ ምሏል፡፡ በነጋታዉ የበለጠ ተጥቶ የባሰ ሰክሯል፡፡ለመስከር ይጠታል፤ደስ ያለዉ እንዲመስለዉ ይጠጣል፤ ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል፡፡ቡና በተፈላ ጊዜ በጉለሌ ቤምድጃዉ ስር መለረኩን አይተዉ ያላወቁ ባልተቶች እንኳ በፍንጃል ቡናን ፉት እያሉ ሌላዉን ሰካራም ተረት በተበጀ ላይ እያላከኩ ይሳሳቁበት ነበር፡፡

"ይህን መስከርህን ካልተዉህ ላንቴ ንስሀ አባት አልሆንህም" ብለዉ የመጀመሪያ ንስሀ አባቱ ብዙ ከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከእርግማን ጋር አስወግደዉታል፡፡ሰራተኞቹም ለርሱ ተቀጥሮ መስራትን ከዉርደት ቆጥረዉት ቨእየነቀፉት ሂደዋል፡፡ "መጠጥ ካልተዉህ

አናገባህም ብለዉ በየጊዜዉ ለጋብቻ ጠይቆዋቸዉ የነበሩ በቁመነዉ አሰናብተዉታል፡፡ በሰንበቴም፤ በማህበርም ማህበርተና ለመሆን የጠየቃቸዉ ነፍሱን ሳይቀር ንቀዉታል፡፡

ብዙ ጊዜ ሰክሮ ኦቶሞቢል ሂዶበታል፡፡ሰክሮ በነጋታዉ ሲነቃ እራሱን እስር ቤት ዉስጥ አህኝቶታል፡፡ በጉለሌ መንገድ ዳር ባሉት በብዙ የዉሃ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ ጉለሌ ህዝብ አዉጥቶታል፡፡ሰክሮ ጎረሰፍ ዉሃ ከወሰደዉ በኋላ ብዙ ጊዜ የእሳት አደጋ ደርሶለታል፡፡ ሰክሮ ከቤቱ መድረስ እያቃተዉ ከወደቀበት ባቡር መንገድ ሳይነሳ፣ ብዙ ጊዜ በላዩ ላይ ጎርፍ ሲሄድበት አድሯል፡፡

ሰዎች መልካም ሰማእትነት ስራዉን ሁኩ ርካሽ አድርገዉ ይቆጥሩበታል፡፡ በግብረገብ መሰረት አደረግሁት ሚለዉን ሁሉ በስካር እንዳደረገዉ ያናንቁበታል፡፡ "በጎ ስራህን ሁሉ በትኩስ መቃብር ዉስጥ አፈር አለበስከዉ፤ አንቱ ሰዉ ሰዉ ሁን ሚስት አግባ ልጆች ይኑሪህ" ይሉና ዘልፉት ነበር፡፡ይህ ሁሉ ዉርደትና ርክስት ነዉ እንጂ ክብር ከቶ አይደለም፡ ፡ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰዉ ከሰዉ በታች ነዉ፡፤ ሰዎች ይሸሹታል፤ ፍጹም ወዳጅነቱንና ዝምድናዉን አይሹም፡፡ እናም ኑሮዉበጨለማ እንደተከበበ ይሆናል፡፤የሰካራሙ ተበጀም እጣ ይሀዉ ነበር፡፡

*(ተመስገን ገብሬ፤የጉለሌዉ ሰካራም፣ 1941፡1-8 ለማስተማሪያ እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ)*

**የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች**

**ክፍል አንድ፡- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥለዉ ቀረቡትን ትክክል ከሆኑ "እዉነት " ስህተት ከሆኑ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡** (9%)

------1.ተበጀ የተባለዉ ሰዉ በአከባቢዉ የሚታወቀዉ ችፍግ ባለ ጽሙና በጎፈሬ ፀጉሩ ነዉ፡፡

---------2..ተበጀ ድምጹ ሚሰማዉና ለአንባጓሮ የሚነሳሳዉ መጠጥ ከጠጣ በኋላ ነዉ፡፡

--------3.ተበጀ ምንም እንኳ በመጠጥ የተጠመደ ቢሆንም በማህበራዊ ህይወቱ ተሳክቶለታል፡፡

**ክፍል ሁለት፡- በምንባቡ መሰረት ከአማራጮቹ ትክክለኛዉን መልስ በመምረጥ መልሱ**(9%)

4."የተበጀ የህይወት ታርክ ፍጹም ገድል ነዉ" ሲል -----------------ማለት ነዉ፡፡

ሀ. አስቅኝ ለ. አስገራሚ ሐ. አስደንጋች መ. አስፈሪ

5. የጉለሌ ባልተቶች የቡና ማጣፈጫ ወሬ የተበጀ ---------------ነዉ፡፡

   ሀ.አረመኔነት ለ. ሰካራምነት ሐ.ቅጥ ያጣ ድፍረት መ.ዶሮ ነጋዴነት

6. ተበጀ በመጠጥ ሱሰኝነቱ በአከባቢዉ ማህበረሰብ --------------------------ነበር፡፡

   ሀ.የተረሳ ለ. የተደነቀ ሐ. የተወደሰ መ. የተገለለ

**ክፍል ሶስት፡- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥለዉ ላሉት ቃላትና ሀረጎች በ "ሀ" አምድ ላሉት ከ"ለ" አምድ ካሉት አዛምድ(12%)፡፡**

| <u>ሀ.</u> | <u>ለ.</u> |
|---|---|
| 7. ሲያቅራራ ---------------- | ሀ.ማሳበብ |
| 8. ማላከክ ------------------- | ለ.ሲፎክር |
| 9. ፉት እያሉ -------------- | ሐ.መልካምነት |
| 10. በጎ ስራ ------------------ | መ.እየጠጡ |

## ምንባብ 2

### ኔልሰን ማንዴላ

ኔልሰን ማንዴላ (1918-2013) ደቡብ አፍሪካዊ የፖለቲካ አቀንቃኝ ሲሆን የአፓርታይድ አገዛዝን በመቃወም ከ20 ዓመት በላይ በእስር አሳልፏል፡፡ እ.ኤ.አ በ1994 ማንዴላ የመጀመሪያው አፍሪካዊ መሪ ሆኖ ተመረጠ እ.ኤ.አ በ1993 የኖቬል የሰላም ሽልማት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የነበረውን የዘር መድሎ ለማስቀም ባበረከተው አስታዋፅኦ ተሸልሟል የደቡብ አፍሪካ ዲሞክራሲያዊ አባት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እንዲሁም አገሪቱን አንድ ለማድረግ ባበረከተው አስታዋፅኦ በስፋት ይደነቃል፡፡ ኔልሰን ማንዴላ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እጅግ ከሚደነቁ የፖለቲካ መሪዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በተለይም የሚታወቅበት በአዲሱ አገር ይቅርታ ስለማድረግ ባደረገው አስተዋፅኦ ነው፡፡

ኔልሰን ማንዴላ ትራንስ አይ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ እ.ኤ.አ በሐምሌ 18 ቀን 1981 ተወለደ፡፡ ኔልሰን ማንዴላ በጠሳ ጎሳ መጠሪያ በሚል ሜልባ በሚል ይታወቃል፡፡ ማንዴላ የአካባቢው ጎሳ መሪ ቴምብል ጎሳ አባል ነው፡፡ በወጣትነቱ ኔልሰን ማንዴላ በአካባቢው ጎሳ ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶች ላይ ይሳተፍ ነበር፡፡ ማንዴላ በፎሮት ሄር ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና ሜተማር ስለአንድ ዩንቨርስቲ ትምህርቱን ተከታትሏል፡፡ ኔልሰን ማንዴላ ጎበዝ ተማሪ ሲሆን በ1942 በህግ ዲግሪውን አግኝቷል፡፡

በዩንቨርስቲ ቆይታ ኔልሰን ማንዴላ ነጭ ባልሆኑ ዜጎች ላይ የሚደርስባቸውን የዘር መድሎ እና እኩልነት ማጣት እንዲሁም ኢ-ፍታዊነት ተገንዝቧል፡፡ በ1943 የኤኤንስ ፓርት መሳተፍ ጀመረ፡፡ በወቅቱ ከነበሩት ጥቂት የትግሉ የህግ ባለሙያዎች መካከል አንዱ የነበረው ኔልሰን ማንዴላ በእጅጉ ይፈለግ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኤ-ኤንስ ፓርቲ ውስጥ ባሳየው ቁርጠኝነት ወደ ከፍተኛ አመራር ደረጃ ተሸጋግሯል፡፡ እ.ኤ.አ በ1956 የኤ-ኤንስ አባላት ጋር ታስሮ አገር በመክዳት ክስ ተመስርቶበታል፡፡

ከተንዛዛ የፍርድ ሂደት በኋላ ተከሳሾቹ እ.ኤ.አ በ1961 በነፃ ተለቀቀ፣ ሆኖም ግን ኤ-አንስ በበኩሉ ኔልሰን ማንዴላ በአፓርታይድ አገዛዝ ላይ በጦር ነይል የተመራ መቋቋም እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል፡፡ ይህም ለኢምኮንተሄሊዝዌ መሰረት አስተዋፆኦ አድረጓል፡፡ ይህን ቡድን የደፈጣ ተዋጊ ቡድን ነበረ አምኮንት ዊሲዝዌ በበርካታ የአፍሪካ አገራት ስልጠና በመውሰድ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የተለያዩ ጥቃቶችን ማድረስ ጀመረ፡፡

እ.ኤ. አ በ1963 ማንዴላ እንደገና ታሰረ እና በአገር መክዳት ተከሰሰ፡፡ በዚህ ጊዜ መንግስት ማንዴላ የደቡብ አፍሪካን መንግስት ለመጣል አሴረዋል ሲል የጥፋተኝነት ወሳኔ ወሰነ፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩ ዓለም አቀፍ ትኩረትን በማግኘት እና የደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ አገዛዝ በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ሥር ጥብቅ ቁጥጥር ወደቀ፡፡ ከፍርድ ሂደት መጠናቀቅ በኋላ ኔልሰን ማንዴላ ረጅም ንግግር አደረጉ፡፡ በዚህ ንግግር ላይ ለዲሞክራሲ ስላላቸው እሳቤ ቁርጠኝነት ማረጋገጥ ችሏል፡፡

የማንዴላ የሞት ፍርድ ወደ ዕድሜ ልክ እስራት ተቀይሮ በ1964-1981 በኬፓታውን አቅራቢያ በምትገኝ ሮበን ደሴት እስር ቤት ውስጥ ታሰረ፡፡ እስር ቤት ውስጥ ሁኔታዎች በጣም አስቸጋሪ ነበሩ፡፡ ሆኖም ግን ማንዴላ ከሌሎች በርካታ የፓለቲካ እስረኞች ጋር በመሆን የጠበቀ ጓደኝነት ለመመስረት እና አስቸጋሪን የእስር ቤት ሁኔታ ለመቋቋም ችሏል፡ ፡ ከዚህ በተጨማሪ እስር ቤት ውስጥ ሄልሰን ማንዴላ ከፍተኛ ስነ ምግባር ያሳይ ነበር፡፡ እስር ቤት ውስጥ በየዕለቱ ጥናት እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያደርግ ነበር፡፡ ከረጅም ጊዜ በኋላ ስለ እስር ቤት ጊዜ ቆይታው ሲናገር ወቅቱ ከባድ ትምህርት የተማረበት ጊዜ እንደሆነ እና እንዳውም በጣም አስቸጋሪ ነበር ብሏል፡፡ በእስር ቤት ቆይታው በመላው ዓለም ለመታወቅ በቅቷል፡፡ ሄልሰን ማንዴላ እ.ኤ.አ ታህሳስ 5 ቀን 2013 ከረጅም ጊዜ ህመም በኋላ በቤተሰቡ ተከቦ በ95 ዓመቱ ህይወቱ አልፋል፡፡

*ምንጭ፡ከዓለማችን ታላላቅ ሰዎች ታሪክ መጠነኛ መሻሻል ተደርጎ የተወሰደ*

**ክፍል አንድ፡- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥለዉ የቀረቡትን ትክክል ከሆኑ “እዉነት “ ስህተት ከሆኑ “ሀሰት“ በማለት መልሱ፡፡** (9%)

1. ኔልሰን ማንዴላ ዘረናዉን አፓርታይድ አገዛዝን ደግፈዉታል፡፡
2. ደቡብ አፍርካን አንድ በማደረግ ማንዴላ ጉሊህ ሚና ነበረዉ፡፡
3. ኔልሰን ማንዴላ ከፖለቲካ አቀንቃኝነት ባለፈ ባከባቢዉ ባህላዊ ስራ አልተሳተፈም፡፡

**ክፍል ሀለት፡- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥለዉ የቀረቡትን አራት አማራጮች ትክክለኛዉን በመምረጥ አመልካቱ፡፡** (9%)

4.ማንዴላ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዉ ከተገነዘባቸዉ እዉነታዎች ያልሆነዉ

ሀ.የነጭ የበላይነት ለ. ኢ-ፍታዊነት ሐ. እኩልነት መ. የዘር መድሎ

5.የደቡብ አፍርካዉ ዘረኛ ፓረቲ መጠሪያዉ

ሀ. ኤ-ኤንሲ ለ. አፓረታይድ ሐ. ቴምብል መ. ሁሉም

6.ለኔልሰን ማነውዴላ እዉቅናና የሰላም ሽልማት ምክንያት የነበረዉ

ሀ.አፐረታይድ አገዛዝን መቃወም ለ. የፖለቲካ ስኬት ሐ. ይቅርታ ስለማድረግ መ. ሁሉም

**ክፍል ሶስት፡- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥለዉ የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ ሀ አምድ ላሉት ከ ለ አምድ ተመሳሳይ ፍች ጋር አዛምድ ፡፡** (12%)

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| --------7. አፓርታይድ | ሀ.የዘር መድሎን የታገለ ፓርቲ |
| ----------8. ኖቬል | ለ.የዘር መድሎ አገዛዝ |
| ----------9. አምኮንትዊዝዌ | ሐ. የደፈጣ ተዋጊ |
| ------------10. ኤ-ኤንሲ | መ.የሰላም ሽልማት |